በፍቅር፥በሰላም፥በአንድነት
ተከባብሮ ለመኖር
መደማመጥ፥
መቻቻል

ህዳር ፲፱፻፹፮
፪ኛ ዓመት ቁጥር ፬

የአማርኛ የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት

$2.50

# ላ ን ዳ ፍ ታ



ኑሮ በአሜሪካ

ልብወለድ

ትውውቅ ፍቅር

ጋብቻ

"ባንዲራዬን ሊከለክሉኝ አይችሉም"
ብሩክ ታደሰ

"ፖትርያርኩ በአሜሪካ ተቃውሞ ገጠማቸው"

# LANDAFTA

November 1993 · Volume II No. 4

An Amharic Family and Entertainment Bi-monthly Magazine
(Amharic is the official language of Ethiopia)




# የኢትዮጵያ መንደር





## ETHIO VILLAGE

CAFE & RESTAURANT

**3462 N. Clark St.**
**Chicago, IL 60657**
**(312) 929-8300**

CATERING AND CARRY OUT AVAILABLE

ቀይ ወጥና ዝግኑ ዶሮ ወጥ አልጫው፤
አትክልት ከሥጋ ጋር ምንቸት አብሽ ክትፎው።
የአበሻ ዳቦና ቆንጆ የማር ጠጅ፤
ሽታው ግቡ ይላል ሳይገቡ ከደጅ።
ቆርጠው በሩን ከፍተው ገባ ሲሉ ገና፤
አገር ቤት የገቡ ያስመስላልና።
የሰኞ ዕለት ዱለት የበግ ወጥ ፍትፍቱ፤
ረቡና ዓርብ ዕለት የጾም በያይነቱ።
በስምንት ዓመት ልምድ የሙያ ክምችት፤
ፍጹም ኢትዮጵያዊ በሆነ ዝግጅት፤
ኢትዮ ቪሌጅ ይምጡ ሲያሻዎት መደሰት።




# ማ ው ጫ


2 ከአዘጋጁ

3 ደብዳቤዎች

5 ልብ ወለድ
"ውበት" (መኰንን ገሠሠ)
"የዴብራ ጦስ" (ገረሱ)

13 ትኩረት
"የመደራጀት አስፈላጊነት"
"ከሌሎች ልምድ ብንማርስ"

18 ኑሮ በአሜሪካ
"ሥራ ማግኘት. . እንዴት?" የቀጠለ
"ተተኪውን ትውልድ መንከባከብ"
"የሳንባ ነቀርሳ" (ዶ/ር ከንፈ ገበየሁ)
"እውነትም ወለም ዘለም" (ዘለቀ ንጋቱ)
"ለእህት አዛለች . . .(ኤደን ዳንኤል)
"አመሰግናለሁ" (ኤልሣቤጥ ገበየሁ)

30 እንዲህ ሆነ
"የመስቀል በዓል በአትላንታ"
"ለቢል ካምብል ኢትዮጵያውያን ድጋፍ ሰጡ"
"ፓትርያርክ ጳውሎስ ተቃውሞ ደረሰባቸው"

34 አዳምና ሔዋን
"መፈለግና አለመፈለግ" (አንዱዓለም)
"እሱና እሷ"
"ተው እንተዛዘን!" (አልማዝ ገ.እ.)
ጓደኛ ለሚፈልጉ

40 እስፖርት
"የሚደነቅ እስፖርተኛና ደራሲ ወጣት"

43 የአበው ቅርስ
ቅኔ/ተረትና ምሳሌ/እንቆቅልሽ

45 ቢስቁም ባይስቁም

46 ጨዋታና ሰንጠረዥ




የአትላንታ ኢትዮጵያዊያን ሕጻናት
(ገጽ 20 )



ቢል ክምብል ከኢትዮጵያዊያን ጋር
(ገጽ 31 )



የመስቀል በዓል በአትላንታ
(ገጽ 30 )

የሽፋን ፎቶ - ወጣት እስፖርተኛ ብሩክ ታደሰ ከብራዚሊያዊው ጓደኛው ጋር (ገጽ 40)

"ላንዳፍታ" የግል መጽሔት ናት። የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ የአዘጋጆቹን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሑፎቹን በሬዲዮ፤ በቴሌቪዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ በከፊልም ሆነ በሙሉ አባዝቶ ለማሰራጨት የጸሐፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።

የሽፋን ርዕስ - ጐጆ ማተሚያ (ኦርላንዶ)

©COPYRIGHT LANDAFTA 1993

ላንዳፍታ
ኅዳር ፲፱፻፹፮
፪ኛ ዓመት ቁጥር ፬
LANDAFTA
November, 1993 V. 2 - No. 4

**Publisher/Editor**
*Mekonnen Gessesse*
**Contributing Editors**
*Girma Zegeye*
*Abera Sisay*
**Editorial Advisors**
*Dr. Abera Molla*
*Haile Demissew*
*Solomon Melesse*
*Dr. Tilahun G. Hiwot*
*Dawit Deres*
*Zelleke Nigatu*
**Editorial Assistant**
Woinishet Bekele

**Distribution**
Atlanta, GA
California Mart
Taste of Ethioipia
Sweet Auburn Grocery
Chicago, IL
Ethio-Village Rest.
E.C.A.C.
Tesfaye B. (Hoddo)
Yeshi Gessesse
Dallas, TX
ET. Beauty Supply
Hartford, CT
Dr. Tilahun G. Hiwot
L.A., CA
K RAH Market
New York
Gion Ethiopian Rest.
Oak Land, CA
Albo-African Shop
Seatle, WA
Amy's Merkato
St. Louis, MO
A & Z Liquor
St. Paul, MN
Bayibih Medfu
Washington D.C.
Addisu Gebeya
Family Food Market
Merkato Market
San Diego, CA
Hotel Sandiego Gift Shop
Windsor, Ontario
Tewodros Zewdu

Landafta
P.O.Box 49301
Atlanta, GA 30359
Phone: (404)728-9122

*Landafta is an independent magazine published in Amharic bi-monthly. Views expressed do not necessarily represent that of its editors and advisors.*

# ከአዘጋጁ

እንደምን ከረማችሁ። ይኸው ደግሞ ብቅ ብለናል። ከተለያዩ አንባቢያን በሚቀርብልን አስተያየት እየተገነባን አቀራረባችንን እያሻሻልን ነን። አያያዛችን ደግ ከሆነ "ጐሽ"፣ በሉን ካልጣማችሁ "አአይ ምነው?" በሉን። እናንተን ደስ ካላለ ምን ሊረባ።

በአለፈው ዕትም ቃል እንደገባነው "ትኩረት" የተሰኘ አምድ ከፍተናል። እየተበታተንን መሄዳችን፣ ያለመሰባሰባችን አዝማሚያ አደገኛነቱ እየታየን ቁጭ የምንልበት ምክንያት የለም። "እስቲ የሚያቀራርቡንን፣ የሚያግባቡንን ነገሮች እያጐላን ልዩነታችንን አቻችለን እንሰባሰብ፤ ያለኛ ለኛ ማን አለንና" ብለናል። "ፍቅር፣ ሰላም አንድነትና ተከባብሮ መኖር" የብልጽግና ፈላጊ ዘመናዊ ሰው መርሆ ነው። "ትምክህት፣ ጠባብነት፣ ትዕቢት፣ ንቀት" የራስ ወዳድነት ኋላቀር በሽታ ነው። መበታተንና የጐሪጥ መተያየት የዘረኝነትና የትምክህት በሽታ ነው።

ዜና ጠቀስ የሆኑ እዚሁ አሜሪካ አገር የተፈፀሙ አበይት የምንላቸውን ክንውኖችም ማቀራረብ ጀምረናል። አምዱን "እንዲህ ሆነ" ብለነዋል። በየአላችሁበት ቦታ የተፈፀመ፣ የተደረገ ሌላው እንዲያውቀው የምትፈልጉት ነገር ካለ በተቻለ መጠን ከፎቶግራፍ ጋር ላኩልን። የኮሚኒቲዎች፣ የማህበራት እንቅስቃሴ፣ ኢትዮጲያዊያን በጋራ የሠሯቸው ሥራዎች፣ የመሳሰሉትን በጣም እንፈልጋለን። የፓትርያርክ ጳውሎስ የአሜሪካ ጉብኝት በዚሁ አምድ ውስጥ አካተን አቅርበነዋል።

አምዶቻችን ሁሉ እንደተጠበቁ ናቸው። የዛሬው የ"እናስተዋውቃችሁ" አምዳችን ከእስፖርት አምድ ጋር አያይዘነው እስፖርተኛና ደራሲ ወጣት ብሩክ ታደሰን አቅርበንላችኋል።


አስተያየታችሁን ላኩልን። በየመዘክራችሁ ያሉ ጠቃሚ ናቸው የምትሉዋቸው ወገኖቻችሁን ማሳወቅ የምትፈልጉትን ነገር ሁሉ ላኩልን።

## ማሳሰቢያ


በላንዳፍታ መጽሔት ላይ እንዲወጣላችሁ የምትፈልጉት መጣጥፍ፤ ደብዳቤ፣ ማስታወቂያና የመሳሰሉት ሁሉ ለዝግጅታችን ክፍል የሚደርሱበትንና መታተም የሚችሉበትን ጊዜ በማስመልከት ይህን እናሳስባለን።

ለSept እትም በ August መጀመሪያ ሳምንት ድረስ የደረሱንን
ለNov እትም በ Oct መጀመሪያ ሳምንት ድረስ የደረሱንን
ለJan እትም በ Dec መጀመሪያ ሳምንት ድረስ የደረሱንን
ለMarch እትም በ Feb መጀመሪያ ሳምንት ድረስ የደረሱንን
ለMay እትም በ April መጀመሪያ ሳምንት ድረስ የደረሱንን
ለJuly እትም በ June መጀመሪያ ሳምንት ድረስ የደረሱንን

የላንዳፍታ መጽሔት ደምበኛ ይሁኑ፤
የማዘዣው ቅጽ በመጨረሻው ገጽ ይገኛል።



# ደ ብ ዳ ቤ ዎ ች



ይድረስ ለላንዳፍታ መጽሔት አዘጋጆች

ሰላም ለናንተ ለኛም ይሁን እንደምን አላችሁ? ጉጆ ሲቀለስ መጀመሪያ ምሰሶው ይቆማል ከዛም ቀስ በቀስ የጣራውና የግድግዳው እንጨቶች እንዲሁም ለክዳን የሚሆነው ሳር ይጨማመርና ጎጆው ጎጆ ይሆናል። ታድያ የናንተን የመጽሔት ዝግጅት ጅማሮ በጉጆው ብንመስለው እናንተ ምሰሶው ትሆናላችሁ ማለት ሲሆን እኛ ደግሞ ጣራና ግድግዳ በመሆን ካልተባበርናችሁ ጉጆው ጉጆ መሆን የማይችለውን ያህል ብዙኃኑ ያልተሳተፈበት የመጽሔት ዝግጅት ደግሞ በጅምር የቀረው ጉጆ አይነት እንዳይሆን ብዬ በመስጋት መጣጥፌ ምንም እንኳ አጠር ብትልም በመጠኑም ቢሆን አንድ ቦታ ትሸፍናለች ብዬ በማመን ልኬያታለሁ። ጽሑፉ በማጠሩ ቅር አይበላችሁ

"አጭር ናት ይላቷል እድሜያቸው ይጠር
ኵረሪማ እኮ ነው ወጥ የሚያሳምር።"

ብሏልና ዘፋኙ እስኪ እንግህ ለማንኛውም እንያት።

ተሻለ መንግስቱ (ከኒዮርክ)

ከአዘጋጁ፤— እናመሰግናለን። የላኩልንን መጣጥፍ በአሁኑ እትም እንዳናወጣው ከጨረስን በኋላ ነው የደረሰን። በሚቀጥለው የገና ልዩ እትም ላይ ይወጣል።

ይድረስ ለተናፋቂዋ ለላንዳፍታ አዘጋጅ፤
በቅድሚያ ሰላምና ጤና በአዲሱ ከተማ እመኝልሀለሁ። ላንዳፍታ ሰፋ ባለ ሁኔታ እያደገች ስለሆነ እጅግ ደስ ብሎኛል። ስለ ዳሎል የአሁኑ ባሮናና፣ ጊዜ ሰፋ ባለ ሁኔታ ታሪካቸውን ሐቁን እንድናውቅ ስላደረጋችሁን በጣም አመሰግናለሁ። እንደ ዕንቁ ብርቅ የሆኑትን ውድ የኢትዮጲያ ልጆች በነሱ የሙዚቃ እድገት የምናገኘው ቦታ ከፍተኛ ነው። በቅርቡ የባሮ ባንድ ላንሲንግ (ሚቺጋን) በተጫወቱ ጊዜ የሁሉንም ልብ ነው የነኩት።

ሃሜት የተባለ የነገር አተላ፣
ይቀራል ከፈጣሪው እሱኑ እየበላ።
ላንዳፍታ አወጣችው አሜቱ ደቀቀ፣
ሙዚቃችሁ ሁሉ ባለም ላይ ዘለቀ።

በሉልኝ።
ዘለቀ በርታ ሃሳብህና አላማህ ልቤን ነው የነካው። ሁላችሁም በርቱ ተበራቱ።

ቴዎድሮስ ዘውዱ (ከዊንድሰር ካናዳ)

ይድረስ ለተወዳጅዋ ላንዳፍታ አዘጋጆች፤— ለጤናችሁ እንደምን ናችሁ? ላንዳፍታን ባንዳፍታ ተመልክቼ ባነበብኩት ስለረካሁ ወደድኳት። ጽሑፋችሁ ትምህርት ሰጪና አዝናኝ በመሆኑ አስደስቶኛል። ሁለተኛ አመት ቁጥር አንድ በእጄ የገባችሁ ባጋጣሚ ነው። ሠፈራችን እንደቆሎ ተማሪ ያልዞረችበት ቤት የለም። እኔም ያለኝን ከሰጠሁ ንፉግ አልባልምና የጎባን ግጥምና እንቆቅልሽ ልኬላችዋለሁ። ሚዛን ከደፋ ለእትመት አብቁ።

መዝገቡ ዘመነ (ጉንደር ከተማ)

ከአዘጋጁ፤— እናመሰግናለን።

ይድረስ ላንዳፍታ!

ሰላምና ጤና ከልብ የምመኝላችሁ ከዚሁ ኬኒያ የስደት ምድር ላይ ሆኜ ነው። ኸረ ለመሆኑ እንዴት ከረማችሁ? እጅ ነስቻለሁ! መጽሔታችሁ በጣም አርክታኛለች። እሰዬው እደጊ ተመንደጊ! ብያታለሁ። እኔንም ዛሬ ለብዕር አብቅታኛለች! እኔ እንኳን ተሳታፊ ልሁን ብል አቅሙ ሊያንሰኝ ሆነ፣ ታድያ ጨክኜ ለናንተ ለመላክ ተነሳሁ። አንድ ትልቅ ጉዳይ ነው የማጫውታችሁ። ሀተታም አይደል አንድ ቁምነገር ነው። እዚህ በኬኒያ የሚኖሩ ስደተኞች በተለይ አበሻ በዘር እየተከፋፈለ እርስ በርሱ ሲቦጫጨቅ፣ ሲመቀኛኝ አንዱ ባንዱ ሲዋሽ፣ ሲበላላ ብታዩ ለጉድ ነው። ወደዚያ ለመምጣት በፕሮሴስ ላይ ያለውን ሰው "ወንድሙ አይደለም፣ እህቱ አይደለችም፣ ሚስቱ አይደለችም፣ ባሏ አይደለም" እየተባለ ኸረ ስንቱ? መገፋፈጥ በዝቷል። ድርጊቱ የሚደረገው ዛሬ ሆኖ አይደለም አመታትን እያስቆጠረ ነው። ዛሬ በጣም የሚያበሳጨኝና እናንተ ጋ ለማድረስ ያነሳሳኝ በጐ አድራጊዎችም በእኛ ቅን አመለካከት እንዳይኖራቸው ይኸው ጉዳይ ያሰናክላቸዋል። አብዛኞቹ ከእናንተ አካባቢ ቤተሰብ ያላቸው ገንዘብ እየላኩ የሚያኖሯቸው ችግርን አያውቋትም። እኛን የመሰሉ ግን በራሳችን ተጣጥረን የምንኖር ከውጭ ረዳት የሌለን በከፍተኛ ችግር እንገኛለን። እባካችሁ! በኢትዮጲያ አምላክ ይዣችኋለሁ እዚህ ላለ ሕዝብ "ላንዳፍታ" ጭንቅላት የሚመታ ምክር አዘል ደብዳቤ ጫር ብታደርጉላቸው ይከፋ ይሆን! እንግዲህ መልካም ቆይታ እየተመኘሁ ዘልቂያለሁ! ያሰንብትልኝ!

ሰለሞን ዮሐንስ (ከኬኒያ)

ለላንዳፍታ አዘጋጅ፤- መጽሔትህን በጣም ወድጄአለሁ። ውጪ ባለን ኢትዮጵያውያን መሐል ትልቅ አሳሳቢ ጉዳይ እተፈጠረ ነው። በወገኖቻችን መሐል የመጠላላት በሽታ እያየለ ነው። አገር ቤት ይኸው በዘር የመለያየት መርዝ ቢረጭም ሕዝባችን ተከባብሮ ለዚህ መርዝ ሰለባ ሳይሆን መቆየቱ ለኛ ትምህርት ሊሆን በተገባ ነበር። አዕምሮአችን በዚህ የዘረኝነት ልክፍት እንዲበከል የሕዝብን አንድነት የማይፈልጉ ኃይሎች የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም። ለሚያልሙት መሰሪ ዓላማ እንዲያመቻቸው የሚጠቀሙበት ዘዴ ሕዝብን መከፋፈል ስለሆነ ልንነቃባቸው ይገባል። የ"ላንዳፍታ" መጽሔት ይህንኑ አሳሳቢ ጉዳይ በተመለከተ የምንወያይበት አምድ መክፈቷ ጥሩ ነው። ትንሽ ግን ዘግይታችኋል። አሁንም ተስፋ የሚያስቆርጥ ሁኔታ ስላልሆነ መበርታት ያስፈልጋል። አንድ አሁን የተያዘ ፈሊጥ አለ። ስለ አገር ማውራት፤ ስለአንድነት ማንሳት ከፋሺን ውጪ እንደሆነ ተቆጥሮ አሳሳቢ የሆኑ ጉዳዮች ማውራት ሲጀመር "ደግሞ ፖለቲካውን ጀመረ" እየተባለ መቀስቀስ ተጀምሯል። በታታኞች የሚፈልጉትን ዓላማቸውን ለማሳካት የሕዝቦችን መከፋፈል በጣም ይፈልጉታል። በተበታተነ ሕዝብ መሐል ያለ ኃይል ያለው አካል ለመጠናከር አመቺ ሁኔታ ይፈጥርለታል። እና ታዲያ እኛ ይህን እያየን በዘር እየተከፋፈልን የት እንደምንደርስ አይገባኝም። እና እባካችሁ ለበታታኞች መሣሪያ አንሁን በሉልን። ይህንኑ ነው የምለው።

ገዛኸኝ ለማ (ዲ ሲ)

ከአዘጋጁ፤- አቶ ሰለሞን (ከኬንያ)ና አቶ ገዛኸኝ (ከዲ ሲ) ያቀረባችሁት ተመሳሳይ ሃሳብ ነው። በውነቱ ያላችሁት ችግር በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ነው። እኛም ይህንኑ በመመልከት ከዚህኛው እትም ጀምሮ የመተባበርን አስፈላጊነት በመመልከት የምንወያይበት "ትኩረት" የተሰኘ አምድ ከፍተናል። ከዚህ እየገባንበት ካለነው ማጥ የምንወጣው በጋራ በምናደርገው ትግል ነው። ዛሬ ትንሽ አውቀናል በምንለው በውጪ አገር ባለነው ኢትዮጵያውያን ዘንድ የዘረኝነት ስሜት መንሰራፋቱ በጣም ያስገርማል። አቶ ገዛኸኝ እንዳሉት ምናለበት ተከባብሮ ከሚኖረው የአገራችን ሕዝብ ብንማር? ስለዚህም ነው እስቲ በሚለያዩን ነገሮች ላይ ሳይሆን አንድ ነን በምንላቸው ነገሮች ላይ ውይይት ከፍተን እንሰባሰብ የምንለው። "በእንቅርት ላይ . . ." እንደሚባለው በኢኮኖሚ በደቀቀ ሕዝብ መሐል ይህን መረዝ የምንረጭ ሃይሎችስ ምናለ ከሌሎች ብንማር? በመበታተን ማን ዕድገትን አገኘ?

ለላንዳፍታ መጽሔት፤- ሰላምና ጤና እመኝላችኋለሁ። መጽሔታችሁ ብዙ አርክታኛለች። ታዲያ እዚህ ለንደን የምናገኘው በተባራሪ የምትመጣውን ነው። ምነው አከፋፋይ የላችሁም መሰለኝ? ይህች መንፈስን እያደሰች እያዝናናች የምታስተምር መጽሔት ለሁሉ ብትዳረስ? አስቡበት። - ሮማነወርቅ (ለንደን)

ለላንዳፍታ መጽሔት፤- እላህ ይጠብቃችሁ። መጽሔታችሁ የቤተሰብ መጽሔት ከሆነች አይቀር ምናለበት የተጋቡ ሰዎችን፣ የተወለዱ ሕጻናትን፤ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩትን የምትገልጹበት አምድ ቢኖራችሁ? ሳትጐዱ ያገልግሎት ዋጋ መጠየቅ ትችላላችሁ። - አህመድ ከማል (ኒው ዮርክ)

ከአዘጋጁ፤- አቶ አህመድ ጥሩ ሃሳብ ነው። ቀደም ብለን እኛም ጠይቀናል። የላከልን ባለመኖሩ አላወጣንም። አሁንም ለወደፊቱ በሚቀጥለው መመሪያ መሠረት ቢላክልን እናወጣለን።

**ዜና ዕረፍት -**

የሟችን ጉርድ ፎቶ ከአራት መስመር ባልበለጠ አጭር የሕይወት ታሪክ ጋር

የአገልግሎት ዋጋ - $30.00 ብቻ

**ሠርግ -**

የተጋቡትን ሰዎች ፎቶ (አንድ ላይ) ከሶስት መስመር ካለበለጠ ዜና ጋር

የአገልግሎት ዋጋ - $30.00 ብቻ

**ልደት -**

የተወለደውን ሕፃን ፎቶ ከሁለት መስመር ካልበለጠ ዜና ጋር (የአባትና የእናት ስም ተጨምሮ)

የአገልግሎት ዋጋ - $25.00

**ምረቃ -**

ትምህርቱን የጨረሰው/ችው ግለሰብ ፎቶ ከመመረቂያ ልብስ ጋር፣ የተመረቀበትን ትምህርትና ት. ቤት ከሚገልጽ 2 መስመር አጭር ዜና ጋር

የአገልግሎት ዋጋ - $25.00

በአድራሻችን ላኩልን። ለኛ የሚደርስበት ጊዜ፤-

ለSept እትም በ August መጀመሪያ ሳምንት
ለNov እትም በ Oct መጀመሪያ ሳምንት
ለJan እትም በ Dec መጀመሪያ ሳምንት
ለMarch እትም በ Feb መጀመሪያ ሳምንት
ለMay እትም በ April መጀመሪያ ሳምንት
ለJuly እትም በ June መጀመሪያ ሳምንት

ከክፍያው ጋር በአድራሻችን ይላኩልን።

(ፍቶ የሚወጣው በጥቁርና ነጭ ነው። የምትልኩት ባለ ቀለም ሊሆን ይችላል።)

አድራሻችን ፤- Landafta - P.O.Box 49301 - Atlanta, GA 30359

# ልብወለድ

## ውበት

ከመኮንን ገሠሠ

(ሶደሬ 1976 እንደኛ አቆጣጠር)
(ይህ ድርሰት በብዛት ባልተሰራጨው የ"ላንዳፍታ"
1ኛ ዓመት ቁ 1 ላይ የወጣ ነው።)

ቦታው ሞቅ ይበል እንጂ በተተከሉት ዛፎች ሳቢያ ነፋሻ አየር አለ። በአካባቢው ከአሉት እነስተኛ ኮረብታዎች እየተጋጩ የሚመለሰው መለስተኛ አቧራ አዘል ነፋስ ግን ሞቅ ያለ ነው። ለአካባቢው ውበት እንዲሰጡ ሁን ተብለው የተተከሉት አበባዎች ለዓይን ከሚሰጡት እርካታ ሌላ ልዩ መዓዛ አላቸው። በዚህ ማራኪ ቦታ የተለያዩ ደማቅ ልብሶችን ለብሰው የሚዘዋወሩ ሰዎች ደግሞ ሌላ ውበት ፈጥረዋል። የአዋሽ ወንዝ ፀጥ ብሎ በሚጓዝበት በዚህ አካባቢ የዕረፍት ግዜን ማሳለፍ ብልህነት ነው ብሎ ሰው የተቀበለው ይመስላል። ከአዲስ አበባ፣ ከናዝሬት እንዲሁም ከተለያዩ ቦታዎች የመጣው ሕዝብ ስፍር ቁጥር የለውም። ቀኑ እሁድ፤ የግንቦት ልደታ በዋለ በአራተኛ ቀን፣ ሶደሬ።

ዳኛቸው ከመሥሪያ ቤት ጓደኞቹ ከይኼይስና ከአረጋ ጋር እዚሁ ነው። የቱሪዝም ኮሚሽን አውቶቡስ ተከራይተው ነበር ቅዳሜ የመጡት። እጉል ቦታ ከመዋልና በመጠጥ አዕምሮን ከመመረዝ የተሻለ ነው በማለት በወር ወይ በሁለት ወር ወደ ሶደሬ መሄድ ከጀመሩ ከረምረም ብሏል። ቅዳሜ ከተከራዩት ድንኳን አጠገብ መጠነኛ እሳት አንድደው ሙዚቃ እየሰሙ የባጡን የቆጡን ሲያወሩ በጣም አምሽተው ስለ ነበር እሁድ ጥዋት ዳኛቸው ድክም ብሎት ነበር። የዋና ልብሱን ለብሶ ገላውን ከተለቃለቀ በኋላ ፎጣውን ደርቦ ወደ መዋኛው ስፍራ ሄደ። የእሁድ የቱሪዝም አውቶቡሶች ገብተው ኖሮ አካባቢው በሰው ተሞልቷል። ከአነስተኛዋ ቡና ቤት አካባቢ ሆኖ ቁልቁል የመዋኛውን ሥፍራ ለአንዳፍታ ቃኘው። ልጆች ይጫወታሉ፤ ይላፋሉ፤ ይንቦራጨቃሉ፤ ከትልቁ መዋኛ ደግሞ ከወደ ዳር ያለውን ቧንቧ የሙጥኝ ይዘው ሌላውን እየተመለከቱ የሚስቁትን ሲያይ አንድ ዓይነት ደስታ ሰውነቱን ወረረው። በተለይ ከውሃው ዳር ካለው ሣር ቦታ ላይ ፎጣ ወይ አነስተኛ እስፖንጅ ፍራሽ አንጥፈው በዋና ልብስ ብቻ ጋደም ብለው የሚጫወቱትን ወንዶችና ሴቶች ሲያይ ልዩ ነገር ተሰማው። የሚቀጥለው ጊዜ ሲመጣ ከሚያውቃቸው ጉብልየዎች አንዷን ይዞ ለመምጣት አቀደ፤ ምንም አብሯት ረጋ ብሎ የቆየች ልጅ ባትኖረውም። በሚያየው ነገር እየተደነቀ ሃሣብ ውስጥ ገብቶ ሳለ፤ "ምን ጊዜ መጣህ?" አለውና ይኼይስ አባነነው።

"እናንተ ስትርመጠመጡ ምን ላድርግ ታዲያ?"

"ቁርሱን ወደድከው?" አለው ይኼይስ፤

"ባልወደውስ ምን ምርጫ ነበረኝ?"

"ይኸው ነው እንግዲህ ያንተ ነገር"

"ሽንኩርቱን አሳርረኸዋል! አላየህም ትላንት እኔ የሠራሁትን?" አለው ዳኛቸው።

"ዘላለም አንተ የምትሠራው ሁሉ ጥሩ ነው ቢሆንም ጥርግ አድርጋችሁ ነው የበላችሁት፣ ምን ልትል ነው?" አለው ይኼይስ ጧት የቁርስ ዝግጅት ተረኛ ሆኖ የጠበሰላቸውን እንቁላል ጥሩ መሆኑን ለማስተማመን ብሎ።

"ሰው በዛ እዚህ" አለው ዳኛቸው፣

"ልትዋኝ ፈልገህ ነበር እንዴ?"

"ነበር፤ ሰው ሲበዛ ግን ጭንቅ ይለኛል።"

"ለምን ወዲያኛው መዋኛ አትሄድም፣ እዚያ ሰው አይበዛም።"

"እውነት አልክ፤ . . .እናንተ እዚሁ ናችው ወይስ ትመጣላችሁ?" አለ ዳኛቸው ወዲያኛው መዋኛ ለመሄድ ቆርጦ።

"አረጋ ሲመጣ እመጣለሁ" አለው ይኼይስ።

ዳኛቸው ፎጣውን ትከሻው ላይ ጣል አድርጎ ወደ ትንሹ መዋኛ ስፍራ ሄደ። መንገድ ላይ እጅ ለእጅ ተያይዘው ወይ ትከሻ ለትከሻ ተቃቅፈው የሚጓዙትን ወንዶችና ሴቶች ሲያይ በመጠኑም ቢሆን ቅናት ተሰማው። በሚቀጥለው ጊዜ አንዷን ይዞ ለመምጣት ያቀደውን ሀሳብ አጠናከረ። ትንሹ መዋኛ ሥፍራ እንደጠበቀው ሆኖ አገኘው። ብዙ ሰው የለም። ዳር ላይ ቆሞ ለጥቂት ጊዜ ውሃውን በዓይኑ ካማተረ በኋላ ፎጣውን አስቀምጦ ዘሎ ገባ።

ውሃ ዋና ይወዳል። በልጅነቱ ነበር የለመደው። ገና ያኔ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሳለ። አንድ ሁለት ዙር ከዋኘ በኋላ እዳሩ ላይ ደገፍ ብሎ ቆሞ የሚዋኙትን ይመለከት ገባ። ደስ የሚል ትርኢት ነበር። ጥቂት ልጆች ከወደዳር በኩል ባለው ጥልቀት ከሌለው ቦታ ይንቦጫረቃሉ። ግማሹ በጎማ፣ ግማሹ እንዲሁ ባዶውን፣ እንዳንዱ ዓይኑ

ላይ መነፅር መሰል ላስቲክ አድርጎ ሲዋኝ የልጅነት ጊዜው ለአንድ አፍታ ብልጭ አለበት። እንዲህ እንዳሁኑ መች ሆነና ያኔ፤ ራቁቱን ያለ ውስጥ ልብስ ጉሬ ጃልሜዳ ኩሬ የሚዋኘው ትዝ አለው። የልጅነት ትዝታ፤ የማይረሳ፤ የዚያን ጊዜ ጓደኞቹ እነፍስሃስ፤...እነአየለስ ...በተለይ ተንኮለኛው ጋረደውስ፤ ጋሬ ነበር የሚሉት። የዛሬ ሃያ አምስት ዓመት ገደማ። አሁን የት ይሆን ያለው ጋሬ? ፍስሃ እንኳን ዩኒቨርስቲ አብረው ነበሩ። አየለ እዚያው ጉሬ የብዙ ልጆች አባት ሆኗል።

"እኔማ ይኸው ብቸኛ፤ ዓይኔን ባይኔ እንኳ ገና አላየሁም።" አለ በሃሣቡ፣

በልጆቹ ትርኢት ሳቢያ የጥንቱን እያሰላሰለ ሳለ ከሚዋኙበት አካባቢ አንድ ቦታ ላይ ዓይኑ ዓረፈ። ትክ ብሎ ተመለከተ።

ቀላ ብላ ወፈር ያለች፤ ሞላ ያሉት ጉንጮችና በፈገግታ የተሞላ ፊት ያደላት፤ የደስ ደስ ያላት ልጅ ውሃው ውስጥ ዳር ላይ ደገፍ ብላ ቆማለች። በሃያና በሃያ አምስት ዓመታት አካባቢ የምትገኝ ውብ ወጣት። የሚንቦጫረቁትንና በጎማ ምክንያት የሚላፉትን ልጆች እያየች ትስቃለች። ከፊቷ የሚታየው ፈገግታ ውስጣዊ ደስታዋን እንደሚያንፀባርቅ ለመረዳት ዳኛቸው አላስቸገረውም።

"ምን ዓይነት ውብ ናት እባካችሁ" አለ በሆዱ።

ከውሃው ወጣና በሷ እንዲታይ ሆኖ ዘሎ ውሃ ውስጥ ተመልሶ ገባ። ትየው አትየው ያወቀው ነገር የለም። ብቻ ጥሩ የዋና ችሎታ ያለው የሚደነቅበት ቦታ በመሆኑ ዓይኗን ድንገት ብትጥልበት። ውስጥ ለውስጥ ዋኝቶ እሷ ካለችበት አካባቢ እንደደረሰ ከእሷ ጋር ሊተያዩ በሚችልበት ቦታ ዳር ይዞ ቆመ። እሱም እንደሷ ልጆቹን እያየ መሳቅ ጀመረ። ለአንድ አፍታ አየት አደረገችውና ልጆቹን ታይ ገባች። ለምን እንደማትዋኝ ግራ ገባው። ባትችል እንኳ እንደልጆቹ መንቦጫረቅ። ጠጋ አለ ወደሷ። በቀረባት መጠን ውበቷ እየጎላ መጣ።

"በፍፁም፤...ዛሬ አታመልጪያትም..."አለ በሆዱ።

ፈገግታዋ ልዩ ስበት አለው። ሞላ ያሉት ጉንጮቿ ስትስቅ የፈጠረው ጎድጎድ ያለ ነገር የዲምፕልን ዊስኪ ጠርሙስ ትዝ አሰኘው። ይህን ሰውነት፣ ይህን በውበት የተሞላ ልስልስ ገላ በእጁ ሲነካ በሃሣቡ ታየውና ያልጠበቀው ስሜት ሰውነቱን ውርር አደረገው። ገጽታዋ ዕረፍት ስለነሳው ዓይኑን ከሷ ሊነቅል አልቻለም።

"እስቲ ነይ እንዋኝና እንወዳደር፤" አላት ወደሱ የምታይበትን አጋጣሚ ጠብቆ።

"ማንን? እኔን ነው?" አለችው ደስ በሚል ለዛ፤ ሙዚቃ የመሰለ ድምፅ፣

'እዎን፣ ምናለበት?" አላት ዳኛቸው ፈገግ ብሎ፣

"ዋና አልችልማ፣" አለችው ተራዋን እንደመሽኮርመም ፈገግ እንደማለት ብላ፤

'ቀላል እኮ ነው፤" አላት፤ ጠጋ እያለ፤

"ታስለምደኛለህ?"

እውነት አልመሰለውም።

"ምን ቸገረኝ" አላት ተቻኩሎ፣

"ግን እፈራለሁ፤ ውሃ እንዳልጠጣ፤ አደራ እሺ?" አለችውና ሁለት እጆቿን አፏ ጋ አስጠጋች፣ የፈራች መሆኗን ለማስታወቅ፣

"አይዞሽ፣...በይ ብረቱን ያዥ በሁለት እጅሽ፤ ...እና..." ብሎ የጀመረውን ሳይጨርስ ሰውነቷን ሲነካ የተሰማውን ንዝረት ያስታምም ገባ።

"እሺ፣ ከዚያስ" አለችው።

"እና! ..." አለ፤ "አሁን እንግዲህ እግሮችሽን ዘርጊና ፊትሽን ውሃው ላይ ስትደፊው ራሱ ያንሳፍፍሻል።"

እንደተባለችው አደረገች። ድንግርግር ብሏት እንደመስመጥ ስትል ዘላ ያዘችው። ከጎኗ ቆሞ ነበር። ብድግ አድርጎ ሲይዛት ዓይን ለዓይን ተያዩ። እፍር ብላ ለቀቀችው።

"አይዞሽ እንጅ፣ ትንሽ ውሃ እኮ ሳትጠጭ መልመድ አትችይም። አየር ሳብ አድርገሽ አንገትሽን ውሃ ውስጥ አስገቢውና መቆየት ተለማመጂ፤"

ሞከረች፣ ደጋግማ ሞከረች፣ ብረቱን ይዛ እግሮቿን ዘርግታ በሆዷ ተኝታ መንሳፈፍ ደግሞ አስጀመራት። ትንሽ እንደተንሳፈፈች እጆቹ ላይ ተኝታ ብረቱን ለቃ መንሳፈፍ እንድትችል አደረጋት።

ዳኛቸው ጥቂት ቆይቶ እጆቹን ወደውሃው ወረድ ሲያደርግ እንደመስመጥ ስትል ዘላ አንገቱ ላይ ተጠመጠመች። ትንፋሽ አግኝታ ነፍስ እንደዘራች አፈረችና ለቀቀችው። ሳቅ አለች ፊቷ ላይ ያለውን ውሃ ጠርጋ፤ እሱም ሳቅ አለ።

"እውቀህ ነው አይደል?" አለች ትንፋሿን መቆጣጠር እንደቻለች።

ሳቅ አለና በይ አሁን እረፊ" አላት።

"እኔ ፈራሁ፤ መቸም የምለምድ አይመስለኝም" አለችው ዳር ላይ ከጎኑ ቆማ፤

"እንዴ! ምን ማለትሽ ነው? አሁን እኮ ጥሩ ይዘሻል። እኔ ስጀምር መቼ እንደዚህ እንዳንቺ ነበርኩና፤ አሁን አየሽ ከጥቂት ልምምድ በኋላ ራስሽን ችለሽ መለማመድ ትጀምሪያለሽ። ኋላ በቃ የሚችልሽ የለም" አላትና ፈገግ አለ። "ብቻ ደፈር ማለት አለብሽ፣ አትፍሪ"

"ስንት ጊዜ ይፈጅብኝ ይሆን?"

"በአጭር ጊዜ ውስጥ፤ ዛሬ ነው እንዴ የመጣሽው?"

"አይ ሦስት ቀናችን ነው፣ ከወንድሜና ለእህቴ ጋር"

"መቼ ትመለሳላችሁ?"

"ሰኞ ብለናል"

"ጥሩ ነው፣ ዛሬ አለማምድሻለሁ፤ ነገ ራስሽን ችለሽ ትለማመጂያለሽ"

"ዛሬ ነው የምትሄደው?"

"አዎ! ከአዲስ አበባ ነው የመጣሽው?"

"አዎን" አለችውና በእጇ ውሃውን መረጫጨት ጀመረች።

እንደገና ልምምዱን ቀጠሉ። ከቅድሙ የበለጠ መቀራረብ መጣ፤ ዳኛቸውም በመሐል ቀልድ አዘል ጨዋታ እያመጣ ያስቃት ጀመር። ዕረፍት ሲያደርጉ ከውሃው ውስጥ እጅ ለእጅ ተያይዘው ሆነ። ወሬውም ደራ።

"ስምሽ ማነው?" አላት ዳኛቸው ድንገት ዕረፍት ላይ እንዳሉ፣

"ምን ያደርግልሃል?" አለችው ፈገግ ብላ ፊት ፊቱን እያየች፣

ተራውን ሳቅ አለና "እንዴት ምንም አያደርግልኝም?"

"እኮ ምን? በላ፤" አለችው የበለጠ ፈገግ ብላ፣

"ስምሽ ከውበትሽ ጋር መስማማት አለመስማማቱን ለማረጋገጥ" አላት

"ኋላ ግን ቅር እንዳይልህ?" አለችውና አንገቷን ዘንበል አድርጋ ውሃውን በእጇ አፈሰች፣

"ለምንድነው ቅር የምሰኘው?" አላት በመገረም፣

"ስሜ ከውበቴ በልጦ የተገኘ እንደሆን" አለችውና ትንሽ የቅሬታ መልክ አሳየች፣

"በፍፁም! ከዚህ ውበት ጋር ሊስተካከል የሚችል ስም ያለ አይመስለኝም" አላት የቅሬታውን መንስዔ በሃሳቡ እያንሰላሰለ፣

"ይህን ያህል?" አለችውና ከመቅጽበት የቅሬታ ፊቷ በፈገግታ ተሞላ፣

"ለአንቺ የትኛው ይበልጣል?"

"ስሜ ውበት ያለው ይመስለኛል" አለችና አንገቷን ዘንበል አደረገች።

"አይመስለኝም፤ እስቲ የኔን ፍርድ ለመስጠት እንድችል ንገሪኛ፣" አላትና ፈገግ አለ፤ ውሃው ውስጥ እጇን ፈልጎ ጨበጥ አደረገው።

"አራዳ መሆንህ ነው አይደል?"

"አቦ ንገሪኝ"

"የሐረር ልጅ መሰልከኝ"

"በምን አወቅሽ?"

"አቦ ስትል ጊዜ ነዋ"

"ሊቅ ነኝ አትይኝም ታዲያ?"

"ይህችን ትወዳለች ሄለን! ማሽሟጠጥህ ነው?" አለችና ፊቷን ቀና አድርጋ ትክ ብላ አየችው።

"ሄለን ሙች አይደለም"

"ማን ነገረህ ደግሞ ስሜን?"

"አንቺው ራስሽ!"

"መቼ?"

"አሁን"

"ጠንቋይ ሳትሆን አትቀርም፣"

"ይህን ይወዳል ዳኛቸው፤...እንዴት አባክሽ?"

"እንዲሁ!"

"እንዲሁ አልኩህ" ውሃ ረጨችበት።

እሱም ረጨባት፤ ሳብ አደረጋት፤ ውሃ ውስጥ ውድቅ አለች፤ እጇን ወደ ላይ አውጥታ ትከሻውንና አንገቱን ያዘች። አነቀችው። የጠጣችው ውሃ ተፋች። ፊቷን በሌላ እጇ ጠረገችና ትክ ብላ አየችው። እንደማፈር ብላ አንገቷን ደፋ አደረገችና እጇን ከአንገቱ ስታወርድ፣

"ለምን ከውሃው ወጥተን አናርፍም። ኮካ ኮላ እገዛልሻለሁ።" አላትና ፍዝዝ ብሎ አያት።

"እሺ እኔም ደክሞኛል።"

"ሄጄ ካሜራዬን ላምጣ፣ ውጪና ቆይኝ" አላትና ከመቅጽበት ከውሃው ውስጥ ወጥቶ እነ አረጋን ፍለጋ ሄደ።

ይኼይስ ራቅ ብሎ ያየው ኖሮ አጠገቡ ሲደርስ፣

"አይ አጅሬ" አለው።

"እ! እዚህ ነህ እንዴ? አረጋስ?"

"እዚያኛው መዋኛ ሥፍራ ነው፤...እሳቱ! ተቀላጠፍክ አይደል?"

"ደስ አትልም? ቆንጆዬ ናት"

"ብቻዋን ናት ወይስ ከጓደኛዋ ጋር?" አለው ይኼይስ በጉጉት።

"ከዘመዶቿ ጋር መሰለኝ ያለችው፣ እባክህ አታድርቀኝ ቸኩያለሁ፤ ካሜራዬን እፈልጋለሁ" አለው ወደዚያኛው መዋኛ ሥፍራ እየሮጠ።

"እህቷ እንደሷ ቆንጆ ከሆነች እዚህ ነኝ" አለው ይኼይስ ከኋላው፤ ዳኛቸው ይስማው አይስማው ግን አላወቀም።

ካሜራውን ከአረጋ እጅ ወስዶ ሲመለስ ይኼይስ እዚያው ቦታ ቆሞ አገኘው።

"እህቷ ቆንጆ ከሆነች አልኩህኮ፣" አለው ይኼይስ እየሳቀ

"ባክህ ተወኝ፣" አለው ዳኛቸው እየተቻኮለ፣

ከቡና ቤቱ ፊትለፊት ካለ አንድ ዝርግ ወንበር ላይ ቁጭ ብላለች። አያት። ቀጥ ብሎ ቆመ። ደነገጠ። እሷ አይደለችም ብሎ ተጠራጠረ። እሷው ናት። ወደ ሌላ ቦታ ነበር የምታየው። ከአጠገቧ ያለውን ነገር ሲያይ ለማመን ተሳነው። ደረቀ። ዞር ስትል ቆሞ አየችው። እሱም ያያት ነበር።

"እዚህ ነኝ እኮ፤ የት አለ ለስላሳው? ኮካ ኮላ እገዛልሻለሁ አላልከኝም? አለችው በሚማርክ ፈገግታ።

"እ!...አዎ!...እሺ!" አለና ተነስቶ ከቡና ቤቱ ሁለት ኮካኮላ ገዝቶ ተመለሰ። ድንጋጤው ከፊቱ ይታወቅበታል።

"ምን ሆነሃል? ፈዝዘሃል፣"አለችው ኮካ ኮላውን እየተቀበለች፣

"እ! አአይ!...አልፈዘዝኩም፣ ውሃው ይሆናላ?" አላት የግድ ፈገግታ እያሳያት።

"ፈዝዘሃል፤ ውሃው አይደለም፤ ሌላ ነው፣ ገባኝ" አለችው የበለጠ ፈገግ ብላ፤ ቅሬታ የለም ሀዘን የለም፤

"ምኑ ነው የገባሽ?" አላት እንደመደንገጥ ብሎ፣

ፊቷ ላይ ያለው ፈገግታ አሁንም ያው ነው። ፊቷን ከሱ ዞር አድርጋ፤

"እግሬ ነው አይደል" አለች። ምንም ምሬት ምንም ኀዘን ሳይታይባት።

"ምን!" አላት ዳኛቸው የበለጠ ክው ብሎ።

"ቅድም ያደነቅሽውን ውበቴን ቀነሰብህ መሰለኝ፤ ነግሬህ ነበር እኮ"

"እ! አላት የሚለው ቅጥአምባሩ ጠፍቶት፣

"በመኪና አደጋ ነው በልጅነቴ እንዲህ የሆንኩት" ፊቷን መለስ አደረገች፣

"እ!" አላት አሁንም ፍዝዝ ብሎ እያያት፤

"የአዕምሮ ሽባ ግን አልምሰልህ!"

"እ!"

"ምን ማድረግ እችላለሁ?...ከጠላኸኝ ይቅር፣ ተወው" አለች።

የገዛላትን ኮካኮላ ሳትጠጣ አስቀምጣ የመመርኮዣ በትሮቿን አንስታ ትታው ለመሄድ ብድግ ስትል እጁን እጇ ላይ አድርጎ አስቀራት። ■

# የዴብራ ጦስ

(በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ልብ ወለድ)
ከገረሱ

"የዴብራ ጦስ" በተሰኘ ርዕስ የተጻፈው ልብወለድ ረዥም ስለሆነ በተለያዩ ክፍሎች በተከታታይ ይወጣል።

## ክፍል አራት

ካሣሁን የዚያን ዕለት ምሽት ባደረገችለት የስልክ ጥሪ መሠረት ዴብራን ሊያመጣት አለችው ቦታ ድረስ ሲሄድ ያልጠበቀው ነገር አጋጠመው። እንዲመጣ የነገረችው አካባቢ እንኳን በምሽት በቀን እንኳ የሚያስፈራ ነበር። እቦታው እንደደረሰ የአካባቢው ጭር ማለት በጣም አሳሰበው። ወዲያው እንደሄደ አላገኛትም። ቆም ብሎ መጠበቅ ጀመረ። እንዲያው ለምናልባቱ ብሎ ሞተሩን አላጠፋም። ትንሽ እንደቆየ ከኋላው የፖሊስ መኪና የማስጠንቀቂያ መብራቱን ብልጭ ድርግም እያደረገ ቆመ። ካሣሁን ፍርሃት ገባው። ወዲያው ከፖሊሱ መኪና በድምፅ ማጉያ የሚነገር ነገር ሰማ።

"ቀስ ብለህ እጅህን ጭንቅላትህ ላይ አድርገህ ከመኪናህ ውጣ"

ካሣሁን ግራ ገብቶት ቁጭ አለ። እሱን አልመሰለውም። የዚህ ዓይነቱ ነገር ደግሞ አጋጥሞት አያውቅም። የመኪና ታርጋ ቁጥሩ ተጠራና፣

"የመኪናህን የውስጥ መብራት አብርተህ ቀስ ብለህ ጭንቅላትህን በእጆችህ ይዘህ ውጣ፣ ተጠንቀቅ" የሚል ድጋሚ ማስጠንቀቂያ ተሰጠው።

ካሣሁን ተርበተበተ። መብራቱን አበራ። የእጆቹን እንቅስቃሴ ለማየት እንዲመቻቸው መብራቱን አብራ ማለታቸው ስለገባው በጥንቃቄ እጁን በጭንቅላቱ ላይ አድርጎ ከመኪናው እየተንቀጠቀጠ ወጣ።

"ፊትህን ወደኛ እንዳታዞር፣ ከመኪናህ ትንሽ ራቅ ብለህ ጭንቅላትህን እንደያዝክ ቁም፤"

እየተርበተበተ የተባለውን ሁሉ ፈጸመ። መንቀሳቀስ በተለይ እጆችን ከጭንቅላት ማውረድ ማለት የጥይት ናዳ እንደሚያስከትል በፊልም ደጋግሞ አይቷል። ፖሊሶቹ ሽጉጥ እንደደገኑ ቀረቡትና እጆቹን የኋሊት ጠምዝዘው ወደመኪናው ወስደው፣ የመኪና ፊት ላይ በሆዱ አስተኙት። አንደኛው ፖሊስ ኪሱን ልብሱን በሙሉ ፈተሸው። ሌላኛው መኪናውን ከፍቶ ይፈትሽ ጀመር። "ምን አጠፋው? ጥፋቴ ምንድነው?" ብሎ በጭንቀትና በሲቅ ድምጽ ኪሱን እየፈተሸ ያለውን ፖሊስ ጠየቀው። ፖሊሱ መልስም አልሰጠው። ፍተሻውን ቀጠለ። ከአንድ አስር ደቂቃዎች ፍተሻ በኋላ የመንጃ ፈቃዱን ለቦርሳው ውስጥ ያወጣው ፖሊስ፤

"ስምህ እንዴት ነው የሚነበበው?" አለው ጉርነን ባለ ድምፅ።

"ካሣሁን፣" አለ።

"እሺ ከሣን፤ በል እንግዲህ ነገር ሳይመጣ እዚህ ምን ምን እንደምታደርግ ንገረን። ሰፈርህ አይደለም።" አለው ፖሊሱ ጉርነን ባለ ድምጽ።

"ጓደኛዬን ነው የምጠብቀው እሷን ልወስድ መጥቼ ነው"

"የጓደኛህ ስሟ ማነው?"

"ዴብራ" ትባላለች

"ዴብራ ማ"

ካሣሁን አያውቀውም። ዓይኑ ፈጠጠ፤

"አላውቀውም"
"የትኛው ሕንፃ ውስጥ ነው የምትኖረው?"

"እዚህ ጋ ጠብቀኝ ብላ ደውላልኝ ነው፤ የትኛው ሕንፃ እንደምትኖር አላውቅም።"

"ሥራዋ ምንድነው?"

የካሣሁን ዓይን ድጋሚ ፈጠጠ፣

"አላውቀውም።"

"የት ነው የምታውቃት?"

"ቡና ቤት ነው መጀመሪያ ተዋውቄ ያገኘሁዋት"

"አነጋገርህ የተለየ 'አክሰንት' አለው።

"ኢትዮጲያዊ ነኝ።"

"ኢትዮጲያዊ?"

"አዎ ኢትዮጲያዊ"

"ከዚህ በፊት እዚህ ሰፈር መጥተሀ ታውቃለሀ?"

"እንዲሁ አልፌበታለሁ እንጂ መጥቼ አላውቅም።"

ይህ ሁሉ ሲሆን ሌላኛው ፖሊስ መኪና ፍተሻውን ጨርሶ ከአንደኛው ፖሊስ የካሣሁንን መንጃፈቃድ ተቀብሎ ወደ ራሱ መኪና በመሄድ በሬዲዮ ይነጋገር ነበር። እንደጨረሰ መጥቶ ካሣሁንን ትክ ብሎ አየው፣ ከመንጃ ፈቃዱ ፎቶ ጋር በማስተያየት።

"የፖለቲካ ስደተኛ ነሀ? አይደለህም?"

"ነኝ"

"ታዲያ እዚህ ሰፈር ምን ታደርጋለሀ? ስለዚህ ሰፈር ታውቃለሀ?"

"ዴብራ የምትባል ጓደኛ ጠርታኝ ነው የመጣሁት ነው የሚለው" አለው ቀድሞ የፈተሸው ፖሊስ።

ፖሊሶቹ ሁኔታውን ሲያዩት የወንጀለኛ ወይም የጥፋተኛ መልክ አላዩበትም።

"ታዲያ ጓደኛህ የታለች እጠብቅሃለሁ ካለች?" አለው አንደኛው ፖሊስ

"እኔ ምን አውቃለሁ?" አለ ካሣሁን።

"ይኼኔ እያየችን ትሆናለች፤ ወንጀለኛ ካክሆነች እኛ ኖርን አልኖርንም ትመጣ ነበር፤ እስካሁን ካልመጣች ነገር አላት ማለት ነው። "አለ ሌላኛው ፖሊስ "ምን ይመስልሃል አንተ?" አለ ካሣሁንን

"እኔ ምን አውቃለሁ?"

"መኖሪያዋ በትክክል አታውቅ፣ ሙሉ ስሟን እንኳን በቅጡ አታውቅም፤ አንተ ደግሞ ሲያዩህ የበሰልክ አስተዋይ ትመስላለህ፤ እንዴት ዝም ብለህ በደንብ የማታውቀው ሰው ና አለህ ቦታ ትመጣለህ?"

"ጥፋቴ ነው አሁን ገብቶኛል " አለ በማስተዛዘን።

ፖሊሶቹ ትንሽ ከሱ ዘወር ብለው ከተነጋገሩ በኋላ መጡና፤
"አድራሻህንና ስምህን እንይዛለን ከፈለግንህ ትመጣለህ። አሁን ልትሄድ ትችላለህ፣ለወደፊቱ ግን ተጠንቀቅ፣ እንትንህ ወደመራህ ዝም ብለህ አትንጎድ፣ ገባህ?" አለውና ሳቀ አንደኛው።

ሁለተኛው ፖሊስ በተመሳሳይ ፌዝ በተመላበት መንገድ አሾፈበትና ተሳስቀው መኪናቸው ገቡ።

ካሣሁን እውነት አልመሰለውም። መኪናውን አስነስቶ ወደ ሰፈሩ በረረ። መኪናውን እየነዳ ገልመጥ እያለ ያይ ነበር። ፖሊሶቹ ተከትለውት እንደሆን። መንገዱም ላይ ሌላ የፖሊስ መኪና ሲያይ ወይም ሳይረን ሲሰማ እንዲሁ እንደተርበደበደ ቤቱ ደረሰ። በቀጥታ ወደ ፍሪጅ ሄዶ የሚጠጣውን አንድ ቢራ ይዞ ሳሎን ቁጭ አለ። በሃሣብ ባህር ውስጥ ዋኘ።

"ምን ማድረጌ ነው? አለ በሆዱ። "በዚህ ምሽት እሷስ እንደዚያ ያለ ቦታ ና ማለቷ ምን ማለቷ ነው?" ትንሽ በቀዝቃዛው ቢራም ዕርዳታ ነፍሱ መለስ ስትልለት "በደህናዋ ይሆን?" ብሎ ያስብ ገባ "ወንጀለኛ ብትሆን ነው እንጂ ጤነኛ ብትሆን እኛም እያለን ትመጣ ነበር፤" ያለው የፖሊሱ አነጋገር ትዝ አለው።

"ዴብራ ወንጀለኛ ልትሆን አትችልም፤ "አለ በሃሳቡ። "ደግሞ ና ብላኝ እንዴት ትጠፋለች?" ጥርጣሬው እያየለ ሲመጣ "ዴብራን እቤቱ ሊያስገባት ወስኖ የነበረውን ሀሣቡን ለመቀየር ተገደደ። "የፈለገ ገንዘብ ይጠይቀኝ እንጂ እዚያው የSecurity Deposit ገንዘብ መስጠት ይሻለኛል "ብሎ ወሰነ። ፍርሃት ገባው። ዴብራን ፈራት ደግሞ ብቸኝነቱን ለማስታገስ ሥጋዊ ፍላጎቱን ለማርካት ማን አለው?

የዛን ዕለት ዴብራ አልመጣችም። ስልክም አልደወለችም። ካሣሁን በሃሣብ ውስጥ ገብቶ እንቅልፍ የሚባል በዓይኑ ሳይዞር አደረ። ንጋት ላይ እንቅልፍ ትንሽ ሸለብ ሲያደርገው ያ መከረኛ ስልክ ተደውሎ አባነነው። ሁለተኛ ጥሪ ላይ አነሳ። እሷው ናት። ዴብራ።

"አንቺ ማታ ምን ሆነሽ ጠፋሽ?"

"ስትዘገይብኝ ጊዜ ሌላ ጓደኛዬ ጋ በቀጥታ ሄድኩ አለች"

"አልዘገየሁም፣ ዘገየሁ እንዴ? የሆንኩትን ብነግርሽ አታምኚም?" አላት ግራ ገብቶት።

"ምን ሆንክ?" አለችው።

"ፖሊሶች ጠብቀኝ ያልሺው የቆምኩበት ቦታ እኮ ያዙኝ?"

"ይዘውህ ምን አደረጉህ?"

"ፈተሹኝና ሂድ ከዚህ ብለው አባረሩኝ።" የሆነውን ሁሉ ሊነግራት አልፈለገም።

"በል Welcome to America." አለችውና ሳቅ አለች።

"እንዴት?" አላት በመገረም።

"ጥቁር ሆነህ ይህ የተለመደ ነው፤ ማወቅ አለብህ?" አለችው።"በል አሁን የደወልኩልህ ጓደኛዬ ጋ መኖሬን ልነግርህ ነው። ደግሞ ያንን የነገርኩህን ምን አደረስከው?

ዴብራ ነገሩን ከምንም አለመቁጠሯ በጣም አስገረመው።
"እንደነገርኩሽ ጥቂት ቀናት እፈልጋለሁ ለማሰብ፤" አላት።

"እየነገርኩህ ለምን እንዳልገባህ ሰው ትሆናለህ። እኔ እኮ ጊዜ በሚሰጥ ሁኔታ ላይ አይደለሁም"

"ምን መሰለሽ ዴብራ፤ ኋላ ብትመጪና ብንነጋገርሳ?"

"ለምን አሁን አትነግረኝም? እንቢ ካልክ እንደነገርኩህ እናቴ ጋ ሌላ እስቴት መሄዴ ነው።"

"እኔ Security Deposit ልክፈልልሽና ሌላ ቤት ብትከራይ ይሻላል። አየሽ የኔ ቦታ እናቴ ስትመጣ ይጠበናል።"

"ጥሩ ነው ገንዘቡን ማታ አዘጋጅልኝ።"

"ቤት አግኝተሻል እንዴ?"

"አልነገርኩህም እንዴ? አንድ የተነጋገርኩት ቤት አለ። በወር አራት መቶ ዶላር ነው። የአንድ ወር ተቀማጭና የመጀመሪያውን ወር ክፍያ በቅድሚያ አብሬ መስጠት አለብኝ።

ካሣሁን አስቦት የነበረው የአንድ ወር ክፍያ በተቀማጭ ለመስጠት ነበር። አሁን ደግሞ የአንድ ወር ኪራይ በተጨማሪ ማስፈለጉ ከግምቱ ውጭ ሆነ። ለማረጋገጥ ፈለገ፤

"እና ስንት ነው የማዘጋጅልሽ ማለት ነው?"አለ እየፈራ እየተባ።

"ስምንት መቶ ነዋ፤ የዕቃ ማጓጓዣውን እንደምንም ብዬ እፈልጋለሁ እኔ" አለችው።

"ስምንት መቶ ብር?" አለ ካሣሁን ሰለል ባለ በሚያሳዝን ድምፅ

"ምነው?" አለችው ዴብራ የሱ አባባል እንዳስገረማት ዓይነት በመምሰል

"ይህን ያህል ገንዘብ እንኳ ሊኖረኝ አይችልም፤" አላት ፍርጥም ብሎ።

"እንዴት? ታዲያ ምኑን ነው እኔ እከፍልልሻለሁ ያልከኝ?" አለችው።

"ይህን ያህል አልመሰለኝም"

"ታዲያ ስንት መሰለህ?

"የአንድ ወር ኪራይ" አለ ካሣሁን እየፈራ እየተባ።

"የመጀመሪያ ወር ክፍያ በቅድሚያ እንደሚከፈል አጣኸው እንዴ?"

"እሱንማ እኔ መቼ አጣሁ።"

"እና ታዲያስ" አለችው። "እኔ እኮ አንተን ስለወደድኩና ስላመንኩ አብሬህ ልሁን ብዬ ነው እንጂ ያስቸገርኩህ ዝም ብዬ እናቴ ጋ እንዳልኩህ እሄድ ነበር። ምነው የገንዘብ ችግር አለብህ እንዴ?"

ካሣሁን የለኝም ማለት በተለይ ሴት ልጅን ራስን ማዋረድ መስሎ ታየው፤ " No, እንደሱ ማለቴ እኳ አይደለም።" አላት በኩራት።

"ጉሽ የኔ ቆንጆ፤ በል አዘጋጅልኝና ማታ እመጣለሁ። ዛሬ አንተ ጋ ነው የማድረው።"

ያ የፍቅር ጨዋታዋ ውልብ አለበት። ያ አካላቷን፣ ስሜቷን ሳትቆጥብ የምትሆንለት ሁሉ ታየው። አሁን አሁን አሰኘው።

"በስንት ትመጪያለሽ?" አላት። የገንዘቡ ሃሳብ ምናባቱ።

"ምሽት ላይ ወደ 8:00 አካባቢ ጠብቀኝ። በል ባይ" አለችውና ስልኩን ዘጋች።

ካሣሁን ብቻውን ሲሆን ብዙ ብዙ ነገር ያስብና ልክ ድምጿን ሲሰማ እሷ እንዳለችው ይሆናል። የጠየቀችውን እምቢ የማለት አቅም እየተሳነው መሄዱ አልተሰማውም።ትላንት ምሽት የደረሰበትን ብሎም ያን ያህል ገንዘብ እምጣ ማለቷን ሁሉ ከምንም ሳይቆጥር ማታ ስትመጣ የሚያገኘውን ሥጋዊ እርካታ በጉጉት እያሰበ ደስ ደስ እያለው ወደ ሥራው ለመሄድ ተነሳ።

ማታም ሌላ ቆንጆ ማታ እንደሚሆን እያሰላሰለ።

▪ (በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል) ▪

# የባሮ ባንድ

# BAARO

## የገናን በዓል ምክንያት በማድረግ በአትላንታ ከተማ ታላቅ ዝግጅት ያደርጋል

**ከዚጊ ማርሊ ጋር ይጫወት የነበረው የቀድሞው የዳሎል ባንድ አባላት**

**Members of Former Ziggy Marley's Band "DALLOL" will perform in Atlanta**




**የ ባ ሮ ባ ን ድ**

በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቀው ባለ ጎልድ ሪከርድ

ቦታውና ቀኑ በቅርብ ይገለጻል

ከላንዳፍታ ጋር በመተባበር




# ፍቅር፣ ሰላም፣ አንድነትና ተከባብሮ መኖር ! !

በማህበር የመደራጀትን፣ በጋራ ችግርን የመወጣትን ዘዴ፤ በአጠቃላይ የአንድነትን፣ የኅብረትን አስፈላጊነት በመመልከት በዚህ ጉዳይ ላይ ለመወያየት፣ ልምድን ለመካፈል፣ ባጠቃላይ የመደራጀትን አስፈላጊነት ተረድተን ለዚሁ ከፍተኛ ትኩረት እንድንሰጥ በማሰብ ይህን "ትኩረት" የተሰኘ አምድ ከፍተናል።

## የመደራጀት አስፈላጊነት

መቼውም እንደ ጨው ዘር በየሰው አገር ተበታትነን ቀርተናል። ዛሬ በአሜሪካ ግዛቶች ኢትዮጲያውያን የሌሉበት ቦታ የለም ለማለት እንቸገራለን። በዋሽንግተን ዲሲና በኤል ኤ ያለው ኢትዮጲያዊ ብዛት መቼም ለጉድ ነው። አትላንታ፣ ዳላስ፣ ሂውስተን፣ ቺካጐ፣ ሳንፍራንሲስኮ፣ ቦስተን፣ ኒውዮርክ እጅግ ብዙ ኢትዮጲያውያን ይኖራሉ። ባሁኑ ጊዜ በኮሚኒቲ ማህበራት ተደራጅተው የመረዳዳትን ተግባር የሚያከናውኑ በጣም ጥቂት ቦታዎች ናቸው። በአንዳንድ ከተሞች እንኳን ተሰባስበው የመደራጃ ማህበራትን ለማቋቋም ይቅርና ሲተያዩ እየተገለማመጡ የሚተላለፉ ብዙ ናቸው። አንዳንድ ቦታዎች በዘር፣ በሃብት መጠን፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ እና በመሳሰሉት ብቻ በጥቂት በጥቂት ሰዎች ጥቂት ቡድኖች ይፈጠሩና አንዱ ቡድን ሌላውን በጎሪጥ እያየ አንዳንዴም ጭራሽ እንደጠላት እየተያየ ሲኖር ስናይ በጣም ያሳዝናል። እሱ የዚያ ቡድን ፣"አይ እሷ የዚያ ግሩፕ" አባል ናት እየተባለ ሲወራ ስትሰሙ ይገርማችሁዋል። ለረዥም ጊዜ የኖራችሁበት ከተማ ከሆነ እናንተም ሳታውቁት በዚህ የመከፋፈል ስሜትና መዋቅር ውስጥ ስለገባችሁ ላይሰማችሁ ይችላል። ነገር ግን በሥራ ምክንያት ወይ በትምህርት ወደ ሌላ እስቴት ተዛውራችሁ ወገኖቼን ልፈልግ ስትሉ ግን ይህ መከፋፈልና የአንድነት ስሜት መጥፋቱ ጉልቶ ይታያችሁዋል። ይህን መከፋፈል ደግሞ በጣም የሚያጠናክሩ የኢትዮጲያን አንድነት የሚፃረሩ ኃይሎች እንደሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው። አንዳንድ አካባቢ ኮሚኒቲ ማህበራት ኢትዮጲያዊ በሚል ስም እንዳይቋቋም ከፍተኛ ሴራ እየሸረበ እንዳለ የአደባባይ ምስጢር ነው። አንዳንድ ቦታ ስለኮሚኒቲ ማህበር ማውራት እንደ ኋላ ቀርነት ነው የሚታየው፤ እንኳን ማህበር እንመስርት ሊባል ይቅርና።

አንድ አካባቢ የሆነውንና የሰማነውን እንንገራችሁ። አካባቢው ብዙ ኢትዮጲያኖች ያኖራሉ። ጥቂቶቹ ስብሰባ ይሉና የኮሚኒቲ ማህበር ለማቋቋም ይመካከሩና ሃሣቡን ከተነጋገሩበት በኋላ አንድ ስብሰባ ለማድረግ ማስታውቂያ ይበትናሉ። ዓላማችው ከፖለቲካ ፍፁም ነፃ የሆነ ሁሉን ኢትዮጲያዊ አቀፍ የሆነ የመረዳጃ ማህበር ለማቋቋም ነበር። ስለስብሰባው በአካባቢው ባሉ ኢትዮጲያኖች ዘንድ በሰፊው ተወራ። "አሁን ምን ሊያደርጉ ነው ያው አሰባስበው ገንዘብ አዋጡ ብለው ገንዘባችንን ሊበሉ ነው፤" ስብሰባውን የጠሩት የዚህ ፖለቲካ ድርጅት አባሎች ናቸው፤" በማለት ፀረ ስብሰባዊ ቅስቀሳ በሰፊው ተናፈሰ። የዋህ የዋሆቹ በቅስቀሳው ተሸነፉ። አንዳንዶቹ ደግሞ እስቲ የሚሉትን እንስማ በማለት ወደ ስብሰባው ለመሄድ ቆረጡ። አይደርስ የለም የስብሰባው ቀን ደረሰና ስብሰባው ተካሄደ። ከ2,000 በላይ ኢትዮጲያዊ ይኖራል በተባለበት አካባቢ የተገኘው ሰው ከ50 አይበልጥም። በስብሰባው ላይ "ገንዘባችንን ሊበሉ ነው የሚሰበስቡን" ብለው ሲቀሰቅሱ የነበሩ ሰዎች በብዛት መገኘታቸው ስብሰባውን የጠሩትን ሰዎች ይገርማቸዋል። የተገኘው ሰው ቁጥር ቢያሳዝናቸውም ባለው ለመጀመር ቆርጠው የስብሰባውን ዓላማ በሰፊው በማተት አስረዱ። ጥያቄዎች ተዥጎደጎዱ። አብዛኞቹ አፍራሽ ጥያቄዎች ነበሩ። አንዳንዶቹ አስተያየቶች የዚህ ዓይነት ማህበር መቋቋም ኋላቀርነትን ያንጸባርቃል የሚሉ ነበሩ። ከሁሉ የሚገርመው ከአስተያየት ሰጪዎቹ አንዱ ውጪ "እኔ ኢትዮጲያዊ አይደለሁም፣" እያለ የሚያወራ ግለሰብ እንደ ነበረ ለማወቅ ተችሏል። ነገሩ በቅድሚያ የተወጠነ ነገር ሆነና ሰብሳቢዎቹን ተስፋ የሚያስቆርጥ ሁኔታ ተፈጠሮ ዕቅዱ ውጤት አልባ ሆነ። ማህበሩም ሳይቋቋም ቀረ።

የኢትዮጲያኖችን በአንድ መሰባሰብ የማይፈልጉ ኃይሎች የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ማህበራት እንዳይቋቋሙ ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ እንዳለ ግልጽ ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን ዛሬ ስለ አገር እንኳ ማውራት ነውር እንደሆነ በመናገር "የምን ፖለቲካ፣ የምን አገር፣ አርፈን ሥራችንን እንሥራ" በሚል ቅስቀሳ አዕምሮአችንን እየተሰለበ እንዳለ ማወቅ አለብን። ስለ አገር ማውራት ስለ

ባህል ማውራት ስለ ማህበር ማውራት ከፋሺን ውጪ የሆነ ፖለቲካ እንደሆነ በመለፈፍ የጸረ ድርጅትና የጸረ አንድነት መርዝ በመረጨት ላይ እንዳለ ተረድተን ለዚህ ቅስቀሳ ሰለባ እንዳንሆን እንሁን። በመጀመሪያ ነገር የአሜሪካ መንግሥት ሕግ የዚህ አይነት ማህበራት "ለትርፍ ያልሆነ -Not for profit" በሚል መልክ መቋቋማቸውን በጣም ከመደገፉ ሌላ በመዋጮም ሆነ በዝግጅት የሚያገኛቸውን ገቢዎች ከታክስ ነፃ ያደርጋል። ሰዎችን የመርዳት ተግባሩን በዕቅድና በንጽሕና የሚሠራ ማህበር መሆኑ ከታወቀ የገንዘብም ሆነ የቁሳቁስ፣ የሰው ኃይልም ዕርዳታ የሚሰጡ በጐ አድራጊ ድርጅቶች (Foundations) እንዳሉም ማወቁ በጣም ይረዳል። የሚቋቋሙ ማህበራት በሚኖርበት እስቴት ለትርፍ ያልሆነ(Not for profit) ድርጅትነት ሕጋዊ እንዲሆኑ ማድረግ እነኚህን ጥቀቅሞች ለማግኘት ይረዳል።

## የማህበራት ጠቃሚነት

በኮሚኒቲ መልክ የሚቋቋሙ ማህበራት ለግልም ሆነ ለጋራ የሚሰጡት ጥቅም ብዙ ነው። ጥቅሞች ይሰጣሉ ከሚባሉ ተግባራት ጥቂቶቹን እንዘረዝራለን።

1. መዋለ ሕፃናትን መቋቋም
2. አዲስ ለሚመጡ ኢትዮጲያኖች አገሩን የማላመድ (adaptation) ፕሮግራም ማካሄድ
3. የሥራ ማግኛትን ዘዴ ማሳየት፤ (Job Counciling)
4. ስለ ጤና፣ ንብረት አመሠራረት፣ ንግድ ማቋቋም፣ ወዘተ...ሴሚናሮችን ማዘጋጀት
5. ባህላዊ የሆኑ የመዝናኛና የማህበራዊ ግኑኝነቶችን ዝግጅቶች ማቀነባበር
6. በኢትዮጲያዊያን ላይ የሚደርስባቸውን ጥቃት ወይም በደል (በግልም ሆነ በጅምላ) ማጋለጥ፣ በተደራጀ ኃይል ተቃውሞ ማሰማት
7. የሕግ ምክር መስጠት
8. የኢሚግሬሺን ጉዳይ ምክር መለገስ
9. ከአገርቤት ልጆቻቸውን ለማየት የሚመጡ ቤተሰቦች በተለይ ዕድሜያቸው ገፋ ያሉ አባትና እናቶች፣ ወይም በዕድሜ ብዛት ጡረታ የወጡ ኢትዮጲያኖች ልጆቻቸው ወደ ሥራ ሲሄዱ ቤት ተዘግቶባቸው ከሚውሉ ተገናኝተው አብረው የሚውሉባቸው ፕርግራሞችን መፍጠር
10. የኢትዮጲያውያንን የባህል ማዕከል (Cultural Center) መመሥረት
11. በየቦታው በስደት ያሉትን ኢትዮጲያኖች መርዳት ማጽናናት
12. በኀዘን ጊዜ ማስተዛዘን፤ በሞት ጊዜ የቀብርን ሥርዓት ማስፈፀም፤ በሕመም ጊዜ ማጽናናት፣ ማስታመም
13. በደስታ (ሰርግ፣ ልደት፣ ሹመት ) ጊዜ የደስታ ተካፋይ መሆን።
14. በአገር ቤት ለሚደርሱ ችግሮች እርዳታን በጋራ የማስተባበር ዘዴ መቀየስ፤ ወዘተ...

እነኚህን ገለጽን እንጂ ሌሎችም ብዙ አሉ። ከላይ የተጠቀሱት ዝርዝር የማህበራት አገልግሎቶችን በከፊልም ሆነ በሙሉ ዓላማ በማድረግ ማህበራትን ማቋቋም ይቻላል። ሆኖም ከልክ ያለፈ ዓላማ (over ambitious የሆነ) ይዞ አለመነሳት። አቅም በሚችለው መጀመር ብልህነት ነው። ከላይ ከተጠቀሱት አንዱን ወይም ሁለቱን ዓላማ ብቻ ይዞ መጀመርና ቀስ በቀስ እድገቱ እየታየ ዓላማና ተግባራትን ማስፋፋት የሚመከር ይሆናል።

## የገቢ ምንጮች

1. የአባላት ወራዊ መዋጮ፤ አነስተኛ ወራዊ መዋጮ ከ$5.00 ያልበለጠ ከአባላት መጠየቅ፣ ወጪውን በሥርዓት አድርጐ የወጣበትን ምክንያት ለአባላት መግለጽ።

2. የምሽት መዝናኛ ፕሮግራሞች፣ የባህል ምሽቶች በበዓላትና በሌሎችም ጊዜ ማዘጋጀት።

3. ድርጅቶችንና ግለሰቦችን ዕርዳታ መጠየቅ፤ ዓላማና ዕቅድን በደንብ አስታውቆ ዕርዳታ መጠየቅ፣ በዕርዳታ የሚገኘውን ገንዘብ በአግባቡ መዋሉን ለበጐ አድራጊዎች መግለጽ።

4.በዕቅድ የተያዘ የሥራ ፕሮግራም መንደፍና ይህንንም ዕቅድና ፕሮግራም የዕቅድ ማስታወቂያና ገንዘብ መጠየቂያ (proposal) አዘጋጅቶ የFunding organization መጠየቅ፤- በጣም ብዙ ድርጅቶች አሉ ሊረዱ የሚችሉ። ነገር ግን proposalን በሥርዓት ማዘጋጀት፤ ዕቅዱ ሊሠራ የሚችል መሆኑን በሚያሳምን መንገድ ማቅረብ፤

## የጊዜና ሰው ኃይል ችግር

የዚህ ዓይነቱን ድርጅት በጥሩ ሁኔታ ለማካሄድ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴውን የሚከታተሉናየሚፈጽሙ ግለሰቦች እጥረት ያጋጥማል። በዚህ አገር ያሉት ኢትዮጲያውያን ለዕለት ተዕለት ኑሮ መወጫ መሥራት ስላለባቸው ለዚህ ተግባር ጊዜ ላይኖራቸው ይችላል። እስቲ እንዲህ እናስበው። 15 የቦርድ አባላት ሆነው የሚመረጡ ሰዎች በሳምንት እያንዳንዳቸው 3 ሰዓት በተለያየ ጊዜ ለዚህ ሥራ መዋጮ ቢያደርጉ በሳምንት 45 ሰዓት በወር 1350 ሰዓት በጣም ብዙ ስራዎች ሊሠራባቸው ይችላል። ዋናው ነገር ሃሳበ ፅኑነት፣ ቅንነትና በዕቅድ መስራትን ይጠይቃል። በተጨማሪ ከቦርድ አባላት ሌላ በጎ ፈቃደኞች ይኖራሉ። ይህ እንግዲህ ማህበሩ በገንዘብ ተጠናክሮ፣ ቢሮ አበጅቶ ሠራተኞችን በደሞዝ እስኪቀጥር ድረስ ብቻ ነው።

በየዩኒቨርሲቲው በበጐ ፈቃደኝነት ሊሠሩ
የሚፈልጉአሜሪካውያን ተማሪዎች እናዳሉም እወቁ።

## የሚገጥሙ ችግሮችና መፍትሔዎች

1. ለሀሜትና ለአፍራሽ ቅስቀሳዎች (Negative Propaganda) አለመበገር፤ አፍራሽ ቅስቅሳዎችን ለመቋቋም የተከናወኑ ተግባራትን፣ በዕቅድ ያሉትን፤ በተለይ ለሀሜት ምክንያት የሚሆነውን ገንዘብ ገቢና ወጪውን ሪፖርት የሚገልጹ እነስተኛ ቡሌቲን ቢቻል በወር፣ ካልሆነም በየሦስት ወሩ ማዘጋጀትና ለአባላት ማሳወቅ፤

2. በሰው ኃይል እጥረት የሚደርሱ ችግሮችን ሥራን ተከፋፍሎ በመሥራት፤ በጐ ፈቃደኞችን (volunteers) መጠየቅ፤

3. በመጀመሪያ ላይ የአባላት ቁጥር በጣም ሊያንስ ይችላል። ግዴለም በአለው ይጀመርና እንቅስቃሴ ማስፋፋት፤ በየጊዜው ማስታወቂያዎችን መበተን፣ የማህበራዊ ምሽቶችን ማዘጋጀት በእነኚህ ዥግጅቶች ላይ አባልነትን መጠየቅ። አፍራሽ ተልዕኮ ያላቸው ግለሰቦች በመግባት ማህበሩ ሊያበጣብጡ ስለሚችሉ በተቻለ መጠን ቁልፍ የሆኑ ቦታዎችና ሥራዎችን እንዳይዙ ጥንቃቄ ማድረግ።

## 2 ጠቃሚ ምክሮች

1. ዓላማውን በተግባር ለመተርጎም የተነሳሳችሁ ወገኖች በተቻለ መጠን ትዕግስተኛ መሆን፤ አሉባልታና ሀሜትን መቻል፤ ጥሩ የሕዝብ ግንኙነት (PR) ሥራዎችን ማከናወን የሚችሉ ሰዎችን በመጀመሪያ መቅረብ፤

2. ይህን ለማከናወን በመጀመሪያ የጊዜና የገንዘብ መስዋዕትነት እንደሚጠይቅ ማወቅና በተቻለ መጠን ችግር ሲገጥም ተስፋ አለመቁረጥ፤

የማህበር ማቋቋምን ልምድ ካላቸውና በጥሩ ሁኔታ ከተደራጁባቸው አካባቢዎች፣ ከልምድም በመነሳት የማህበርን አስፈላጊነት ለመጠቆምና ማህበር በሚቋቋምበት ጊዜ መደረግ ስለሚገባቸው አንዳንድ ነገሮች ለመጠቆም በማለት ይህን አቅርበናል። ከዚህ የተሻለ ዘዴ የለም ብለን ደፍረን አንናገርም። የተሻለ መንገድም ሊኖር ይችላል። ዋናው ነገር መሰባሰብ ነው። ከተሰባሰብን ደግሞ ብዙ ችግሮችን በጋራ ልንቋቋም እንችላለን። ግለኝነት አያጥቃን። የጋራ ችግሮች ሞልተውናል። እኛም እንደ ሰው ይመርብን እንጂ።

**እንደራጅ! እንሰባሰብ! እንረዳዳ! እንደጋገፍ!**

**ለእኛ አለኛ ማን አለንና ?**

## ከላንዳፍታ መጽሔት ዝግጅት ክፍል

የኢትዮጵያውያን ማህበራትን በየቦታው መቋቋም ሙሉ በሙሉ የምንደግፍ መሆናችንን እየገለጽን ባልተቋቋሙበት ቦታዎች እንዲቋቋሙ፤ በተቋቋሙባቸው ቦታዎች እንዲጠናከሩ የበኩላችንን ጥረት እናደርጋለን። ስለዚህም፤

1. ይህ አምድ ለዚሁ ተግባር የተከፈተ ስለሆነ ልምድ ለመቀያየር፤ ምክር ለመለጋገስ፣ ሃሳብ ለመለዋወጥ የሚውል መሆኑን እንገልጻለን።

2. አዲስ ማህበራት ለማቋቋም ጥረት የሚያደርጉ በጐ ፈቃደኞችን በማገዝ በአካባቢያቸው ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን የሚበተን ፍላየር (ከአንድ ገጽ ያልበለጠ) በነጻ እናዘጋጃለን። የዚህ ዓይነት ፍላየር እንዲዘጋጅላችሁ የምትፈልጉ በማስታወቂያ የምታወጡትን ቃላት በማዘጋጀት፣ ፍላየሩ ምን መልክ እንደሚይዝ አስረድታችሁ በአድራሻችን ላኩና በስልክም አነጋግሩን። እኛ በአካባቢያችሁ ሊባዛ የሚችል ማስታወቂያ በአማርኛና በእንግሊዝኛ በሚያምር ግራፊክስ አስውበን ሠርተን እንድ ኦርጅናል እንልክላችኋለን። ይህን የምናደርገው በመረዳጃ መልክ ለሚቋቋሙ ማህበራት ብቻ ይሆናል።

3. የማህበራትን እንቅስቃሴ በፎቶግራፍ በማስደገፍ በመጽሔታችን ላይ እናወጣለን።

**የኢትዮጵያውያን ማህበራት እንዲያብቡ**

**ኢትዮጵያዊ የሆን ሁሉ የበኩላችንን**

**አስተዋጽዖ እናበርክት !**

ማንኛውም በኢትዮጵያ ስም የተቋቋሙ ማህበራት በአካባቢያቸው ራሳቸው ወስደው ከሚሸጡት የ"ላንዳፍታ" መጽሔት 25% (25 በመቶ)፣ ከአንድ መጽሔት ሽያጭ 0.60 ሣንቲም ለማህበሩ ማጠናከሪያ እንሠጣለን። "ላንዳፍታ"ን በመሸጥ ለማህበሩ ገቢ ለማስገኘት ስትፈልጉ በደብዳቤ ግለጹልንና ወዲያውኑ እንልክላችኋለን።


አድራሻችን
LANDAFTA
P.O.BOX 49301
Atlanta, GA 30359
ስልክ (404)728-9122
ምሽት ላይ ደውሉልን

# ከሌሎች ልምድ ብንማርስ?

ከአንሞኝ (አትላንታ)

"Let us not learn the hard way" ይላሉ ፈረንጆች። በቀላሉ ከሌላው ልምድ ልንማር ስንችል የምን ሞኝነት ነው። መሰሎቻችን በደረሰባቸው የኑሮ ስቃይ መፍትሄ ብለው ከያዙት መንገድ መማር መቻል ሲኖርብን የግድ እነሱ ባለፉት ሲቃይ ውስጥ ገብተን መውጣት አለብን የምንል ከሆነ ሞኞች ያስብለናል። እነሱ እኮ ሞክረው ሞክረው ከጥቅሙ ጥፋቱ ስላየለባቸው ነው ለየት ያለ መንገድ የመረጡት። ይህን ለማለት ያስናኘኝ ምክንያት ቢኖረኝ ነው። አንድ ወቅት በሀብት የሌለውና ያለው (በዝባዥና ተበዝባዥ) በሚል አስራ ሰባት ዓመት ተከፋፍሎና ተደናቁሮ የቆየው ወገናችን በአገር ውስጥም በውጪ ያለ ዛሬ ደግሞ በዘርና በጐሣ የጐሪጥ እየተያየ፣ እየተኮራረፈ ጭራሹኑ ይባስ ብሎ እንደከፋኛ ጠላት ተያይቶ መጠፋፋትም ጀምሯል። ሥልጣኔ እየገፋ በሄደበት በአሁኑ ወቅት እኛ የታሪክን ፈረስ ወደ ኋላ እየጐተትን መሆናችን ለምን እንደማይሰማን ሲገርመን ይኖራል።

በታደሉት ቦታዎች (የታደሉት ልበል እንጂ) በጐሣዎች በተለያዩ ዘሮች መካከል ይደረግ የነበረው ግጭት እየጠፋ በምትኩ ስምምነትና መቻቻል እየተፈጠረ ትኩረት ወደ ኢኮኖሚና ባህል ዕድገት እየተደረገ እያለ እኛን ቁልቁል የሚመልሰን ነገር ለምን መምረጥ እንደተገደድን ሳስበው ያቅለሸልሸኛል። መቼም በየጊዜው ከሚፈጠሩት የፖለቲካ መሪዎቻችን ለዚህ መፍትሔ አላገኘንም። የሚብስ የሚብሰው ነው እየመጣ ያለው። እኛ ታዲያ አዲስ የፖለቲካ ኃይል በመጣ ቁጥር እየተበጣበጥን፤ እርስ በርሳችን እየተደነቋቆልን እስተመቼ እንደምንኖር ይገርመኛል።

እስቲ አሜሪካን አገር የነበረውን ሁኔታ ለአፍታ ቃኘት እናድርገው። ከአህጉራችን በባርነት እየተገዙ ወደዚህ አገር የመጡት ጥቁር አፍሪካዊ ወገኖቻችን ያለፉበትን ስቃይ፣ የደረሰባቸውን መከራ፤ ከመከራም ለመላቀቅ በየጊዜው የወሰዷቸው የተለያዩ እርምጃ ሙከራዎች በኋላም እንደነ ማርቲን ሉተር ኪንግ የመሳሰሉት ታላላቅ መሪዎችና አስተማሪዎች "መፍትሔ የምናገኘው በዚህ ነው" ብለው የቀየሱትን የሰላም፣ የአብሮ በፍቅር መኖርና መታገል ዘዴ፤ አሁንም የተደረሰበትን ውጤት እንመርምር።

ወንድሞቻችን የሆኑት ጥቁር አሜሪካኖች በዘረኛ ነጮች ይደረሰባቸው የነበረው ስቃይ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ዛሬ በርግጥ አሜሪካ ለጥቁር ዜጐቿ ገነት ሆናለች የምንልበት አፍ ባይኖረንም በ1930 40 ና 50ዎቹ ውስጥ ከነበራቸው መከራ በትግላቸው እየተላቀቁ በመምጣት የተሻለ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ እናያለን። የዛሬ 35 ዓመት ጥቁር አሜሪካውያን እንኳን በመንግሥት ወንበር ተወካዮቻቸውን ሊመርጡ ይቅርና እንዳይገኙ የሚከለከሉባቸው ቦታዎች ብዙ ነበሩ። ዛሬ በኮንግሬስና በሴኔት ጥቁሮች ተመርጠው ይሠራሉ። ይህን የተሻለ ሁኔታ ለማግኘት የጥቁሮች መብት ተገፎልና ተገንጥለን የራሳችንን መንግሥት እንመሥርት ብለው ወይም የራሳችን ግዛታዊ ክልል ነው በማለት ከልለው ከሌላው በመለየት አይደለም። ጠመንጃ በማንሳት አይደለም። ወይም ደግሞ ጠቅላላ የነጭ ዘርን ሁሉ በመኮነን ነጭ ባዩ ቁጥር "ዓይንህ ላፈር" በማለት አይደለም። በሰላማዊ መንገድ ባሉት መድረኮች ሁሉ በመሪዎቻቸውና በተወካዮቻቸው አማካይነት በመወያየትና በመታገል ነው። ዘረኝነትን በመዋጋት እንጂ በማስፋፋት አይደለም።

ይህን በማነሳበት ወቅት በጥቁር አሜሪካኖች የዘመናት ትግል ሰፊ ጥናት አድርጌ ሳይሆን እዚህ አብሬ በመኖር ከነሱ በሰማሁትና በተማርኩት ነው ይህንን የምለው። ጉበዝ እኛን ምን ነካን። አገር ቤት ያለው ወገናችን የመከፋፈያ መርዝ ተረጭቶበት "በዘርህ ካልተሰለፍክ ሥራ የለህም፣ መብት የለህም፤" እየተባለ በመሣሪያ ኃይል ቢገደድም አሻፈረኝ በማለት ተከባብሮና ተዋህዶ ለዚህ መሠሪ ተንኮል መሣሪያ አልሆንም እያለ አውቀናል የምንለው በውጭ አገር በስደትም በተለያየ መልኩ ያለን ኢትዮጵያውያን ምን አስገዳጅ ሁኔታ ተፈጥሮብን ለዚህ ኋለቀር አስተሳሰብ ራሳችንን እንደምንገፋፋ የሚያስገርም ነው።

አንድ የመሆንን፣ ኤኮኖሚ የማሳደግን በጠቅላላ የትብብርን አቅጣጫ ያስይዙናል ብለን የምንተማመንባቸው አንዳንድ ምሁራን የመለያየትን፣ የዘረኝነትን፣ የጠባብ ስሜትን በ"ላይብራሪ ጥናታቸው" ባገኙት "ቲዎሪ" እየበረዙን ስናይ ደግሞ መኩሪያችን ሳይሆኑ ማፈሪያችን መሆናቸውን መገንዘብ አለብን። የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪክ እንደየፈለጉት በራርዘው እያቀረቡ ውንብድብዳችንን ሲያወጡት የነሱ ጭራ ሆነን እኛ መከፋፋላችን ልክ አይዳላም እላላሁ።

የኢትዮጵያን ሕዝብ በአብዛኛው የሚወክለውን የኦሮሞ ሕዝብ ታሪክህ ይህ ነው እያሉ የሚያወናብዱት፤ የግዕዝ ፊደል የአበሻ ኮሎኒያሊስቶች ፊደል ስለሆነ የላቲኑ (ኮሎኒያልስት ያልሆኑት እንግሊዞች) ፊደል ነው ለኦሮሚኛ የሚስማማው ብለው የሚያስተምሩን ጥቁሮች በብዛት በሚማሩበት ዩኒቨርሲቲ የሚያስተምሩት ዶክተር መሐመድ ገርመውን ሳይጨርሱ ጎጃሜዎች ኢትዮጵያዊ አይደሉም የሚሉ ሌላ ማፈሪያ ዶክተር ሙሴ ብቅ ማለታቸው ያስቀናል። ምነው ይህን ሕዝብ ናቁት።

የተማረ ሰው ኃይል ያጥረናል ስንል "እንደሱ ከሆነ የምንለውን ሁሉ ተቀበሉን ልክ ነንና" ማለታቸው ይሆን? በዚህ አጋጣሚ እነኚህንና መሰል ጉሰኛ ምሁራንን እያጋለጡ ቁጭ የሚያደርጉዋቸውን መኩሪያችን የሆኑትን ምሁራንን ሳላወድስ አላልፍም። እነሱማ ባይኖሩ ይኼኔ ብትንትናችን ወጥቶ ነበር።

እንግዲህ ያህን ካልኩ ሌላ የምለው አለኝ። በየአቅጣጫው እየተሴረብን ያለውን ሁኔታ እንረዳ። ከችግራችን ለመላቀቅ መፍትሔው ራሳችን ነንና በየጊዜው እኛን ለመከፋፈል ለሚወጡ ተንኮሎች ሰለባ አንሁን። እኛም ከሌሎች ልምድ በመውሰድ ለመግባባት የሚያስችሉንን ሁኔታዎች እንፍጠር። በሕይወት ዘመኔ ይፈጠራል ብዬ ያላሰብኩት ለዘመናት ሲናቆሩና ሲዋጉ የነበሩት ፍልስጤሞችና እስራኤሎች በውይይት መድረክ ቅራኔዎቻቸውን ፈትተዋል። ትምህርት ይሁነን ይኸ። ከሌላው ልምድ እንማር ስንልም በመወያየት እንፍታው ለማለት ነው።

ለመግባባት መነጋገር፤ ለመነጋገር ደግሞ ፈቃደኝነትና ቅንነት ይጠይቃል። እንግዲህ ለመግባባት ከፈቀድን ብለንም ለመነጋገር ከተስማማን የመግባቢያ ንግግራችንን በምን እንጀምር? በመካከላችን ባሉት ልዩነቶች እንጀምር ወይስ በመካከላችን ባሉት አንድ በሚያደርጉን ነገሮች? እንደኔ እንደኔ አንድ ነን የምንልባቸውን ነገሮች በቅድሚያ አንስተን ብንወያይባቸው የበለጠ መቀራረብን እንፈጥርና የተለያየ አመለካከት ወይም ተቃራኒ አመለካከት የፈጠሩትን ነገሮች በምናነሳ ወቅት መደማመጥን አትርፈን ለመግባቢያ መንገድ እንከፍታለን። የችግራችን መነሻው ይህን ያለማጤን ይመስለኛል። ችግርን ለመወጣት ጠንካራ ማህበራዊ ግንኙነትን ማጠናከር መቻል ይኖርብናል። ማህበራዊ (Social) መሆናችንም ነው ሰው የሚያሰኘን። እንደኔ እንደኔ ማህበራዊ ግኑኝነቶች ጠንካራ በሆኑባቸው ቦታዎች ያሉት ሌሎች ችግሮች ኤኮኖሚያዊም ይሁኑ ፖለቲካዊ ጐልተው አይታዩም። ሲፈጠሩም ሰው ይግባባልና ተመካክሮ ይፈታዋል።

በተቃራኒው የማህበራዊ ኑሮ ነቀርሳዎች የሆኑ እንደ ምቀኝነት፤ ትምክህተኝነት፤ ንቀት፤ ትዕቢት፤ ወዘተ... የመሳሰሉት በተንሰራፉባቸው ቦታዎች ሁሉ ብዙ ችግሮች ይኖራሉ። መግባባት ከሌለ ዕድገት በየት አድርጎ ይመጣል? እንግዲህ ማህበራዊ ግንኙነታችንን እናጠናክር ስንል ተስማምተን፣ ተግባብተን ከኛ ለኛ ተርፈን ለወገን ብሎም ለሰው ልጅ ሁሉ የሚበጁ ነገሮችን ለመፈጸም እንዘጋጅ ማለታችን ነው።


TASTE OF ETHIOPIA

ETHIOPIAN CUSINE

197 Auburn Av.
Atlanta, GA 30303
(404)681-9406

ባህላዊ የኢትዮጵያ
ምግብ ቤት

በንጹህ ጤፍ እንጀራ

ምሳና ራት

ምሳ - ከ$4 እስከ $6 ብቻ

ራት - ከ$4 እስከ $6 ብቻ

(ለልዩ ዝግጅት ዋጋችን ለየት ሊል ይችላል)

የምግባችንን ጣዕም ይወዱታል!

ዋጋችንም ርካሽ ነው!

ብቅ ይበሉ!

LUNCH $4.00 TO $6.00
DINNER $4.00 TO $6.00
*(Special order price may vary from the above.)*
Open 11:00 A.M. to 11:00 P.M. 7 days a week




ውብሸት ገሠሠ



መኩሪያ በቀለ

ከአዲስ አበባ ቤታቸው በ ፲፱፻፸፯
እንደወጡ የጠፉ
ያሉበት ባለመታወቁ ቤተሰቦቻቸው
በትልቅ ጭንቅ ላይ ናቸው።

ስለነሱ የምታውቁ
ለላንዳፍታ አስታውቁልን።

ቤተሰቦቻቸው

# ኑሮ በአሜሪካ

## የሥራ ኢንተርቪው

ከመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል (ካለፈው የቀጠለ)

ባለፈው እትማችን ኢንተርቪው ተደራጊው በቅድሚያ ሊዘጋጅባቸው የሚገባውን መሠረታዊ የኢንተርቪው ጥያቄዎች አቅርበናል። እነኚህ ጥያቄዎች በአብዛኛው የሚጠየቁ መሠረታዊ ናቸው የሚል እምነት አለን። ለእነኚህ ጥያቄዎች ደግሞ የሚሰጡት መልሶች ትክክለኛና ያልተምታታ መሆን አለባቸው። ያልተምታታ ስንል በመስቀለኛ ጥያቄ መልክ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ስላሉ መጠንቀቅ እንደሚያስፈልግ ለማሳሰብ ነው። እስቲ ሁሉንም ባይሆን አንዳንዶቹን ጥያቄዎች እንመልከት፤ መልስ ሊሆኑ የሚችሉትንና የማይችሉትን እንመርምር።

1ኛ. እዚህ ድርጅት ለመቀጠር ምን አነሳሳህ/አነሳሳሽ? – ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ሊሆኑ አይችሉም የምንላቸው፤
ሀ. ሌላ ቦታ ሥራ ስላጣሁ ነው፣
ለ. መሥሪያ ቤታችሁ ከሌሎች መሥሪያ ቤቶች ስለሚበልጥ ነው።
ጥሩ መልስ ይሆናል ብለን የምንገምተው፤ –
ሀ.የመሥሪያ ቤታችሁ (የድርጅታችሁ) ዓላማና ተግባር ከተማርኩት ቶምህርት ጋር የሚስማማ በመሆኑ፤
ለ. ይህ ኢንተርቪው የተደረግሁበት የሥራ ቦታ እኔ ከተማርኩትና ልምድ ካከማቸሁበት ዕውቀትና ችሎታ ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ ስለታየኝ።
ሐ. የድርጅታችሁ ዓላማና ተግባር በትምህርትና በሥራ ልምድ ያከማቸሁትን ዕውቀት የበለጠ የማዳብርበት ቦታ ሆኖ ስለታየኝ።

2ኛ.እንዴት ነው ትምህርትህን መቀጠል ትፈልጋለህ?
ይህን ጥያቄ የሚጠይቁበት ምክንያት አላቸው። ድርጅቱ ራሳቸውን በትምህርት ማሻሻል የሚፈልጉ ሰዎች የሚደግፍ ይሆናል፣ ወይም አይፈልግም ይሆናል፣ ወይም የመደበኛ ሥራውን ጊዜ ይሻማበታል በሚል ፍራቻ ትምህርቴን እቀጥላለሁ የሚለው ሰው ላይፈልጉ ይችላሉ። ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት በቅድሚያ የድርጅቱን አቋም ማጤን ይረዳል። ድርጅቱ ራሱ የማሰልጠኛ ተቋም ይኖረው ይሆናል። ወይም ደግሞ "በሥራ ላይ ስልጠና" 'On the Job Training" ፕሮግራም ይኖረዋል። ድርጅቱ በዚህ የሠራተኞች የሙያ ማሻሻል ላይ ያለውን አቋም ካልተረዱ ይህን ጥያቄ በጥንቃቄ ማስተዋል ያስፈልጋል። አብዛኛው ቀጣሪ ድርጅቶች "መሸጋገርያ ድልድይ' መሆንን አይፈልጉም።3ኛ. ከአንድ ከአምስት ዓመት በኋላ ምን አደርጋለሁ ብለህ አቅደሃል? – ይህ ተጠያቂው በዓላማ፣ በዕቅድ፣ በፕሮግራም የሚመራ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ የሚደረግ ጥያቄ ነው። "እሱን እግዚአብሔር ያውቃል" ብሎ ማለፍ የሚቻል አይመስለኝም።የተምታታ መልስ ላለመስጠት መጠንቀቅ ያሻል። በፍፁም ቀደም ተብሎ ያልታሰበ መልስም መስጠት ያሳፍራል። ሊሆን የማይቻል 'ሕልምም ማውራት ልክ አይደለም። ከሙያ ዕድገት አኳያ፣ ራስን ከማሻሻል አኳያ፣ በጣም Ambitious ያልሆነ ዕቅድ መናገር ያስፈልጋል።

4ኛ. ከሰው ጋር የመግባባት ችሎታህ እንዴት ነው? ከምን ዓይነት ሰዎች ጋር መሥራት የሚያስቸግር ይመስልሃል? – ይህ በጣም ከባድ ጥያቄ ነው። ኢትዮጲያኖች ስንባል "Humble", ፈገግታ የማይለየን፤ ሰውን የማክበርና በትህትና የማናገር ዝንባሌ እንዳለን እናውቃለን። ከምንም ዓይነት ሰው ጋር መሥራትም እንችላለን። ኩሩም ነን። ጥቃትን አንወድም። ይህ ሁለንተናዊ ባህርያችን ይመስለኛል። ታዲያ "እኛ ኢትዮጲያዊያኖች ...እንደዚህ ነን...እንደዚህ አይደለንም "ብሎ ለጥያቄው እንደመልስ ለማቅረብ መሞከር ይጐዳል። "ሌላው ሰው ከእናንተ በምን ይለያል?"የሚል ጥያቄ ሊያስከትል ይችላል። "ከሰው ጋር የመግባባት ችሎታ አለኝ። ሥራን በጋራ መሥራትን (Team work) አምናለሁ። በጋራ ሥራ ለመሥራትና ጥሩ ውጤት ለማምጣት አብሮ ከሚሰሩ ሰራተኞች ጋር መግባባት መቻል ዋነኛ ነገር ነው። ለመግባባት አብሮ የሚሰሩትን ሰው ባህርይ፣ የሚያስከፋውን፣ የሚያስደስተውን ነገር ማጤን ያስፈልጋል። በግል ደረጃ ከሚያስከፋው ነገር መራቅ፣ ከሚያስደስተው ነገር መቅረብ ያስፈልጋል ብዬ አምናለሁ። ይህ ካለ ከምንም ዓይነት ሰው ጋር መሥራት ይቻላል እላለሁ።" ብሎ መመለስ ወይም በተመሳሳዩ መንገድ አዎንታዊ (Positive) አመለካከትን ሊያንፀባርቅ የሚችል መልስ መስጠት።

5ኛ. እኛን የምትጠይቀን ነገር ካለ? – ትዝብት ውስጥ የሚከቱ ጥያቄዎችን፣ የራስን ችሎታ መጥፎ ግምት ላይ የሚጥል ጥያቄዎችን ከማቅረብ መጠንቀቅ። ለዚህም ነው ይህን ጥያቄ በቅድሚያ

አዘጋጅቶ መግባት ይጠቅማል የምንለው። የደሞዝ ጭማሪ ጉዳይ፣ የግለሰብ ዕድገት ጉዳይ፣ በአጠቃላይ ስለራስ የሚደረግ ጥያቄ ግምት ውስጥ ሊከት ይችላል። የድርጅቱን ዓላማና ተግባር በተመለከተ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ሸጋ ናቸው። ይህም ቢሆን ቀደም ብሎ በተደረገ ውይይት ያልተገለፀ ወይም ግልጽ ሆኖ ያልተብራራ ካልሆነ ነው። የተባለን ነገር በድጋሚ እንደአዲስ አድርጎ መጠየቅም "አይሰማም ነበር እንዴ?" ያሰኛል።

**6ኛ. ከሥራህ ውጪ ምን ማድረግ ደስ ይልሃል?**

እውነቱን መናገር ያስፈልጋል። "እስፖርት፣ (ቢቻልም ዓይነቱን)፤ መጽሐፍ ማንበብ፣ (ቢቻል ዓይነቱን)፣ ቲያትር ማየት፣ ሲኒማ ማየት፣...ወዘተ... ከመደበኛ ሥራ ጋር ያልተያያዘ በትርፍ ጊዜ የሚከናወን የመዝናኛ ተግባር ማለት ነው። አንድ ነገር መርሳት የለብንም፤ "በዕረፍት ጊዜ አዕምሮ የሚያዝናና ተግባር መፈጸም ለሚቀጥለው ቀን ሥራ ጥሩ (Fresh) አዕምሮ ይዞ ለመምጣት ያመቻል። " የሚል እምነት አለ። ስለዚህ "እኔ ሥራ እንጂ ዕረፍት አላውቅም" ብሎ የማይሆን መልስ መስጠት አጉል የጀብደኝነትን ባህሪ ማንጸባረቅ ይሆናል። ጠያቂዎቹም እውነተኛ መልስ እንደተሰጣቸው አድርገው ላይቀበሉት ይችላሉ።

**7ኛ.የሕይወት ታሪክን መግለጽ**

አለማንዛዛት። ይህንን ቀደም አድርጐ በሥርዓት ማዘጋጀት። ቅድም ተከተሉን አለማዛነፍ። ጠያቂዎቹ ባህላችንን፣ ታሪካችንን አያውቁም ይሆናልና በተቻለ መጠን ሊገባቸው የሚችለውን ወይም ሊገባቸው በሚችል መንገድ ማቅረብ ያስፈልጋል። የተምታታ ነገር አቅርቦ ቀደም ብሎ ከተነገረ ነገር ጋር ሊጋጭ የሚችል አባባል መሰንዘር ለመስቀለኛ ጥያቄዎች መጋለጥን ያስከትላል።

በአጠቃላይ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ጥንቃቄ የተመላበት መልስ መስጠት በጣም አስፈላጊ ነው። ለጥያቄ የሚሰጡ መልሶች ሌሎች ጥያቄዎችን ወይም ማብራሪያዎችን ሊያነሱ ይችላሉ። አለመደንገጥ።

ኢንተርቪው ሲጀመር ጠያቂው ማለትም ቀጣሪው በትንሽ መግቢያ ይጀምራል። ስለድርጅቱ መጠነኛ ማስታወቂያ ያቀርባል። ከዚያም እንግዲህ ጥያቄውን ይጀምራል። ኢንተርቪው ሲያልቅ ውጤቱ ወዲያው አይነገርም። አዝማሚያው ጥሩ ይሁን አይሁን በተቻለ መጠን በትህትና ፣ በፈገግታ በራስ በመተማመን (በconfidence) መሰናበት ጥሩ ነው።

አንድ የሰማነውና የሆነ ነገር ነው እሱ፣ እንንገራችሁ። ሰውዬው ኢንተርቪው ይጨርሳል። በመጨረሱም በል እንግዲ በቅርብ ቀን ውስጥ ደውልልን እናነጋግርሃለን፣ ውጤቱንም ትሰማለህ? ይለዋል ኢንተቪው አድራጊው።ኢንተርቪው ተደራጊውም ሳቅ ይልና

"You are kidding? You are not calling me? Right?" ይላል። ኢንተርቪው አድራጊው ይደነግጣል።

ይህ እንግዲህ ምን የሚሉት አስተያየት ነው። ፈረንጆቹ attitude የሚሉት ዓይነት ነው። ሰውዬውን ለድጋሚ ኢንተርቪው ለመጥራት ሃሳብ ያለው ከጠያቂዎቹ aንድ እንኳ ቢኖር በዚህ አስተያየት ሃሳቡን ይቀይራል።

ኢንተርቪው አድራጊዎች በችሎታቸው ከተጠያቂው ያነሰ የትምህርት ችሎታ ቢኖራቸው (አንዳንዴ ያጋጥማል) ኢንተርቪው ተደራጊው በመልሶቹም ሆነ በሁኔታው ይህን የችሎታው መብለጥን ሁኔታ ማጋነን የለበትም። አደገኛ ነው። አንዳንድ የከፍል ሀላፊዎች በበታች ሠራተኞቻቸው challenge መደረግን ይፈራሉ። ብዙ ጊዜ በጣም ከፍተኛ የትምህርት ችሎታ ያላቸውን አመልካቾች (ለምሳሌ Ph.D. ያላቸውን) ከሚፈለገው ችሎታ በላይ (over qualified) በማለት የሚሸኙዋቸው ከዚህም ፍራቻ ነው።

የኢንተርቪው አድራጊዎችን ባህሪ ማወቅም ትልቅ አስተዋጽዖ አለው። አንዳንዱ ቶሎ ተናዳጅ ሊሆን ይችላል፤ አንዳንዱ ነገር ቶሎ ላይገባው ይችላል። አንዳንዱ በጣም መከበርን ይፈልጋል፤ አንዳንዱ ተጠራጣሪ ባህርይ ሊኖረው ይችላል። ዋናው ነገር በመጀመሪያ አካባቢ በሚደረጉ የሃሳብ ልውውጦች የጠያቂዎቹን ባህሪ ለመገንዘብ መረዳት ጥሩ ነው። ለሁሉም እንደየባህሪው መልስ ለመስጠት መቻል ጥሩ ዘዴ ነው።

የኢንተርቪው አድራጊዎችን ባህርይ በተመለከተ በሚቀጥለው እትም እንወያያለን።

## ለ አ ን ባ ብ ያ ን

በዚህም ሆነ በተለያዩ ርዕሶች ላይ የዕውቀትና የሥራ ልምዱን ያላችሁ ሃሳባችሁን እንድታካፍሉ እንጋብዛለን። በተለይ በኢሚግሬሽን ጉዳይ ላይ ጥሩ ልምድ ያላችሁ የሕግ ሰዎች እባካችሁ ለወገኖች ምክራችሁን ለግሱ። በዚህ ጉዳይ ብዙ ኢትዮጵያውያን ትልቅ ችግር አለባቸው።

# ተተኪውን ትውልድ በባህላችን ኮትኩተን እናሳድግ የሚያኮራ ባህልና ቋንቋ አለንና!

በስደትም፣ በትምህርትም በተለያየ መልኩ በአሜሪካን ክፍለ ግዛቶች ውስጥ የኢትዮጵያውያን ቁጥር በብዛት እንዳለ በተለያዩ አጋጣሚዎች ገልጸናል። የአገር ቤቱ ሁኔታ ከአሁን አሁን ተሻሽሎ ወደ አገራችን እንመለሳለን የሚሉበት ጊዜ እየተራዘመ በመሄዱ ቤተሰብ መሥርተው በመኖር ላይ ያሉ ብዙ ናቸው። ቤተሰብ ሲመሠረት ከአብራክ የሚፈጠሩ ልጆች ይኖራሉና እነኚህን በውጭ አገር የተወለዱ ኢትዮጵያውያን የመንከባከብና ባህላቸውን ጠብቀው ቋንቋቸውን ለምደው ማንነታቸውን (identity) እንዲያውቁ የማድረግ ሃላፊነት አገራችንን እንወዳለን የምንል ወገኖች ሁሉ ነው። ኢትዮጵያውያን በብዛት (ወደ አምስት ሺ) ይኖራሉ የሚባልበት የአሜሪካን ከተማ አንዱ አትላንታ ነው። በአትላንታ ከተማ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ከአብራኮቻቸው የተፈጠሩት ልጆች ቋንቋቸውን ለምደው በባህላቸው ተኮትኩተው ያለማደጋቸው ያሳሰባቸው ቤተሰቦች ተሰባስበው ልጆቻቸው ቋንቋቸውን ባህላቸውን የሚማሩበት "የኢትዮጵያውያን ወጣቶች በአትልንታ፤ የባህልና የትምህርት ተቋም" የተሰኘ ማዕከል አቋቁመዋል። እኛም ይህን እንደሰማን ትምህርቱ በሚሰጥበት ጊዜ በቦታው ተገኝተን በመመልከት በሥራቸው ኮርተን የተቋሙን የቦርድ ሊቀመንበርና ዋና ጸሐፊ አነጋግረን ያየነውንና የሰማነውን ዘግበን አቅርበንላችኋል።



ሕፃናቱ በክፍል ውስጥ ፊደል ሲማሩ

ቀኑ እሁድ ነበር፤ ከሰዓት በኋላ። በያዝነው ቀጠሮ መሠረት ወደ ክላርክስተን አመራን። እተባልነው ቦታ ማለትም ክላርካስተን ባፕቲስት ቤተክርስትያን እንደደረስንና ትምህርቱ ወደሚሰጥበት ክፍል እየሄድን እያለን ሀ ሁ ሂ . . . የሚል የሕጻናት ድምጽ እየቀረበን መጣ። ለረዥም ዓመታት ያልሰማነው ነገር ነበርና እየተገረምን ከቦታው ደርሰን መምህራኑን አስፈቅደን ስንገባ መንፈሳችን ባገር ቤት ትዝታ ለአፍታ ሸፈተ። በጸጥታ ወደ ኋላ መቀመጫ ሄድንና ቁጭ አልን። አንደኛው መምህር ከአንድ ትልቅ የፊደል ገበታ ላይ ፊደሎቹን እየጠቆሙ ሕጻናቱን ያስተማራሉ። ሌላው መምህር ከወደ ጥግ ባለው ጠረጴዛ ላይ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ያዘጋጃሉ። ተማሪዎቹ በተመስጦ መምህሩ የሚሉትን ይቀበላሉ። የመምህራኑ በስሜት ማስተማር፤ የተማሪዎቹ በተመስጦ መቀበል ስሜታችንን ቆሰቆሰው። የተማሪዎቹ የፊደል ቆጠራ እንደ "ትዝታ" ዘፈን ስሜታችንን አሸፍቶ የመጣንበትን እስከ መርሳት ደርሰን ነበር። ወደ 25 የሚደርሱ ወገኖቻችን የሆኑ በባዕድ አገር የተወለዱ አበባዎቻችን ለባህልና ለአገር ቋንቋ ፍቅር አሳይተው በስሜት ሲከታተሉ ማየትን የመሰለ ምን ደስታ አለና። ከሁሉ የገረመን ሕጻናቱ ፊደል መቁጠር ችለው በየተራ እየተነሱ የፊደል ገበታውን እየጠቆሙ ሲያንበለብሉት ነው።ይህ የሕጻናት የአማርኛ ፊደልና ቋንቋ ትምህርት ዕቅዱ ከወጣ ትንሽ ቀደም ቢልም ትምህርቱ የተጀመረው ወደ አምስት ወር ገደማ መሆኑን ለመረዳት ችለናል። የቦርዱ ሊቀመንበር አቶ አበረ አያናና ዋና ጸሐፊው አቶ አዳምጤ ተችሎ እንደገለጹልን የዚህ ማዕከል ዓላማዎች 1ኛ. በስደትና በመሳሰሉት እዚህ ባሉ ያኢትዮጵያውያን ቤተሰብ የተወለዱት ሕጻናት እንዲተዋወቁ፤ 2ኛ. ቋንቋቸውን እንዲማሩና 3ኛ. ባህላቸውን እንዲያውቁት ማድረግ ሲሆን ወደፊትም ጠቅላላ ወገናችን ከተባበረን ብዙ ዕቅድ አለን ብለውናል።

በመምህራን፣ በመማሪያ መሣሪያ፤ በማስተማሪያ ቦታ፤ በአመራር በኩል ባጠቃላይ እንዴት እንደተሳካላቸው ጠይቀን በሰፊው አስረዱን። "ዓላማ፣ ቅንነት፣ በጐ ፈቃደኛነትና ትብብር ካለ ምን ይቸግራል፤" ነበር የአቶ አበረ የመጀመሪያው መልሳቸው። አጭር መልስ ይምሰል እንጂ በዚህ አባባል ብዙ መልስ ሰጥተውናል። መምህራኑም ሆኑ የቦርዱ አባላት በጐ ፈቃደኞች መሆናቸውን ተረድተናል።

ተቋሙ 16 አባላት ባቀፈ ቦርድ ሲተዳደር የሥራ አስኪያጅ አባላቱ ቁጥር 7 ነው። ትምህርቱ የሚሰጠው ዘወትር እሁድ ለ3 ሰዓት ነው። ቦታውንም የሰጣቸው የክላርክስተን ባፕቲስት ቤተክርስትያን ነው። ዘመናዊ የሆነ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ባይኖሩንም በፈጠራ ሥራ ሙከራ እንዳደረጉ ገልጸውልናል።ለመሆኑ ይህን ለማከናወን ወጪውን እንዴት ቻላችሁት? ብለን ለጠየቅናቸው ጥያቄ ሲመልሱልን "መምህራን በጐ ፈቃደኞች በመሆናቸው ክፍያ አይጠይቁንም፤ ይህ ትልቅ ዕርዳታ ነው።



የቦርዱ አባላት

ከዚህ በተረፈ ለመማሪያ መሣሪያ ዝግጅትና ለሥራ ማስኬጃ ለያንዳንዱ ሕጻን $20.00 ብቻ በወር በመዋጮ መልክ እንጠይቃለን። እኛም በአቅማችን እናዋጣለን። ይኸው ነው።" አሉን። በጣም ገረመን። የመተባበርና የመግባባት ውጤት ምን እንደሚያመጣ ተማርን። በዚህም ላይ በዚህ አገር ባለው የወጣቶች ችግር (ጋንግ፤ ድራግ የመሳሰሉት) በየትምህርት ቤቱ የሚውሉት ልጆቻችን በባህላችውና በቋንቋችውም ጭምር ተኰትኩተው ማደጋቸው ከዚህ ጎጂ ነገር ምን ያህል እንደሚያርቃቸው ለመረዳት አላዳገተንም።

በመጨረሻም ያላቸው መልዕክት እንዳለ ጠይቀናቸው የሚከተለውን ብለውናል።

1ኛ. ይህ ማዕከል ከምንም የፖለቲካ፣ የሃይማኖት ድርጅት ሆነ ማንኛውም ቡድን ነጻ ሆኖ የሚንቀሳቀስ መሆኑን በመረዳት ወላጆች ልጆቻቸውን እንዲያመጡ እንጋብዛለን።

2ኛ. ባለን የጊዜና የአቅም ችግር ትምህርቱ የሚሰጠው በሳምንት 3 ሰዓት ብቻ በመሆኑ ልጆቹ የተማሩትን እንዳይረሱ ቤተሰቦች ቤት ውስጥ ልጆቻቸውን በአማርኛ ቢያናግሩ፣ ጥናታቸው ላይ ቢረዱዋቸው በአጭር ጊዜ ቋንቋውን ለመያዝ እንደሚችሉ እንገልጻለን።



ከክፍልም ውጪ ይበልጥ የሚተዋወቁበት ሽርሽር (picnic) አላቸው።

3ኛ. ሕዝቡ ይተባበረን፤ ቢያንስ ቢያንስ "እይዟችሁ" ይበለን። ይህ ለኛ ትልቅ ድጋፍ ነው። ተባበሩን ነው የምንለው። ቀረብ በሉንና እዩን ነው የምንለው። ጉብኙንና ገምቱን ነው የምንለው። ሌላውን ሕዝቡ ካየን የሚያደርገውን ራሱ ያውቀዋል።

ማንንኛውንም መረጃ ለማግኘት በስልክ ቁጥር (404)758-2529 አቶ አዳምጤን ማነጋገር ይቻላል። የተቋሙ አድራሻ ክላርክስተን አካባቢ ቸርች ከተሰኘው ጉዳና ላይ ካለው የክልርክስተን ባብቲስት ቤተክርስቲያን ነው።

እኛም የምንለው አለን። በመጀመሪያ ያህን ድንቅዬ ተግባር ጀምረው ለዛሬው ብቻ ሳይሆን ለተተኪው ትውልድ ጥሩ ዜጋ የማፍራትን ተግባር የጀመሩትን ቤተሰቦችና ይህን በማስተባበርም ሆነ በማስማሩ ተግባር ላይ የተሰማሩትን ዕንቁ ወገኖቻችንን "ጉሽ፣ አበጃችሁ፤ መኩሪያችን ናችሁ፤ " እንላቸዋለን። ቀጥለንም "ጥሩ ሲሰራ በጥብጭ አይጠፋምና ለእሉባልታ ሳትበገሩ በርቱና ግፉበት።" እንላቸዋለን። ሌሎቻችንም በማቴሪያልም በሞራልም እንደግፋቸው። እኛም ልጆቻችንን እንዲያስተምሩልን እንውሰድላቸው።



የቦርዱ አባላት በስብሰባ ላይ

የላንዳፍታ እትመት ክፍል ለዚህ ታላቅ ዓላማ መሳካት የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማድረግ ቃል እየገባ በግዕዝ ፊደላት እትመት በኩል የሚያስፈልገውን ለማገዝና በዚህ በኩል ነፃ አገልግሎት ለመስጠት ሙሉ በሙሉ ዝግጁ መሆኑን ይገልጻል።


# Addisu Gebeya አዲሱ ገበያ

## We Carry Large Selection Of Ethiopian Foods & Spices

*We have everthing you need to prepare an Ethiopian Feast !*

| DESCRIPTION | QTY(ib) | Price |
|---|---|---|
| 1. Berbere | 1/2 | 3.99 |
| 2. Miten Shiro | 1/2 | 3.50 |
| 3. Aja | 1/2 | 3.50 |
| 4. Mitmita | 1/2 | 3.50 |
| 5. Awaze | 1/2 | 3.99 |
| 6. Butter Maker | 1 | 13.99 |
| 7. Tef | 1 | |
| 8. Mekelesha | 1 | 13.50 |
| 9. Kik | 1 | 0.49 |
| 10. Bakela | 1 | 1.79 |
| 11. Miser | 1 | 0.89 |
| 12. Kinche | 1 | 0.39 |
| 13. Telba | 1 | 1.25 |

NAME ____________
ADDRESS ____________
____________
CITY ____________
STATE ________ ZIP ______
Tel. ( ) ____________

**WE DO MAIL ORDER**

Please Include $5.50 For Shipping And Make Your Check Or Money Order Payable To: Addisu Gebeya

- JEWELRY
- VIDEOS
- CASSETTES
- REKEBOTE (ረከቦት)
- COFFEE
- ETHIOPIAN ARTS
- ETHIOPIAN DRESS AND MUCH MORE

2202 18th St. N.W.,
Washington, DC 20009
202 •986 •6013 / 23

# የሳንባ ነቀርሳ ሁኔታ

## አጭር መግለጫ

ከዶክተር ክንፈ ገበየሁ (ቺካጐ)

በሐገራችን አጠራር ሳንባ ነቀርሳ የሚባለው ቱበርኩሎሲስ (TB) ነው። ነቀርሳ የሚለውን ቃል ለካንሰርም ስለምንጠቀምበት ሁለቱን በግልፅ መለየት ያሻል። ቱበርኩሎሲስ (የሳንባ ነቀርሳ) ለዓይን በማይከሰቱ ጥቃቅን ጀርሞች TB Bacilli በሚባሉና ከበሽተኛው ወደ ሌላው በሳልና በማንጠስ በሚበተነው አከታ ሊዛመትና ሊራባ የሚችል ነው። ሕፃናትን፣ ጐልማሶችን፣ ባልቴትን አዛውንትን ሳይመርጥ ሊደፍር ይችላል። በተለይማ በሲጋራ፤ በመጠጥ፤ በምግብ ጉዳትና በእረፍት እጦት የተጎሳቆለ ሰውነትን ሲያገኝ ደስታው ነው።

በማደግ ላይ ያሉ ሐገሮችና የጤናና የኑሮ ይዞታቸው ያልዳበረ ክፍለ አለማት በብዛት በቱበርኩሎሲስ ይሰቃያሉ። ቱበርኩሎሲስ ሰውነትን አመንምኖ ከመጨረሱም ሌላ የመከንቸር አቅም አለው።ባሁኑ ዘመን ከዳበሩትም አገሮች በተለይ በአሜሪካ ይብልጡኑ በትላልቆቹ ከተማዎች ቱበርኩሎኪስ በመብዛት ላይ እንዳለ ተረድተናል። ይህም የችግረኞችና የቤት አልባ ሰዎችን መብዛት የኑሮ ምስቅልቅልን ይጠቁማል። በAids ሕመም የተጠመዱ ሕሙማን የበሽታ መከላከያ ኃይላቸው ከተዳከመ ብዙ ጊዜ ቱበርኩሎሲስ ይይዛቸዋል።

እንግዲህ ወደ አርዕስቱ መለስ ልበልና የመጽሔቷ አዘጋጅ የጠየቁትን የሳንባ ነቀርሳ የምርመራ ውጤት ለመግለጽ ልሞክር። በጤና ጥበቃ መስክ የሳንባ ነቀርሳ መያዝ አለመያዙን መርምሮ ለማወቅ የመጀመሪያ እርምጃ ማንቱ(Mantou ወይም PPD) ቴስት የምንለው ከመሐል ክንድ ላይ በቀጭን መርፌ ተሰጥቶ ከሁለት እስከ ሦስት ቀናት ውስጥ ውጤቱ የሚጠናው ነው። Positive የምንለው ያ በክንድ ላይ ከቆዳ ስር የተወጋው መድኃኒት በዚያው በተወጋው የአካል ክፍል አካባቢ የቀላና በተለይም ያበጠ ከሆነ ተመርማሪው ከአሁኑ ቀደም በቱበርኩሎሲስ ጀርም ሰውነቱ መደፈሩን ይገልፃል። መርማሪው የእብጠቱን መጠን ለክቶ Positive ወይም Negative ይለዋል።

Positive ነው ማለት ምን ሊሆን ይችላል?

ሀ. የተመርማሪው ሰውነት በቱበርኩሎሲስ በሽታ የተጠመደ ነው ማለት ይሆናል።

ለ. የቱበርኩሎሲስ ጀርም ካሁን ቀደም የተመርማሪውን ሰውነት ደፍሮ ነበር ግን የተመርማሪው የሰውነት መከላከያ ብርታት ጠንካራ በመሆኑ በሽታው ላይዘው ችሏል።

ሐ. ተመርማሪው የቱበርኩሎሲስ መከላከያ ክትባት (የBCG) ካሁን ቀደም ወስዶ ነበር ማለት ሊሆን ይችላል።

ክንዱ ላይ የሚሰጠው የመርፌ ምርመራ ከላይ ከተዘረዘሩት አንዱን ሊሆን ስለሚችል ይህ ውጤት በተገኘ ጊዜ መርማሪው በቃለ መጠየቅና በማየት፣ በመዳሰስ፣ በማዳመጥ፣ በደም ምርመራ ተጨማሪ መረጃዎችን ከመሰብሰቡም ሌላ የራጂ ምርመራ እንዲደረግ ይጠይቃል።የምርመራ ውጤቶቹን በማስተባበር በተለይም በራጂው ውጤት በመመርኰዝ ተመርማሪው በበሽታው መጠመድ አለመጠመዱን ያረጋግጥለታል።

ብዙውን ጊዜ በበሽታው ያለመጠመዱ መግለጪያ ሲገኝ የማንቱው ምርመራ Positive ከሆነ በተለይ ዕድሜያቸው ከ30 ዓመት በታች የሆኑ ጀርሙ ተንሰራርቶ ወደ በሽታ እንዳይለወጥ የመከላከያ መድኃኒት ከ6 እስከ 12 ወራት ያህል እንዲወስዱ ይደረጋል። ይህም መከላከያ (Prophylaxis) ተብሎ የሚነገረው ጠቃሚ ጠንቁን ማውደሚያ ዘዴ ነው።

ባሁኑ ጊዜ የቱበርኩሎሲስ ጠንቅ በተለይም በራጂ ምርመራ የተገኘለት ሰው የኤይደስ (የHIV) የደም ምርመራ እንዲያደርግና የሰውነቱ አያያዝ እንዲታወቅለት ማሳሰቢያ ይሰጠዋል። በማሳሰብያው መጠቀም ለወደፊቱ ለተመርማሪው የሕክምና እቅድ ስለሚረዳ በምክሩ ከመጠቀም ወደኋላ አለማለት ነው።

=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=-=

ዶክተር ክንፈ ለአደረጉት አስተዋጽዖ በአንባብያን ስም ከልብ እያመሰገንን ወደፊትም እንደሚልኩልን እንተማመናለን። ተጨማሪ የጤና አጠባበቅ ምክር አዘል ጽሑፎችን እንድትልኩልን ሌሎችንም የጤና ባለሙያዎችን እንጋብዛለን።

# የኢትዮጵያውያን ጓደኝነት አገልግሎት

## ETHIOPIAN MATCH MAKER SERVICE

Girmay and Foster

**የአገርዎን ልጅ ጓደኛ ያብጁ!**

ሥራ በዝቶቦት ጊዜ በማጣት የተቃራኒ ጾታ ጓደኛ ለማበጀት ችግር አለብዎት?

እስቲ በዚህ እኛ እንቸገርሎትና እንርዳዎት።

ቀላል ነው። እኛ ከአገር ቤትም ሆነ ከዓለም ዙሪያ ካሉ ኢትዮጵያውያን ብዙ ደብዳቤዎችና ፎቶግራፎች ይደርሱናል። እኛ እንግዲህ ጥያቄዎ እንደደረሰን ምርጫዎ ሰፋ እንዲልሎት በማሰብ በአንድ ጊዜ የአምስት ሰው (እንደ ጥያቄዎ ወንድም ሆነ ሴት) ፎቶግራፎችና መተዋወቂያ ደብዳቤ እንልክሎታለን። እርሶ እንግዲህ ከሚስማማዎት ተጻጽፈው ጓደኛዎን ይይዛሉ። "ፈረስ ያደርሳል እንጂ . . ." ይባል የለ!



የአገልግሎት ዋጋችን $75.00 (U.S) ብቻ ነው።

ከኢትዮጵያ ለምትልኩ የአገልግሎት ዋጋ አናስከፍልም።

**Girmay and Foster**
*5300 N. Sheridan Road. #211*
*Chicago, IL 60640*
*Phone - (312)769-2360 Fax - (312)732-5478*

በአገልግሎታችን ይረካሉና ዛሬውኑ በአድራሻችን ይጠይቁን።

# ሞዴት ን Modem


የኢትዮጵያ ቃላት ማተሚያ

Ethiopian Word Processor

በAmi Pro ግዕዝ

ግዕዝ in WordPerfect for Windows ግዕዝ

# ኢትዮጵያ





Ethiopian Computers & Software
9781 W. Fremont Pl.
Littleton, Colorado 80123, USA

Tel: (303) 972-2186
Fax: (303) 973-4342

# « እውነትም ወለም ዘለም!»

ከዘለቀ ንጋቱ

ባለፈው ሰሞን በ"አዕምሮ ኢትዮጲያ" ሰኔ 1985ዓ.ም. በአንደኛ ዓመት ቁጥር 5 እትም ላይ "...ጠጢትም ቆንጆ?" በሚል ርዕስ ከባሻ ወለም ዘለም የቀረበውን ጽሁፍ አንብቤዋለሁ። ጽሁፉ ፍሬከርስኪና ቁም ነገር የጎደለው ስለሆነ አነበብኩት የምለው በጣም እየከበደኝ ነው። ጽሑፉ ከወጣ ከሁለት ወራት በላይ ሆኗል። እኔም በዚህ ጊዜ ውስጥ ባሻዬ የአንባቢን ግንዛቤ አይተው ማረምያ ያወጣሉ ብዬ ነበር። ሆኖም ውጠ ቁልጭ ዓይነት ስለሆኑብኝ ይሄን መልስ ቢገባቸውና ቢረዱት ብዬ ጽፌያለሁ።

ከጸሐፊው ስም (የብዕር ስማቸው መሆኑ ነው መሰለኝ) ጀምሮ የቃላት አመራረጥና የሥነ ጽሑፍ አጣጣላቸው 'አቤት' የሚያሰኝ ነው። ሆኖም የጣሉትንና የጨበጡትን ባለማወቅ በዘፈቀደ አንባቢን አስቃለሁ ብለው ዘመቻ የወጡ ይመስላል። እውነትም 'ወለም ዘለም' በኔ ግምት በዛ ጽሑፋቸው የሣቀ ቢኖር እንደሳቸው ያለ "ጡንቻ ራስ" ካልሆነ በስተቀር ለብዙሀኑ አንባቢ አስደንጋጭ ሳይሆን አልቀረም። በዚህ ነገር ዓዋቂነታቸውና አፃፃፋቸው የአትላንቲክ ውቂያኖስን ወይም መጽሔቱ አውሮፓ ከታተመ የሜዲተራንያን ባህር መሻገር አይገባውም ነበር፤ (እውነት ባሻዬ ያሉት አገር ቤት ከሆነ) እዛው ባሉበት ቦታ የ"አዲስ ዘመንን" የጊዜው ጸሐፊዎችን መቀላቀል ይቀላቸው ነበር። ከነሱ ምንም አይለዩምና። አልፎም ይሄን ወርቅ ጊዜያቸውንና ለፖስታ ያወጡትን ገንዘብ ባዳኑም ነበር እላለሁ። እንደኔ እንደኔ ባሻዬ ያሉት እዚቹ አሜሪካ መሰለኝ። መቼ አገር ቤት ያለ ሰው ሥራ ፈቶ ይህን ወሬ ብሎ ይጽፋል? ስንት የሚጻፍበት ጉዳይ እያለ። ባሻዬ ምነው ከአሜሪካ ነኝ ማለትን ፈሩ?

ጽሑፉ መረን ከመልቀቁ የተነሣ ማንን እንደሚመለከትና ለምን እንደተጻፈ ሊገባኝ አልቻለም። አንዴ ስለኢትዮጲያዊያን ሴቶች የ'ወሲብ ዕቃነት' (Sex Object)፤ አንዴ ኢትዮጲያ ውስጥ ስላለው መንግሥታዊ አስተዳደር፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሳንፍራንሲስኮ ስለተደረገው የቁንጅና ውድድር፤ ሲቦዝባቸው ደግሞ ስለ ኢድሃቅና መድህንም ጭረዋል። በአንድ አጭር ጽሑፍ ይህ ሁሉ የጉድ የሚያሰኝ ነው። እንዴት አንዱ ከሌላው እንደሚያያዝ ግን ያልገባኝ ነገር ነው። ይባስ ብለው ቆዳቸውን ሲያዋድዱ "እንዳትሰድቡኝ" ብለዋል። እራሳቸውን በራሳቸው ስለሰደቡ ሌላ ሰዳቢም ባላስፈለገ ነበረ። ነገር ግን መንገዱን ከከፈቱልን አይቀር የመልስ ምት ቢሰጥዎና ሳይገነዘቡ የቀሩትን ነገሮች ቢማሩ ብዬ ነው። ቢገባዎት።

ያተኮሩት እንደመሰለኝ ቁንጅናው ውድድር ላይ ነው። የጽሑፉም ርዕስ ይሄን ያመለክታል። "ጠጢትም ቆንጆ" ብለው እህቶቻችንን (ምናልባት ለርሶዎ ልጆችዎም ሊሆኑ ይችሉ ይሆናል፤) የወረፉበት ምክንያት ግን ሊገባኝ አልቻለም። አንድ ሦስት መንግሥት ሳይበሉ አልቀሩም መሰለኝ (የአፄ ኃይለ ሥላሤን፣ የደርግንና የወያኔን)፤ ቢያንስ ያለፈው መንግሥት አሥራ ሰባት አመታት የአሁኑ ደግሞ ሁለት አመታት በኢትዮጲያ ሕዝብ ላይ ስለ የግላቸው ሕብረተሰብ ግንዛቤና አወቃቀር የስማ በለው ደወል ሲደውሉበት ጸሐፊው እራሳቸውን ለአሥራ ዘጠኝ አመታት ዋሻ ቀብረው ወደ ድንጋይ ዘመን ማሕበራዊ ኑሮ አመለካከት ነጉደው ካልሆነ በስተቀር የዚህ አይነት አጻጻፍ አሁን ካለንበት ሁኔታ ጋር አለመጣጣሙን በተረዱ ነበር። ሌላ ብዙ አንገብጋቢ ወቅታዊ ሁኔታዎች እያሉ ማለቴ ነው። ነገሩ እንኳን "በደላንም" ጊዜ የዚህ አይነት ጽሑፍ መዋጥ ቀርቶ መጉረስ እንኳ አንችልም ባይ ነኝ። እዚሁ አሜሪካ መሆንዎን መጀመሪያ እንካካድ፤ እንግዲህ እዚህ ኖትና አመለካከቶን ለማረቅና መስመር ለማስያዝ ያደረጉት ሙከራ ያለ አልመሰለኝም። ሴቶች ውበታቸው አካላዊ ቅርጻቸው ላይ ብቻ ሳይሆን ብዙ ነገር ላይ እንደሚያተኩር ማወቅ ብዙ ዕውቀት አይጠይቅም።

ያለሁት አገር ቤት ነው ካሉም እዚያ ተቀምጠ ባህር ማዶ (U.S.) ስላለው የኢትዮጲያ ሕብረተሰብ መተቸት "ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ" አያሰኝም ብለው ነው? እዛው ያሉበት ቦታ እነ አራንሺን ጠበቅ ቢያደርጉ ፍሬ ያለው አይመስሎትም? አለዛ አያስችለኝም ካሉ ደግሞ እንደባልደረባዎ እንደ ዶክተር ሙሴ (በያ ሰሞን ጉጃሞች ኢትዮጵያውያን አይደሉም ብለው ሊያስተምሩን የከጀሉት እበላ ባይ 'ምሁር')፣ ዝባዝንኬዎን "በነፃ ልላክላቸችሁ" ብለው በሽፍንፍን እንዳያዳርሱን አደራ። "የፖለቲካውን ነገር ለነ . . ትቼ አገኛለሁ ብዬ ወደ ሴት ገዳም መንኛለሁ. . ." ብለውናል። አይ ባሻዬ እንዲህ ሲሉ "የአገራችን ሴቶች የአገር ፍቅር ስሜት የላቸውም፤" ማለትዎ እንደሆነ አልገባዎትም ይሆን? ወይስ ሴቶቻችን ከአገር ጉዳይ ማለትም ከፖለቲካ የሸሸ ፈሪ መደበቂያ ናቸው ለማለት ነው? በዚህ ምላስዎ እሴቱ መንደር እደጁ እንደማይደርሱ አውቀውታል? እንዲያው አንድ ነገር ልጠይቆትና "እያልነሽን" ጀግንነቷን በተናገሩበት አፍዎ ሌሎች ሴቶቻችንን ሲሰድቡና ትምክህተኝነቶን ሲያንጸባርቁ ሁለቱ ነገር መጋጨቱ አልታይዎትም? ጀግናዋ እህታችን እያልነሽ የተዋጋችው ደርግንና ወያኔን ብቻ ሳይሆን የርሶ ብጤ የወንድ ትምክህተኛንም ጭምር መሰለኝ። ለዚህ ተራ ስድብዎ መሸፈኛ ሆና ባትቀርብ ደስ ይለኛል። ባሻዬ ቁንጅና እኮ አካላዊ

ገጽታ ብቻ አይደለም። እንደርስዎ ቢሆን ኖሮ ውድድርም ባላስፈለገ ነበር። መፍረድም ያስቸግር ነበር። ለዚህ ነው እዚህ ያለንበት ሕብረተሰብ ተጨማሪ የውበት መለኪያዎች ብለው የሚወስዱት አካላዊ ውበትን ብቻ ሳይሆን ማሕበራዊ አስተዋጽዖን፣ የትምሕርት ችሎታን፤ አስተሳሰብን፣ ዓላማን፣ የመሳሰሉትን ሁሉ ነው። አጅሬ ግን ዘለው የፊት ገፅታ ላይ፤ ሮጠው "ጦጣ" አሉ። የሰው ልጅን ሰው ያሰኘው ከገፅታው አልፎም አስተሳሰቡ ነው። እርስዎ ግን ከሁለቱም የተነፈጉ ይመስላሉ። ...ይቅርታ! ምስለ ቅርጽዎን (ፎቶዎን) ስላላየሁ በመሰለኝ ነው። ነገር ግን ከልምድ እንዳገኘሁት የሰውን በተለይ የሴትን ልጅ ውበት በተለይ ስለማያውቋቸው ሴቶች የሚያንቋሽሹ ወንዶች ብዙ ጊዜ መልካቸው አስከፊና አዕምሮዋቸው እንጭጭ የሆኑ ብቻ ናቸው። ቢገባዎት ውበት አንጻራዊ ነው። እርሶ ያምራል ብለው የተቀበሉት ነገር ለሌላው አስከፊ ሊሆን ይችላል። እንደተመልካቹ ነው። ጠባብ አመለካከት ያለው "ጡንቻ ራስ" የሚታየው ውበት የበሰለ አመለካከት ያለውን ሰው ላይማርክ ይችላል። ገባዎት አሁን።

ለመሆኑ እርስዎ የነኚህን ኢትዮጲያዊያን ፎቶ ከመጽሔቱ ሲያዩ ዝቅ ብሎ ስለትምህርት ደረጃቸው የተጻፈውን ልብ ብለው ተመልክተዋል? በተለያዩ ኰሌጆች ብዙኃኖቹ የሣይንስ (የሕክምና፣ የመሃንዲስና የኮምፒዩተር...ወዘተ) ተማሪዎች ናቸው። እዚህ ሁለተኛ ቤታችን /አገራችን ብለን በያዝነው አሜሪካን ያሉት ኢትዮጲያዊያን እህቶቻችን የዕለት እንጀራቸውን አቸንፈው ኰሌጅ ተምረው፣ በአሜሪካን የኢትዮጲያውያን ማኅበራዊ እንቅስቃሴ ተካፍለው፣ ዘረኛነትን ተቋቁመው ከሁሉም በላይ ደግሞ እንደርስዎ ያለውን አሉባልተኛ የወንድ ትምክህተኛ ተቋቁመው እዚህ መድረሳቸው እሰየው በርቱልን በተባሉ እንጂ እንደርሶ ባለ ድንጋይ ራስ ባልተዘለፉ ነበር። እንዳው አበዛኸው አይበሉኝና እርሶ በትምሕርትዎ ምን ያህል ገፍተዋል? እንዳይሳሳቱ ከኮሌጅ መመረቅ የግል ዕውቀት መለኪያ አይደለም። የትምሕርት ቤት ደጃፍ ሳያዩ ባስተሳሰባቸው የላቁ ግለሰቦች አገራችን ነበራት አላትም፣ ይኖራታልም። የርስዎን ግን ተጠራጥሬ ነው። አሁንም ፈረንጆቹን ልጥቀስና ‘ትንሽ ዕውቀት አደገኛ ናት’ እንዲሉ አዋቂ መስለው መታየት ፈልገው እንደሆነ ማለቴ ነው። በመጨረሻ "...ትምክህተኛ ብላችሁ እንዳትኮንኑኝ ...እኔ የምፈራው እናንተን ይህን የምታነቡ ነገረኞቹን ነው።" ብለዋል። ተሳስተዋል እዚህ ጊዜ የተረፈው እንደርሶ ያለ አሉባልተኛ የለም። ሁሉም ጥሮ ለፍቶ አዳሪ ነው። ቢሆንም በዚህ አያያዝዎ ሌላ የተደናበረ፣ ዓላማ የሌለው፣ ኢላማውን የሳተ ጽሑፍ ከመጻፍዎ ወይም ብዕሮን ከማሾልዎ በፊት ስለምንድን ነው የምጽፈው? ለማን ነው የምጽፈው? የሚለውን ጨምሮ ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ እንዳሉት

"ምላስን በልጓም ስበህ ካልያዝከው፣
እንኳን እራስህን ታስፈጃለህ ሰው።"

የእርሶ አንሶ እኛን እንዳያሰድቡን ነው። በርግጥ ወንድ ሁሉ እንደርሶ አያስብም። በርስዎ ጽሁፍ የተነሳ ሌሎች ወንዶች መተቸታቸው ግን አይቀርም። ታድያ በሚቀጥለው ጊዜ መረን ከለቀቀና ስድብ ካዘለ ኢ ማሕበራዊ ትንታኔዎ ቆጠብ ብለው ግራ፣ ቀኝ፣ ላይ፣ ታች አይተው ስሜታዊ ሳይሆን ነባራዊ (Objective) የሆነ ጽሑፍ ይጻፉ። መፖትለክ ወይም ስለፖለቲካ መጻፍ ከፈለጉ በቀጥታ ይጻፉ። እንዲሁ ካረጉ እንዳለፈው ጽሑፎ ገብተው ሊወጡ ከማይችሉበት የአስተሳሰብ ማጥ ከመጥለቅ ይጠብቅዎታልና። . . .አሜን

ለማጠቃለል የቁንጅና ተወዳዳሪዎቹንና አዘጋጅዋን እንኳን ደስ ያላችሁ እላለሁ። አንድ ነገር ለመጀመር ብዙ ችግሮች ያጋጥማሉ። ለተሳካ ነገር ደግሞ እንደ ባሻ ወለም ዘለም ግንባር ቀደም አሉባልተኛ መኖሩን አውቃችሁ ሳትደናገጡ በርቱበት። የሚቀጥለው ዓመት ዝግጅት የተሻለና የበለጠ የተሳካ እንዲሆን ምኞቴ ነው።

## በሚቀጥለው እትም የሚወጣ

## « ዕጣዬ »

"ተወልጄ ያደግሁት አዲስ አበባ ነው። አባትና እናቴ የመጡት ከኤርትራ ነው። አስመራ አለ እንዴ አልሄድኩም። አላውቀውም ብል ይሻለኛል። ባሌ የልጄ አባት የአማራና የኦሮሞ ቅልቅል ነው። አሁን ያለሁት አሜሪካን ነው። ባሌ በስደት ኬንያ ነው ያለው። የመጣሁባት እህቴ የአባቴ የእናቴ ልጅ ከአማራ በመውለዴ ከዳችኝ። አብሮ አደግ ጓደኞቼ (አማራዎችም፣ ኦሮሞዎችም) ሁሉ ‘ገንጣይ ነሽ’ ብለው ሸሹኝ። . . . ያለሁበት ችግር፣ የደረሰብኝ መከራ ይህ ነው አይባልም። በተለይ ባለፉት ሶስት ዓመታት . . ." (አብረኸት)

በጣም ሰፊና እጅግ አሳዛኝ እውነተኛ ታሪክ ነው። በብዕር ስሟ "ዕጣዬ" በሚል ርዕስ በሚቀጥለው እትም እናቀርበዋለን።

ለእህት አዛለች

ከኤደን ዳንኤል (D.C)

ይድረስ ለእህት አዛለች በሁለተኛ ዓመት ቁጥር ሦስት ላንዳፍታ እትም የጻፍሺውን ጽሁፍ አንብቤ ከጨረስኩ በኋላ ለሁለት ወይም ለሦስት ደጋግሜ ከአሰብኩበት በኋላ እንደ እራሴ ጉዳይ ነገሩ ስለከነከነኝ ቢጠቅምሽም ባይጠቅምሽም ከእራሴ ሕይወት ታሪክ ጋር ተመሳሳይነት ስላለው ለምን አላጫውታትም በሚል ብዕሬን አነሳሁ።

አዛለች! በእውነቱ የኔ እግር በአንቺ ጫማ ውስጥ ነበር ብልሽ ማጋነን አይሆንብኝም። እንደምገምተው 70% ኢትዮጲያዊ ስደተኛ እንደ አንቺ አሜሪካ ማለት ብር በአካፋ የሚዛቅበት ሀገር ብሎ ነበር የሚያምነው። እንዲያውም አንቺ አጎትሽን የአሜሪካ ፊልም አሳይተሽ የአሜሪካንን ታላቅነት እንዲያዩት እንዳደረግሺው ሁሉ የሰው ፖርሽ መኪና ተደግፎ ፎቶግራፍ ተነስቶ ተልኮለት ሀሳቡንና አላማውን በሙሉ ያልቀየረ አልነበረም። የኔ እመቤት ወንድሜ የሶዳ ቆርቆሮ አንስታ የላከችለት በቅርቡ የመጣች እህቴን ፎቶግራፍ ተመልክቶ "ወይ ጉድ አገራችን ቆርኪ ጥለህ ዞር እስከምትል ቆርኪውን አታገኘውም እንዲያው "በቆርቆር ያለሽ" ንግድ የሚተዳደረው የሀገሬ ዜጋ አሜሪካ ቢመጣ እንዴት ይከብር ነበር?" ብሎ የጻፈላትን ደብዳቤ ሳስበው ምን ያህል እንኳን እንደነበረ ይገርመኛል። ከመጣንም በኋላ ቲቪው፣ መብራቱ ምንም እንኳን አገራችን የበለጠ አለባበስ ቢኖርም የሀገራችን ወጣቶች የሚለብሱት ተወዳዳሪ ባይኖረውም ይበልጥ የሚታየን እዚህ በፈረንጂኛ ተነጋግሮ መኖርን ያልሆኑትን ሆንን ብሎ ማስወራት ሊያውም የአንድ ካምፓኒ ሃላፊ ወይንም ባለስልጣን ነን ብሎ ማስወራቱ የተለመደ ስለሆነ አያስደንቀኝም።

በታዳጊዋ ላንዳፍታ መጽሔት እድል ገጥሞሽ በቁጥር 2 ወይንም ተከታታዩን እትም የመጽሔቱን አዘጋጅ ክፍል ጠይቀሽ ብትገናኚና ብታነቢ በተለይም "ኑሮ በአሜሪካ" የሚለውን እትም በእውነቱ ችግርሽ ሊቃለል የሚችል ይመስለኛል።

በእውነት አብረሻት ያለሽው ዘመድሽ እርዳታዋ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። እንኳንስ ከሥራ ደክሞት መጥቶ ከተማውን ሊያስጐበኝሽ ቀርቶ ሊያውስ አንድ ወር በጣም እድለኛ ሆነሽ ነው። የትምህርቱን ጉዳይ እሷ እንዳስቀመጠቺው እየሠራሽ የምትማሪበት መሆኑንም ሳልጠቅስልሽ አላልፍም። ነገሬን ባላበዛም ይኸው የጓደኛዋ ጓደኛ ባለግሪን ካርዱ

"ወይ ግሪን ካርድ የለሽ ወይ የሥራ ፈቃድ!
እንዲው ቡልሺት ብቻ ከአንቺ መዋደድ።"

የሚለውን ጭውውት አስታውሰኝ። እንዲያው ምን ያህል እውነትነትስ አለው የሱ ሲቲዝን መሆን ወይንም ባለግሪን ካርድ። ከላይ እንደጠቀስኩልሽ ሕይወቴን በሰው እጅ እስከማጣ ጉድ ያረገኝ ግሪን ካርዱ ነበር። "አሄሄ ጎበዝ! እንዲያው ይህ ግሪን ካርድ የስንቱን ቤት አንኳኳቷል" ያልኩትም የአንቺን ጽሁፍ ከአነበብኩ በኋላ ነው። ለመሆኑ ሳትጠቅሺው ያለፍሺው ጉዳይ የዘመድሽስ የስራ ፈቃድ የተገኘው በዚሁ በጋብቻ ይሆን?

የኔ እህት ሁለቴ አስቢበት። እንደማንኛውም ኢትዮጲያዊ በሕጋዊ መንገድ ጠበቃ አግኝተሽ ብትነጋገሪ የሚሻልሽ ይመስለኛል። "ተቀምጠው የሰቀሉት . . ." ይባል የለ እምዬ! ሀገሪቷ በቀማኞች የተሞላች ናት። ደግሞስ ምን ያህል እርግጠኛ ሆነሽ ነው በእሱ የምታገኚው? ለኢንተርቪው ከመቅረባችሁ ሁለት ሳምንት ቀደም ብሎ ሕጋዊ ሚስቱ ስለሆንሽ በአንድ ጣርያ ስር መኖር አለብን ቢልሽሳ? የኔ እመቤት አስቢበት። በእውነቱ ጠቅላላውን የሀገሬን ዜጋ በአንድነት መጨፍለቄ እንዳልሆነ ተገንዘቢልኝ። የዋሆች ከመጡበት የሱዳንና የግሪክ እንዲሁም የኬኒያን ስደተኞችን አያጠቃልልም። እኔ ልንገርሽ። "እኔ ከበላሁ ለሷም ላጉርሳት" ከሚባልበት ምድር ሳይሆን ያለሽው እዚሁ ታላቋ አሜሪካ ቅሌታምና ሌባ ከበዛበት ነው። እህት "ከባለቤቱ ያወቀ ..." እንደሚባለው አስተያየቴን አድምጪኝ። "ምን አለች?" ትይኛለሽ።

## የላንዳፍታ መጽሔት መርህ

## ፍቅር ሰላም አንድነትና ተከባብሮ መኖር !!

ምነው ልዩነታችንን አችችለን በሰላም መኖርን መማር አቃተን ?

# « እመሰግናለሁ! »

ከኤልሣቤጥ ገበየሁ
(ሲያትል ዋሽንግተን)

በወንድማችን መስፍን መንገሻ አስከሬን መጓጓዣ በተደረገው የገንዘብ መዋጮ ለረዳችሁ ሁሉ ስላደረጋችሁት ሰብዓዊ ዕርዳታና ከልብ የሆነ ሀዘናችሁን እያመሰገንን በተለይ በሲያትል ዋሽንግተን ለሚገኙ የኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አባላቶች፣ በሲያትል የኢትዮጲያ ኮሚኒቲ በካሊፎርኒያ የኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አባላትና የቤተ ክርስቲያን ሃላፊዎች ለ"ጊዜ" የሬጌ ሙዚቃ ባንድ በአጠቃላይ ለዚህ ዓላማ መሳካት እርዳታችሁን ለለገሳችሁ ሁሉ በድጋሚ ከፍ ያለ ምስጋናዬን በቤተሰቡ ስም አቀርባለሁ። በተጨማሪ አስከሬኑን ወደ ኢትዮጲያ ለመላክ በነበረው ዝግጅት ላይ ምንም እንኳን መስፍንን ባታወቁትም በኢትዮጲያዊነቱ ብሎም በደረሰበት አሣዛኝ አደጋ ልባዊ አዘን ተሰምቷችሁ የፈረንጅ አገር የጊዜው ውድነት ሣይወስናችሁ ጊዜአችሁን ሰውታችሁ የነበረውን ውጣ ውረድ ለተጋፈጣችሁ ጥቂት ሰዎች ደግመን በቤተሰቡ ስም ምስጋናዬን ከማቅረብ ሌላ ይህ ቅዱስ የሆነ ሃሣባችሁ በሕይወት ዘመናችሁ ሁሉ ካደረጋችሁት መልካም ሥራ የበላይነት አለው ብዬ አምናለሁ። በዚህ አጋጣሚ በሌላ መልኩ ይህንኑ ጉዳይ ለማስፈፀም የገንዘብ መዋጮ በሚደረግበት ወቅት ለዚህ ጉዳይ ወደ ካሊፎርኒያ ሄጄ ያጋጠመኝን ገጠመኝ ይህን ዕድል ካገኘሁ ለአንባቢያን ላካፍል እወዳለሁ።

ካሊፎርኒያ የሄድኩበትን ዓላማ ለማሳካት የመጀመሪያው ሥራዬ የየቤተክርስቲያኑን ሃላፊዎች የመጣሁበትን ጉዳይ በስልክ ማስረዳት ነበር። ስለዚህም በመጀመሪያ በኦክላንድ ካሊፎርኒያ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሃላፊዎችን ደውዬ በማግስቱ ማለትም እሁድ ቀን በአባላት ፊት የመጣሁበትን ጉዳይ ከሟች ሕይወት ታሪክ ጋር አያይዤ እንድናገር የ5 ደቂቃ ጊዜ እንዲሰጡኝና መዋጮ እንዲደረግ ፈቃዳቸውን ጠየቅሁ። እነሱም በነገሩ ደንግጠውና አዝነው የምገኝበትን ቦታና ሰዓት ነግረውኝ ስልኩን ዘጋሁ። ሁለተኛው ስልኬ ለኢትዮጵያውያንን ክርስቲያን ፌሎሺፕ (ወንጌላዊት) ቤተክርስቲያን ሃላፊዎች ነበር። ከላይ እንደገለጽኩት ለዚህኛውም ቤተክርስቲያን ሃላፊዎች ይህንኑ ጉዳይ አስረዳሁ። መልሳቸው "ምንም የወንድማችን ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ቢያሳዝንም በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ስለ ሟቹ ምንም ማስታወቂያ መደረግ እንደማይቻል" ተነገረኝ። በመጀመሪያ ጆሮዬን አላመንኩትም። ተሳስቼ እንደሆን ብዬ ደግሜ አስረዳሁ። አሁንም መልሱ አይቻልም ነበር። ምክንያቱን ለማወቅ ችኮላዬ ለጉድ ነበር። ታዲያ ከመልሱ የምክንያቱ ባሰብኝ። ምክንያቱም ያ ነፍሱና ሥጋው የተለያየችው ወንድማችን በሕይወት ዘመኑ የዛች ቤተክርስቲያን አባል አለመሆኑ ነበር።

ወደ አዕምሮዬ መለስ አልኩና ምንአልባት ሃሣቤን ያለመገንዘብ ይሆናል ብዬ እኔ እኮ ከቤተ ክርስቲያኑ ባጀት ምንም ገንዘብ አልጠየቅኩም። የጠየቅኩት ነገር ቢኖር ያችን እሁድ ቀን ኢትዮጲያዊያውያን አንድ ላይ እንደተሰበሰቡ የማገኛ ወይም የመያገኘ መንገድ እንዲሆነኝ እያንዳንዱን ሰው በየቤቱ ሄዶ መጠየቅ ስለማይቻል ያንን አጋጣሚ ለመጠቀም እንደሆነ ደግሜ ደጋግሜ አስረዳሁ። በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያኑ ሣንቲም የገንዘብ ስጦታ ጋር ከተሰጠ በኋላ መጨረሻ ላይ ህዝቡ ሊወጣ ሲል 5 ደቂቃ ሰጥታችሁኝ የደረሰውን አሣዛኝ አደጋ ከሟቹ የሕይወት ታሪክ ጋር አያይዤ አጭር ማስታወቂያ እንዳደርግ ብዬ ደግሜ ልመና ገባሁ። በፍፁም የቤተክርስቲያኑ አባል ስላልሆነ ይህ የኛ አላፊነት አይደለም ተባልኩ። ያኔ ነበር የሰው ልጆች ምን ያህል የደነደነ ልብ እንዳለው የተረዳሁት። ከሁሉም በላይ ያስደነቀኝ የሃይማኖት ሰዎች ነን በማለት የእግዚአብሔርን ቃል እየሰበክን ሰዎችን ወደጌታ ቤት ለማምጣት የቆምን አልፎ ተርፎ በክርስትና ሕይወታችን ውስጥ የክርስቶስን ህያውነት በመልካም ምግባራችን በዚች ምድራዊ ሕይወታችን ውስጥ አንፀባርቀን ለሌሎች ምሳሌ መሆን ሲገባን የዚህ ዓይነቱ ሥራ እጅግ አስደነገጠኝ።

ኸረ ለመሆኑ የትኛው የእግዚአብሔር ቃል ነው የትኛውስ ቦታ ላይ ነው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ለአባላት ብቻ የሚለው? ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ዮሐንስ ራዕይ የእግዚአብሔርን ቃል ስናነብ አባል የሚባልስ የት ቦታ ነው ያለው? ሟቹ ክርስቲያን ባይሆንስ የሌላ ሃይማኖት ተከታይ ቢሆን? ደግሞስ የማንንም ዕምነት ማንም መለካት እንደማይችል የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል። ከሞት በላይ የምድራዊ ሕይወታችን አስከፊ ነገር አለን? በሰው አገር ላይ በሰው እጅ ሕይወትን ከማጣትስ ሌላ ምን የሚደርስ ነገር አለ? የአባልነትንስ ጥያቄ ምን አነሣው? የምናወራው አሁን ነፍሱ ከስጋው ስለተለየችው አንድ ቀን ግን እንደኛ በሕይወት ቆሞ ሲመላለስ ስለነበረው መስፍን መሆኑ ተረስቶ በሕይወት ዘመኑ ስለነበረው ዕምነት ማንስ ማን ጠያቂ አደረገን? እዚህ ላይ መረሳት የሌለበት ነገር ደግሜ እላለሁ፤ ከቤተ ክርስቲያኑ ባጀት 0.5 ሣንቲም አልጠየቅኩም። ህዝቡ ያለውን ተሠምቶት እንዲሰጥ አጋጣሚውን ያቺን 5 ደቂቃ ልጠቀም ነበር ጥያቄዬ። የቤተክርስቲያን አገልግሎት የእግዚአብሔርን ህያውነት ላልተረዱ ቃሉን በማስተማር ወደ እግዚአብሔር ቤት እንዲመጡ መሆኑ ቀርቶ የተገላቢጦሽ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ለአባላት ብቻ፣ እንዴ አምነው ክርስቲያን ለሆኑ መሆን የለበትም። ይህ የኔ አስተያየት ነው። ለአባላት ብቻ የቆመች ማህበር ስሟ ቤተክርስቲያን አይመስለኝም። ከተሣሣትኩ ምንግዜም ልታረም ህሊናዬ የተዘጋጀ ነው። ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤት ለሁሉም ክፍት የሆነ ያመነ

ያላመነ የማትል በእግዚአብሔር አምሳል ለተፈጠረ ፍጡር ሁሉ እጆቿን ዘርግታ የቆመች መሆን አለባት። ምክንያቱም ክርስቶስ የመጣው የእግዚአብሔር ሰዎች ለተባሉት ሳይሆን ለኃጥያተኞች ነውና። እግዚአብሔርም ለሰው ልጆች ሁሉ ሲል አንድ ልጁን አሳልፎ ሰጥቷልና። የሃይማኖት ሰዎች ከምንባል የዚህ አይነቱ ነገር ሲሰማ እጅግ ያሳዝናል። ሌላው ቀርቶ ይህ ሰው በኢትዮጲያዊነቱ ብቻ መረዳት የለበትምን? ባህላችንን፣ ኢትዮጲያዊነታችንን የት ልናደርገው? ሞት ደግሞ ሳያስጠነቅቅ፣ መጣሁ ሳይል፣ ነጭ፣ ጥቁር፣ ወንድ፣ ሴት፣ያመነ፣ ያላመነ ሳይል ድንገት የሁላችን ቤት ሊያንኳኳ የሚችል ነገር ነውና ነገ አፈር መሆናችን ተዘንግቶን ከእንሰሳት ሁሉ የበላይነትን ቦታ ያሰጠንን ያንን ክቡር ህሊናችንን ለደግ ነገር ሳናውለው ስንቀር ያሣዝናል። ወደ ታሪኩ መገባደጃ ልመለስና ማስታወቂያውን በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ በጉባኤው ፊት መንገር እንደማልችል ሲነገረኝ እንግዲያውስ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ምንም ስልጣን ስለሌለኝ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ለሚደረገው ነገር እንደማይከለክሉኝ ተስፋ በማድረግ በሩ ላይ ቆሜ ህዝቡ ሲወጣ ጊዜውን ወስዶ የሚሰማኝ ካገኘሁ ልለምን ወሰንኩ።

ነገር ግን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ልባቸው ቢራራ ብዬ ተስፋ ሳልቆርጥ እሁድ ቀን ፕሮግራሙ ከመጀመሩ በፊት ላነጋግራቸው ሄድኩ። ጊዜውን ወስዶ የሚያነጋግረኝ ሰው አጥቼ ከስንት ደጅ ጥናት በኋላ የቤተ ክርስቲያን ሶሻል ኮሚቴ ተነጋግሮበት ውሳኔውን ይነግርሻል ተባልኩ። ይሄ ሲነገረኝ የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም ተጀምሮ ዘማሪያን የመጀመሪያውን መዝሙራቸውን እያሠሙ ነበር። መቼ ነው ሶሻል ኮሚቴው ተሰብስቦ ውሳኔ የሚያሳልፈው? ለነገሩ ምንም ዓይነት ትኩረት አለመስጠቱና የልጅ ጨዋታ ዓይነት መሆኑ የገባኝ ያኔ ነበር። የስዓቱ መጣበብና የእኔ ምሽቱን ወደ ሲያትል መመለስም ተነግሯቸዋል። ብቻ የሞት አስደንጋጭነቱ መልኩን የቀየረበት፣ ርህራሄና ሰብአዊነት የጠፋበት ስሙ ግን የእግዚአብሔር ደጅ ሲሆን ሁኔታውን ህሊና ያለው ሁሉ እንብቦ ይፍረድ ብዬ እተወዋለሁ።

ከዚያም መጨረሻውን እያለሁ ብዬ ፕሮግራሙን ለመካፈል እኔም ወደ ቤተ ክርስቲያን ገባሁ። መዝሙሩ፣ ፀሎቱ፣ ስብከቱ ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር ይደረጋል። ምዕመናንም በመንፈስ እግዚአብሔርን ያመልካሉ። ለእኔ ግን ያቺ ሰዓት የጭንቅ ነበረች። እግዚአብሔር የማያዳላ ሁሉን በአንድ ፍቅር ዓይኑ እንደሚያይ ልቤ እያወቀው የተሠራውን ሥራ ሣስበው አዕምሮዬ እረፍት አጣ። መዝሙራችን፣ ፀሎታችን፣ አምልኮታችን፤ ፍቅር ከሌለው ከንቱ እንደሆነ ሀዋርያው ጳውሎስ በ፲ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 13 ላይ ይነግረናል። ታድያ መቼ በዚያ ቆሙ። ፕሮግራሙ ሊያልቅ ጥቂት ደቂቃ ሲቀረው የሶሻል ኮሚቴውን ውሣኔ ለመስማት ቸኩያለሁ። ድንገት ፕሮግራሙን ይመራው የነበረው ፓስተር "አንድ ልጅ የምነግራችሁ ነገር አለኝ ብላለችና አንድ ነገር ትነግራችኋለች፤ ስንወጣ ሻይ ቡና ለመጠጣት የምንሰበሰብበት ክፍል ውስጥ ጠብቋት፤ እስቲ እንዲያዩሽ አንዴ ተነሺ፤" አለ። ጉልበቴ እየተንቀጠቀጠ ቆምኩ። ሲቃ ተናንቆኝ ወጥቼ በር ላይ ቆምኩ። አንድ ነገር ተብሎ የተሸፋፈነው ሞትን ያህል ነገር ነበር። ምናልባት ቀኑ Nov. 29, 1992 በፕሮግራሙ ላይ የነበራችሁ ሰዎች ካላችሁ ማስታወቂያው ይህን ይመስል እንደነበር ለማስታወስ አይቸግርም። ሻይና ቡና ለመጠጣት ያልፈለጉና የቸኮሉ ሰዎች ከቤተ ክርስቲያኑ ወጥተው "አንድ ነገር" የተባለውን ሳይሰሙ ቀጥታ ወጥተው ወደ የመኪናቸው ገቡ። በር ላይ ቆሜ ከብቱ እንደተበታተነበት እረኛ "እባካችሁ ተመለሱ የምናገረው አለኝ" ብዬ መማፀን ገባሁ። የሄዱትም ሄደው ጥቂት ሰዎች ቡናው መጠጫው ክፍል ተገኙልኝ። የተባለውን "አንድ ነገር" ነገርኳቸው። ልባቸው በሀዘን ተሰብሮ እንባቸውን ያፈሰሱም አየሁ። "ከኑግ ጋር የገባ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ" እንዳይሆንብኝ እነዚህ ከገንዘባቹው ጋር እንባቸውን ያፈሰሱትንስ ዝም ብዬ ባልፈው ህሊናዬ የእነሱም በጐ ሥራ ይወቅሰኛል። በተለይም እንደ አቶ ይሽው ሣህለ ማርያም ያሉ የዚያው ቤተ ክርስቲያን አባል በነገሩ ደንግጠው ሣይሄዱ ከተረፉት ሰዎች የተገኘውን ገንዘብ አሠባስበው እንዲሁም ሳይሰሙ ለሄዱት ሰዎች ተቆጭተው በሌላ ጊዜ በቅርብ ለሚያውቋቸው ነግረው ሲያትል ድረስ ቼክ የላኩልኝ ሰውም አሉ። እንደነዛ አይነቶቹን ሰዎች የትኛው ቦታ ላስቀምጣቸው? እሁንም ለአንባቢያን ትቼዋለሁ።

ምንም እንኳን የመልዕክቴ ዋና ዓላማ የወንድማችን መስፍን መንገሻ አስከሬን ለአገሩ አፈር ላበቃችሁ ሁሉ ምስጋናዬን ለማቅረብ ቢሆንም በሌላው መልኩ ደግሞ በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አባል ካልሆናችሁ አንረዳም የሚለው ብዙዎቹን ከእግዚአብሔር ቤት የሚያሸሽ ነገር መሆኑን ላልተረዱ የቤተ ክርስቲያን ሃላፊዎች ይታሰብበት እላለሁ። አሁንም መልዕክቴ ለቤተ ክርስቲያን አባላት ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያን ሃላፊዎች ነውና የተሰጣችሁ ሃላፊነት ቀላል አይደለምና ልፋታችሁ ከንቱ እንዳይሆን አንዴ አምነው አባል ለሆኑ ብቻ ሳይሆን ወደ እግዚአብሔር ቤት በመምጣት ላይ ላሉም ይታሰብበት እላለሁ። ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤት፣ የእግዚአብሔርን ህያውነት አምኖ ለመጣ የሰው ልጅ ፍጡር ሁሉ ክፍት የሆነና አገልግሎቱም ለተቸገሩ ሁሉ መሆን አለበት ብዬ አምናለሁ። ስለዚህም የተሰማኝን እውነታን አስደግፌ በዚህች አጋጣሚ መልዕክቴን በማስተላለፌ ቅር የተሰኛችሁ ብትኖሩ የጽሑፉ መድረክ ለሁላችንም ክፍት ነውና ከተሣሣትኩ ለመታረም ህሊናዬ የተዘጋጀ ነው። ስህተትን ስህተት ነው ካላሉት ለእውነታ የተጠጋ ይመስላልና።

እንዲህ ሆን

# የመስቀል በዓል በአትላንታ በደማቅ ሁኔታ ተከበረ



ነጋሪቱ እየተጐሰመ፣ እልታታውና ዘፈኑ እየቀለጠ ሕዝበ ክርስቲያኑ ደመራውን ሲዞር

መስከረም 17 ቀን 1986 ዓ.ም. አትላንታ የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን ተከታዮች የመስቀልን በዓል በደመቀ ሁኔታ አክብረዋል። ኮርትላንድ ጐዳና በሚገኘው በቅድስት ማርያም የኢትዮጲያ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቁጥራቸው በግምት ወደ ሦስት መቶ የሚሆን ኢትዮጲያዊያን አብዛኞቹ በአገር ልብስ አሸብርቀው በጠዋት በመገኘት ሙሉ የቅዳሴ ሥነሥርዓት በማከናወን ጸሎት አደረሱ።



በአገር ልብስ ያሸበረቁ ልጆቻችን በበዓሉ ላይ

ልብሰ ተክዕኖ የለበሱ ቀሳውስት ሥነሥርዓቱን በአገራችን ባህልና ወግ መሠረት አካሂደው ሥርዓተ ቁርባን ተካሂዶ ከተፈጸመ በኋላ ጉዞ ደመራ ወደተዘጋጀበት ወደ ግራንትት ፓርክ ሆነ። በተለይ የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች የሆኑት ታዳጊ ሕፃናት በአገር ልብስ አሸብርቀው በዚያ የደመራ ሜዳ ላይ ውር ውር እያሉ ሲጫወቱ ማየት እንዴት ደስ ያሰኝ ነበር። ደመራው እንደ አዲስ አበባው መስቀል አደባባይ ሰማይ ጠቀስ ባይሆንም ለሥነሥርዓቱ መድመቅ ትልቅ አስተዋጽዖ አድርጓል። በሚቃጠል ችቦ ፋንታ ሕፃናትና ወጣቶች በእጃቸው የያዙት ጧፍ ሌላ ድምቀት ሰጥቶ ነበር። ምዕመናኑ ተሰብስበው እንዳበቁ ቀሳውስቱ ልብሰ ተክዕኖና ዣንጥላ በመያዝ በደመራው የሚደረገው የፀሎትና የቅዳሴ ሥነሥርዓት ተከናወነ።

ከዚያም ነጋሪቱ እየተጎሰመ በደመቀ ሁኔታ ሕዝቡ እየዘፈነ እያጨበጨበ ደመራውን ዞሮ እንዳበቃ ያገር ባህል ዘፈንና ጨዋታ ተጀመረ። ኦርኬስትራ ወይም ባንድ ወይም ታዋቂ ድምፃዊ ተጫዋች ሳያስፈልግ ወንዱም ሴቱም እየተቀበለ ዘፈኑንና እስክስታውን አስነካው። ግራንት ፓርክ ለዛን ዕለት መስቀል አደባባይን መሰለ። ይህ ድምቀት በዚህ እንዳለ ከበዓሉ አካባቢ ያለው ጎጆ መሳይ ቤት (ጋዜቦ) ሴቶች እህቶቻችን ደፋ ቀና ሲሉ አየንና ወደዚያው ስንሄድ በያይነቱ የአገር ምግብ ሲዘጋጅ አየን። "እንዴ ለዚህ ሁሉ ሕዝብ የሚበላ ምግብ ከየት ሊመጣ ነው?" እያልን ስንገረም የምግብ ሰዓት ደረሰና ስናይ ገረመን። ከየቤቱ የመጣው ጣፋጭ ምግብ በበዓሉ የተገኘውን ሕዝብ አጥግቦ መገበ። ጨዋታው እንደደራ ቆይቶ መምሸት አይቀር ሲመሽ "ዓመት ዓመት ያድርሰን" ተባብሎ ተለያየ።



ጭፈራውና እስክስታው ለጉድ ነበር

# ቢል ካምብል ኢትዮጵያውያን ድጋፍ ሰጡአቸው!

ለአትላንታ ከተማ ከንቲባነት የሚወዳደሩትን ቢል ካምብልን እንደሚደግፉቸው በአትላንታ ከተማ የሚገኙት የኢትዮጵያውያን ቢዝነስ አሶሲዬሽን አበላት ገለጹ። አክቶበር 25 1993 በኒኮስ ሬስቶራንት ማህበሩ ባዘጋጀው የቁርስ ሥነ ሥርዓት ላይ እጩ ከንቲባ ቢል ካምብል ተገኝተው ይኸው የድጋፍ መግለጫ የተነገራቸው ሲሆን ለመወዳደሪያ ወጪ መደጐሚያ የማህበሩ አባላትና ደጋፊዎች $5,000 (አምስት ሺህ ብር) አዋጥተውላቸዋል። ቢል ካምብል ከውጪ አገር በመጡ ሰዎች በተቋቋመ ማህበር የዚህ ዓይነቱ ድጋፍ ሲደረግላቸው የመጀመሪያው በመሆኑ የተደነቁ ሲሆን በተደረገላቸው ድጋፍ በጣም ደስ ያላቸው መሆኑን ገልጸዋል። ዝግጅቱን በማስተባበር ያካሄዱት አቶ ተክሌ አየለ የ 'ኤ ኤንድ ቢ አሶሺየት ሞርትጌጅ ኩባንያ' ባለቤት፣ ወ/ሮ ኢትዮጵያ አልፍሬድ የ'ደራሽ ኢንክ አስመጪና ላኪ' ባለቤትና አቶ መክረን ጣሰው 'የጂክስ ካፌ'ባለቤት ናቸው። የዝግጅቱን አስባባሪ አቶ ተክሌ አየለን ቃለ መጠይቅ አቅርበንላቸው ነበር።

— ላንዳፍታ፤ ይህን ዝግጅት ለማድረግ ምን አነሳሳችሁ?

— አቶ ተክሌ፤— በአትላንታ ከተማ የምንኖር ኢትዮጵያውያን ከከተማው መሪዎች ጋር ግኑኙነታችችንን ለማጠናከርና እነሱም አውቀውን ከተማዋ ለነዋሪዎቿ የምትሰጠውን ዕድል ሙሉ በሙሉ ለመካፈል እንድንበቃ መንገድ ስለሚከፍትልን ነው።

— ላንዳፍታ፤— በከተማው የሚኖሩትን ኢትዮጵያውያንን በሚመለከት ያቀረባችሁት ጥያቄ አለ በዚህ አጋጣሚ?

— አቶ ተክሌ፤— አምስት ጥያቄዎች አቅርበንላቸዋል፤ 1ኛ. በ1996 በአትላታ በሚካሄደው ኦሎምፒክስ የሁለት ጊዜ ተከታታይ ማራቶን አሸናፊ የሆነው ኢትዮጵያዊው አበበ ቢቂላ የተለየ ትውስታ (recognition) የሚሰጥበት ሁኔታ በፕሮግራም እንዲያዝ። — 2ኛ. በአትላንታ ከተማ ውስጥ ዕውቀትና ችሎታ ያላቸው ኢትዮጵያውያን በከተማው አስተዳደር መሥሪያ ቤት በሙያቸው እንዲቀጠሩ፤ 3ኛ.ለኦሎምፒክ ዝግጅት ሠራተኞች ሲቀጠሩ በአትላንታ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የሥራ ዕድል እንዲሰጣቸው፤ — 4ኛ. በከተማው መማክርት ሸንጐም ሆነ የአስተዳደሩ ጽ. ቤት በሚቋቋሙ ኮሚሽኖች፣ ቦርዶችና ኮሚቴዎች ውስጥ ኢትዮጵያውያን እንዲሳተፉ፤ — 5ኛ. የከተማው አስተዳደር በሚያሠራቸው የኮንትራት ሥራዎች፣ በተለይም በኦሎምፒክ ዝግጅት ላይ በኢትዮጵያውያን የሚተዳደሩ ድርጅቶች ኮንትራት እንዲያገኙ ዕርዳታ እንዲያደርጉ ጠይቀናቸዋል።

— ላንዳፍታ፤— እጩ ከንቲባው ምን መልስ ሰጡአችሁ? በመልሳቸውስ ረክታችሁዋል ወይ?

— አቶ ተክሌ፤— ያቀረብናቸው ጥያቄዎች ያላንዳች ችግር እንደሚያሟሉልን ቃል ስለገቡልን እኛም በጣም ተደስተናል።

— ላንዳፍታ፤— ይህ ማህበራችሁ የተቋቋመው ለዚሁ ጉዳይ ብቻ ነወይስ ዘላቂነት አለው?

— አቶ ተክሌ፤— ስንጀምረው ለዚሁ ጉዳይ ነበር። አሁን ውጤቱ አርኪ ሆኖ በመገኘቱ ከሌሎች በቀረበው ሃሳብ መሠረት ቋሚ አድርገነው ሌሎችንም ጨምረን ማህበሩን ለማጠናከር ወስነናል።

— ላንዳፍታ፤— በመጨረሻ የሚያክሉበት ነገር ካለ?

— አቶ ተክሌ፤ በዚህ ዝግጅት ለተባበሩን ሁሉ ጠለቅ ያለ ምስጋና አስተላልፉልን። እጩ ከንቲባው የጠየቅነውን ለመፈጸም ቃል የገቡልን ያደረግነው ትብብርና የሰጠነው ድጋፍና ዕርዳታ ነውና መተባበር ትልቅ ጥቅም እንዳለው ወገኖቼ እንዲረዱልኝ እፈልጋለሁ። ካምብልም የገቡልንን ቃል እንደሚፈጽሙ እተማመናለሁ።



ቢል ካምብል ከዝግጅቱ አስተባባሪዎች ጋር



በአገር ልብስ ካሸበረቁ ኢትዮጵያውያን ጋር

እንዲህ ሆነ

# ፓትርያርክ ጳውሎስ በአሜሪካ ጉብኝታቸው ወቅት ከፍተኛ ተቃውሞ ገጠማቸው



ፓትርያርክ ጳውሎስ በአሜሪካ ጉብኝታቸው ወቅት

Oct.17, 1993 እሁድ ዕለት ፓትርያርኩ አቡነ ጳውሎስ አትላንታ ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ ደረሰባቸው። ቀደም ሲል ፓትርያርኩ አትላንታ በምትገኘው ቅድስት ማርያም የኢትዮጲያ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ለመገኘት ዕቅድ ማውጣታቸው እንደተሰማና የቤተክርስቲያኑ ቦርድ ጥያቄው እንደቀረበለት ፓትርያርኩ የኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሕጋዊ ፓትርያርክ አይደሉም በማለት ጉብኝቱን በመቃወም በቤተክርስቲያኑ እንዳይገኙ ይወስናል። ሆኖም ውሳኔውን በመቃወም የተወሰኑ የቤተክርስቲያን አገልጋዮች በጎን አቡኑን እንዲመጡ ያደርጋሉ። ፓትርያርኩ አትላንታ መግባታቸው እንደታወቀ ብዙ የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተከታይ ምዕመናን ከንጋቱ 5:30 a m. ጀምሮ በመደበኛው ቤተክርስቲያን በመገኘት ከውሳኔ ውጪ የመጡትን አቡን ወደ ቤተክርስቲያኑ እንዳይገቡ ለመከላከልና ተቃውሞ ለማሰማት ተዘጋጅተው ሳለ በሁኔታው ፍርሃት ያደረባቸው አቡንና አስተናጋጆቻቸው እዚሁ አትላንታ ወደሚገኝ ሌላ ቦታ የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ከአጃቢዎቻቸው ጋር ይሄዳሉ። በተቃዋሚ ምዕመናን ይኼ እንደተሰማ ተቃዋሚ ኃይሉ እንዳለ ወደ ሩሲያው ቤተክርስቲያን በመሄድ ከቤተክርስቲያኑ ፊት ለፋት ባለ ፓርክ በመገኘት ከፍተኛ ተቃውሞ አሰምቷል።




በአትላንታ የተቃውሞው ሰልፍ ላይ የታዩ መፈክሮች

የኢትዮጲያንና የአሜሪካንን ሰንደቅ ዓላማ እንዲሁም መፈክሮችን ያነገቡ ከ150 የሚበልጡ ምዕመናን "አቡኑ የፖለቲካ ካድሬ እንጂ የሀይማኖት መሪ አይደሉም፤ በጎንደር ከተማ ለተካሄደው የምዕመናን እልቂት ተጠያቂ ናቸው፣" ወዘተ... በማለት ከፍተኛ የተቃውሞ ድምፅ አሰምተዋል። በቤተክርስቲያኑ ፊት ለፊት የተሰበሰቡት ምዕመናን ሥነሥርዓቱ እስኪያልቅ በትዕግሥት በመጠበቅ ላይ እንዳሉ ሁኔታው ያስፈራቸው ጋባዦችና የሩሲያው ቤተክርስቲያን አባላት ፖሊስ ይጠራሉ። ሆኖም ከሥነሥርዓት ውጪ የሆነ ነገር ባለመኖሩ ፖሊሶቹ በተቃዋሚዎቹ ላይ የወሰዱት እርምጃ አልነበረም። ሥነሥርዓቱ እንደተፈፀመ ሁኔታው ያሳሰባቸው አስተናጋጆች አቡኑን በጓሮ በር ለማውጣት ይወስኑና በዚሁ በኩል ሊያስወጧቸው ሲሉ ተቃዋሚው ኃይል ድምፁን እጅግ ከፍ በማድረግ ለአቡኑ በሚታይበትና በሚሰማበት ሁኔታ ሆኖ "ጳውሎስ ሌባ፣ ጳውሎስ ዲያብሎስ" በማለት ተቃውሞውን አሰምቷል። በሁኔታው የተደናገጡት ፓትርያርክና አብረዋቸው የነበሩት አቡኖች በፖሊስ ታጅበው መኪናቸው በመግባት ወደ ማረፊያቸው ሄደዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ቀደም ሲል በኒውዮርክና በዋሽንግተን ዲሲ ባደረጉት ጉብኝት ተመሳሳይ ከፍተኛ ተቃውሞ እንደደረሰባቸውና እንዲያውም ቲማቲም፣ እንቁላልና ድንጋይ እንደተወረወረባቸው ዋሽንግተን ፖስት Oct.15 ዓርብ ዕለት ባወጣው እትሙ ዘግቧል። ጋዜጣው ተቃዋሚ ምዕመናንን በአቡኑ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ጠይቆ የዘገበ ሲሆን አቡኑ ስለደረሰባቸው ተቃውሞ በጋዜጣው ተጠይቀው ለሰጡት መልስ "የሚጠሉኝን እወዳቸዋለሁ ምንም አይደለም"ብለዋል። ጋዜጣው ጎንደር ስለተደረገው እልቂት ላቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት መልስ ብዙ ኢትዮጲያዊያንን አስቆጥቷል። "ዋኮ ቴክሳስ የዳቪዲያን ቅርንጫፍ ካሳየው ሁኔታ ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ አንድ አምሓ የሱስ የተባለ ችግር ፈጣሪ ሰው በፈጠረው ችግር ምክንያት ነው ይህ የሆነው" በማለት የጎንደርን ሁኔታ ዋኮ ቴክሳስ ላይ ከተፈጠረው ሁኔታ ጋር ለማመሳሰል መሞከራቸው ብዙውን ከማስገረሙ ሌላ ትዝብት ውስጥ ከቷቸዋል። አንዳንድ ታዛቢዎች "ፓትርያርኩ የጉንደርን ምዕመናን እልቂት ከቴክሳሱ ሁኔታ ጋር ሊያይዙ የፈለጉት የአሜሪካኖችን ድጋፍ ለማግኘት ሲሉ የሰነዘሩት "ፖለቲካዊ" ሸር ነው፤" በማለት ግምታቸውን ገልጸዋል። "ዘ ሰን የተሰኘው የሜሪላንድ ጋዜጣ October 17 ባወጣው እትሙ እንደገለጸው በባልቲሞር የሚገኘው የዋልተርስ አርት ጋለሪ ያዘጋጀው "Africa Zion - The Sacred Art of Ethiopia" የተሰኘውን ፓትርያርክ ጳውሎስ ሊከፍቱት የነበረው ኤግዚቢሽን በቦታው ተገኝተው ተቃውሞ ባሰሙ ኢትዮጵያውያን ምክንያት ሳይከፈት ቀርቷል። ጋዜጣው ተቃዋሚዎቹ በሥዕል ኤግዚቢሽኑ ላይ ምንም ቅሬታ እንደሌላቸውና ቁጣቸው በእንግድነት በተጋበዙት ፓትርያርክ ላይ መሆኑን ዘግቧል። ከአትላንታ መልስ ለንደን ላይም ከፍተኛ ተቃውሞ እንደደረሰባቸው ይወራል።

ፓትርያርኩ ወደ አሜሪካ የመጡበት ምክንያት በይፋ የታወቀ ነገር የለም። በአሁኑ ጊዜ በአሜሪካ አገር ያሉት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በእኚሁ ፓትርያርክ ላይ ባለው ተቃውሞ የተነሳ ኢትዮጵያ ከሚገኘው በፓትርያርክ ጳውሎስ ስር በሚተዳደረው ዋናው ቤተክህነት ስር አይደለንም ማለታቸው የታወቀ ሲሆን ምናልባትም አመጣጣቸው ይህንኑ መስመር ለማስያዝ የተደረገ ነው የሚሉ አሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ዕርዳታ ለመጠየቅ ነው የሚባልም ወሬ ነፍሷል። እውነተኛነቱ አልተረጋገጠም እንጂ አመጣጣቸው በየዓመቱ አሜሪካ በመመለስ መታደስ ያለበትን የአሜሪካ የመኖሪያ ፈቃዳቸውን (ግሪን ካርድ) ለማሳደስ ነው የሚልም ወሬ ሰምተናል። ለማንኛውም በዚሁ ጉብኝታቸውን አቋርጠው ይሁን ጨርሰው መመለሳቸውን ለማወቅ ችለናል። ■


በላንዳፍታ መጽሔት ድርጅቶን ያስተዋውቁ!

Lion of Judah Travel
የይሁዳ አንበሳ የጉዞ ወኪል

Announcing our winter airfares. We are ready to give you discounts up to 70% on your domestic travel
also call and ask how your friends can fly for free.

ወደ አዲስ አበባና አስመራ የምትጓዙ መንገደኞቻችን ሁሉ ጉዟችሁ የተቃና ያማረ እንዲሆን እየተመኘን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አየር መንገዶችበመጠቀም ልናገለግላችሁ ተዘጋጅተናል::

የኢትዮጵያ አየር መንገድ+ሉፍታንዛ+ ብሪትሽ፥ አሜሪካንና ዩናይትድ ኤር እንዲሁም ሌሎችን በመጠቀም የመጨረሻና አነስተኛ ዋጋ ይዘን እንወዳደራለን:: ከኛ ያነሰ ዋጋ ካለ ልዩነቱን እንከፍላለን:

$1065.00 ደርሶ መልስ ነው $725.00 አንድ ጊዜ ነው
ለአንድ ዓመትና ለስድሥት ወር የሚሆን ትኬት አለን::

818-776-8484
ሎስ አንጀለስ 310-275-7767 ዋሽንግተን ዲሲ 703 671 9175
18040 Sherman Way Suite 122 Reseda, CA 91335

# አዳም ና ሔዋን

## « መፈለግና አለመፈለግ »

ከአንዱዓለም

ሰውዬው ልጅቷን ፈቅዷታል። ወዷታል እንበል። ቀረባት አነጋገራት፤ ልጅቷ በምንም ይሁን ብቻ በምንም አልፈቀደችውም። ሰውዬው በመጀመርያ መግደርደሯ ነው ይልና ልምምጡን ይገፋበታል። እሷ ደግሞ ልምምጡ በበዛ ቁጥር "የምን መመናቸክ" ነው በሚል ጭራሽ እምቢታዋን እያጠናከረች ጭራሹኑ እሱን የማታይበትን ቦታ እየመረጠች፤ መንገድም ስታየው መንገዷን እያሳበረች ብትሸሸው አልሆን አለ። ሰውዬው እልህ ገባ። ልጅቷ ምናልባት ይረሳኝ ይሆናል ብላ ከወንድ (ከሌሎች) ጋር እየሆነች ስትታየው ጭራሽ ባሰበት። "ከማን አንሼ ነው እኔን እምቢ የምትለው?" ይልና በፊት ፍቅር የነበረው አሁን እልህም ቅናትም ውስጥ ይገባል። መንገድ ላይ እየጠበቀ ድሮ ይለማመጣት የነበረው አሁን ተቀይሮ ያስፈራራት ጀመር። ልጅቷ ብሽቀት ውስጥ ትገባና ሙልጭ አድርጋ ትሰድበዋለች። ሊመታት ከጅሎ ነበር። ግን ቂም ይዞ ሄደ። "አገኝሻለሁ " ብሎ ዛተባት። ፍቅር ፍለጋ ሄዶ ጠላት ማትረፍ ይኧል ይህ ነው። እስቲ እዚህ ላይ ቆም አድርገን ትንሽ እንመራመር። አንዳንድ ወንዶቻችን "አለመፈለግን" (Reject መደረግን) በፀጋ የማይቀበሉ እንዳሉ ሁሉ አንዳንድ እህቶቻችን ደግሞ የፈለጋቸውን ወንድ "አንፈልግም" ብለው የሚገልጹበት ዘዴ (Reject ማድረግን) በጣም ተፃራሪ ሲሆን ይታያል።"ከማን አባቷ በልጣ ነው እኔን እምቢ የምትለው" የሚል አንዳንድ ትምክህተኛ ወንድ እንዳለ ሁሉ "እንዴት አባቱ ቢደፍረኝ ነው የጠየቀኝ?" የምትል ጉረኛ ሴት እንዳለች ማወቅ አለብን። ይህን ነው እንግዲህ ጤነኛ አይደለም የምንለው። ከጥቂት ዓመታት በፊት አዲስ አበባ የተፈጸሙ ድርጊቶች እስቲ እናውሳ። ስድስት ኪሎ ድሮው ሊጋባ ቢሮ አካባቢ ላይ ጠብቆ የወደዳትን ልጅ በጩቤ ወግቶ ጓዶኛዋን አቁስሎ የጠፋውንና በኋላም ተይዞ ከታሰረ በኋላ ያመለጠው ተማሪ ትዝ የሚላችሁ አትጠፉም። ልጅቷን ወዷት ገልጾላት፣ እንደማትፈልገው ነግራው እየደጋገመ ሲጠይቃት ከጓደኞቿ ጋር ሆና ስለተሳለቀችበት በዚህ እልህ ውስጥ ገብቶ ገደላት። እንዲሁ መጽሐፍት ቤት ውስጥ ሰው በተሰበሰበበት በጩቤ ሆዷን ነድሎ የገደላትን ደግሞ አስታውሱ። የአንድ የታወቀ የዱሮ እስፖርተኛ ልጅ ነበረች። ከዚያም እዚህ አገር በተለያዩ ጊዜ ከዚሁ በመነጨ ብዙ ወንጀሎች የተሰሩትን አስታውሱ። ደግሞ በኛ ብቻ የታየ አስመስለን መገንዘብ አይኖርብንም። የትም ያለ ነው። እንግዲህ በ"ሪጀክሽን" አለመቀበልና "ሪጀክሽንን" በሥርዓት ካለመግለጽ የተደረጉ ወንጀሎች ናቸው። የስነ ልቡና ሊቃውንት ስሜትን (emotional feeling)ን በተመለከተ ብዙ ያተቱት ነገር አለ። ከሁሉ በላይ ስሜትን መጉዳት የሚያህል ጉጂ ነገር የለም ይላሉ። ስሜት ሲጐዳ በጣም ያማል። ስለዚህም ነው የሰለጠኑ ሴቶች የጠየቃቸውን ወንድ አለመፈለጋቸውን ሲገልጹለት በጣም ተጠንቅቀው፤ ስሜቱን እንዳይጐዳ ቃላት መርጠው ተለማምጠው የሚያስረዱት። አንድ ወንድ አንዷን ሴት የመውደድ መብት ማንም ሊነፍገው አይችልም። እንዴት እንዲህ ያለ ስሜት ሊያድርብህ ቻለ? ተብሎ ሊከሰስ አይችልም። ፍቅርን እሱ ራሱ ባለቤቱም ሊቆጣጠረው አይችልም። ታዲያ መወደድም እንዳለ ሁሉ አለመወደድም እንደሚኖር ወንዱ ተገንዝቦ ሴቷን ሲቀርባት "እሺ ማለት አለባት" በሚል ሙሉ ግምት ብቻ ሳይሆን እምቢ ልትል እንደምትችልም ገምቶ መሆን አለበት። ለማንኛውም የምመክረው ጉዳይ ይኖራል:-

በወንዶች በኩል:-በተቻለ መጠን አንዲት ሴት ልጅ ተጠይቃ እንቢ የማለት ሕጋዊም፣ ሕብረተሰባዊም መብት እንዳላት መገንዘብ፤ አንዲት ልጅ ወዶ ጠይቆ እምቢ ካለች በመናቅ ወይ በማንኳሰስ ነው እንቢ ያለችኝ ብሎ መገመት የለበትም። ጠያቂው ደስ የሚለው ሴት እንዳለ ሁሉ ሴቷም ደስ የሚላት፣ የምትፈቅደው ሌላ ወንድ ሊኖር እንደሚችልና የማትፈቅደው ወንድ ከጠየቃት እንቢ ማለት እንደምትችል ማወቅ ጥሩ ነው። አንዷ እምቢ ብትል ሌላዋ አለች ብሎ ማሰብ። የዛችኛዋ እምቢ ማለቷ መሬት የተደፋ አድርጎ መውሰድ ትልቅ ስህተት ነው።

በሴቶች በኩል:-አንድ የጠየቃት ወንድ የማትፈቅደው ከሆነ አለመፈለጓን ስሜቱን በማይጐዳ መንገድ በጥንቃቄ ልትነግረው ይገባል። መወደድ ማለትም ለሌላው ደስ ማለት ጸጋ ነውና በሰውዬው መጠየቅን እንደስድብ በመቁጠር ማንቋሸሽ በተለይ ከጓደኛ ጋር በሰውዬው መሳለቅ ከብልግና አልፎ አደገኛ ሁኔታ ሊፈጥር መቻሉን ማወቅ አለባት። በተለይ "እከሌ እኮ አስቸገረኝ፣ እኔ አልፈልገውም፣ አይገርምሽም" እያሉ ለጓደኞችና ለተገኘው ሁሉ ማውራትና ማስወራት ከጉራ ሌላ የሚሰጠው ጥቅም የለም። ሌላው "ጠይቆኝ እምቢ አልኩት" የሚለው አባባል ለተናጋሪው ምን ጥቅም እንደሚሰጥ ዘላለም ሲገርመኝ ይኖራል። ■

# እሱና እሷ

በአንድ የአሜሪካን ከተማ እሱ ከአገር ቤት ከመጣ ከረምረም አድርጓል። እሷ ግን ገና አንድ ዓመቷ ነው። እሷ በአንድ እስቶር ካሽር ናት። እሱ ዕቃ ገዝቶ ሊከፍል ሲል ያያታል። ኢትዮጲያዊ መሆኗን ያውቃል። ብዙ ገበያተኛ አለመኖሩ አመቺ ሁኔታ ፈጠረና ለመነጋገር ቻሉ።

እሱ:- አበሻ መሰልሺኝ
እሷ:- አዎ ኢትዮጲያዊ ነኝ
(የአገሯን ሰው በማግኘት ደስ ይላታል)
እሱ:- ___ እባላለሁ
እሷ:- ___ እባላለሁ።
እሱ:- ምነው አላየሁሽ ከዚህ በፊት፣ አዲስ ነሽ መሰለኝ።
እሷ:- ባንተ ያይ ይሆናል እኔስ ቆይቻለሁ
እሱ:- ምን ያህል ጊዜ?
እሷ:- ከአገር ቤት ከመጣሁ ዓመቴ፣ እዚህ ሥራ ከጀመርኩ አንድ አራት ወር ሆነኝ
እሱ:- ገና ነሻ?
እሷ:- ለምኑ?
እሱ:- ማለቴ ቅርብ ጊዜ ነው የመጣሽው፤
እሷ:- አንተ ቆይተሃል እንዴ?
እሱ:- አዎ አንድ አሥር ዓመት አልፎኛል። (ይኩራራል)
እሷ:- አሥር ዓመት? ብዙ ቆይተሃል?
እስ;- ቀጥታ ከአ/አ ነው?
እሷ:- አይ ሱዳን ነበርኩ
እሱ:- እንዴት ነው ታዲያ አገር ለመድሽ
እሷ:- መልመድ የት ይቀራል? ይለመዳል።
እሱ:- ከዘመድ ጋር ነው የምትኖሪው?
እሷ:- አዎን ከወንድሜ ጋር ነው፣
እሱ:- የአሜሪካን ኑሮ አላስቸገረሽም?
እሷ:- ማስቸገሩማ የት ይቀራል?
እሱ:- ብዙ ኢትዮጲያዊ አግኝተሻል?
እሷ:- አላገኘሁም፤ ጥቂት ናቸው። እኔም ሥራ ይበዛብኛል።
እሱ:- አገር የሚያለማምድሽ ታዲያ የሚያስፈልግሽ አይመስልሽም?
እሷ:- እንዴት አያስፈልገኝም፤ ወንድሜ ሥራ ስለሚበዛበት ብዙ ጊዜ የለውም፣
እሱ:- እንደዋወላ ዥንግዲህ ስልክ ቁጥርሽን ትሰጪኛለሽ?
እሷ:- (ወረቀት ላይ ጫር አድርጋ ትሰጠዋለች የሱን ግን አልሰጣትም። ለምን እንዳልሰጣት ሳይገርማት አልቀረም።)
እሱ፤- (በሁለተኛው ቀን ይደውልላታል) ታዲያስ
እሷ፤- ታዲያስ
እሱ፤- ይሽውልሽ ደወልኩ
እሷ፤- እሺ፣
እሱ፤- እንዴት እሺ?
እሷ፤- አአይ ጥሩ ነው ማለቴ ነው።
እሱ፤- ታዲያ መቼ ለመገናኘት እንችላን።
እሷ፤- እንዴት መገናኘት
እሱ፤- አለ አይደለም፣ አገር እንዳሳይሽ
እሷ፤- ምን ጊዜ አለ ብለህ ነው።
እሱ፤- አንቺ ደግሞ! እንዴት ይጠፋል
እሷ፤- እያወቅሽው፤ ሥራ ይበዛል፣
እሱ፤- ቢሆንም፤ ከልብ ካለቀሱ እምባ አይገድም።
እሷ፤- ችግር ሆኖብኝ እኮ ነው። በዚህ ላይ ያለሁበትን ሥራ አልወደድኩትም።
እሱ፤- ሽረ ሳልጠይቅሽ፤ አሳይለም ነው ያመለከትሽው?
እሷ፤- አዎን
እሱ፤- ውጤቱ ገና አልመጣልሽም አይደል?
እሷ፤- የሥራ ፈቃድ አግኝቻለሁ።
እሱ፤- ግሪን ካርድ ማግኘት አለብሽ፤ ጥሩ ሥራ ለማግኘት
እሷ፤- ለመሆኑ እንዴት ነው የሚገኘው?
እሱ፤- ደህና ጠበቃ አለሽ?
እሷ፤- ራሴ ነኝ ያመለከትኩት፤ ወንድመሜ ረድቶኝ።
እሱ፤- ምን መሰለሽ? ጥሩ ጠበቃ እንፈልግና እሱ እንዲካታታልልሽ ኣዳርጋላሁ።
እሷ፤- በጣም አመሰግናለሁ።
እሱ፤- እና ግሪን ካርድሽን እንዳገኘሽ እኔ ጥሩ ሥራ አስይዝሻለሁ፤ ok?
እሷ፤- አመሰግናለሁ በጣም፤
እሱ፤- ምን መሰለሽ እኔ እምሠራበት ማኔጀር ነኝ። እና እዚያም ቢሆን፤ ሌላም ቦታ ቢሆን ጥሩ ደመወዝ ያለው ሥራ አገኝልሻለሁ።
እሷ፤- በጣም ነው ያደከምኩህ፤ ውይ ታድዬ፣
እሱ፤- አይዞሽ፤ ታዲያ ምን አልሽ?
እሷ፤- ምኑን?
እሱ፤- እንዴ ረሳሽው እንዴ? መቼ ነው ሻይ ቡና የምንለው?
እሷ፤- እንደተመቸኝ ብደውልልህ አይሻልም።
እሱ፤- እንዴ ምን ማለትሽ ነው?
እሷ፤- ሙት ስለማይመቸኝ እኮ ነው።
እሱ፤- ስለ ሥራውም ቢሆን እኮ መመካከር ያስፈልጋል።
እሷ፤- እሱማ አዎን (ይጨንቃታል) ለምን ነገ ወይም ተነገወዲያ አልደውልልህም።
እሱ፤- ስልክ የለኝም። (ውሽቱን)
እሷ፤- እንዴ እንዴት? በአሜሪካን ያለ ስልክ
እሱ፤- ተበላሽቶ ተቋርጦ ነው።በቃ እኔው ተነገወዲያ ደውልልሻለሁ። ቻው።
እሷ፤- እሺ ቻው (ስልኩ ይዘጋል)
እሷ፤- (ማታ ወንድሟ ሲገባ የሌላ ሥራ ተስፋ እንዳገኘች ትነግረዋለች)
ወንድሟ፤- ማነው ያገኘልሽ?
እሷ፤- ___ ይባላል። ታውቀዋለህ?
ወንድሟ፤- የ___ ባል እኮ ነው።

(ለምን ስልክ የለኝም እንዳላት ገባት)

# « ተው እንተዛዘን!»

አልማዝ ገ/እግዚአብሔር (ከአትላንታ)

እንዲህ ነው ታሪኩ ውድ የአገሬ ልጆች፤ ከኢትዮጲያ ከመጣሁ አንድ አመቴን ልከናነብ ምንም አልቀረኝም። ታድያ በዚች አንድ አመት ውስጥ ያየሁት ነገሮች ተወርተው የሚያልቁ አይደሉም።ታሪኩን ሳጫውታችሁ ልብ ብላችሁ ስሙኝ።

በመጀመሪያ ከራሴ ብጀምር። ኪዩባ ነበርኩ። በልጅነቴ ሄጄ ኩባ ውስጥም ብዙ አመት ኖሬአለሁ። የሄድኩትም ለትምህርት ነበረ። ትምህርቴን ጨርሼ ወደ ኢትዮጲያ ከተመለስኩ በኋላ አንድ ጥሩ የደስደስ ያለው ልጅ እተዋወቃለሁ። ከዚያም ስለ ጋብቻ እጫውተዋለሁ። እሱም ከትንሽ መግደርደር በኋላ እሺ ይልና ቀለበት እናስራለን። ከዕለታት አንድ ቀን ወደ አሜሪካ ለመሄድ እፈልጋለሁ ብዬ መጥፎም ይሁን ጥሩ ሀሳብ አቀርባለሁ። ታዲያ ይህ ንጹህ ልብ ያለው የኔ ቆንጆ "ታዲያ ምን ችግር አለ ላንቺ ያልሆንኩ ለማን እሆናለሁ፤" ይልና ከቅርብ ዘመዶቹ ጋር ሆነው የጎደለውን ነገር አሟልተው ይልኩኛል። መቼም ልመጣ ስል የጓደኞቼ፣ የዘመዶቼ ግብዣ እንዲያው አይነሳ። አንዳንድ ጓደኞቼ "ንጹህ ልብ ስላለሽ ነው፤ ግልጽ ስለሆንሽ ነው፤ እግዜር ቢወድሽ ነው።" እያሉ ትልልቆቹም የምርቃት አይነት አዥጎድጉደው ይሸኙኛል። እኔም አሜሪካ ገብቼ ከአዲስ አበባው ኑሮ የተለየና በሰማይ ካለው ገነት ቀጥሎ የምኖር መሰለኝና ቪዛው ከተመታ በኋላ የልብ ልብ ይሰማኝ ጀመር።

ታድያ ገና ለንደን ላይ አውሮፕላኑ አርፎ ማደርያ ማደርያችን ስንይዝ ሆድ ይብሰኝ ጀመር። "ሆዴ በርታ ምንድን ነው የምታቅማማው?" እያልኩ እራሴን እያጽናናሁ አደርኩ። "እይ ምንም አይደለም እንዴ እናቶቻችን ከባሎቻቸው ተለይተው አምስት ስድስት አመት ይኖሩ የለም፤ እንኳን እኔ ለትንሽ ግዜ" ብዬ ራሴን አጽናናሁ። አሜሪካ እንደገባሁ የእጮኛዬ ወንድም ጋር አርፋለሁ። ከሱ ጋር እያለሁ አገሬ ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ይናፍቀኝ ጀመር። ጠየም ያለውን፣ እያስቆምኩ "ኢትዮጲያዊ ነህ? ነሽ?" እያልኩ እየጠየቅኩ "እዎ" ያለኝን ችግሬን ነግሬ መፍትሔው ምንድነው? ስል "አይደለሁም" ያለኝን ደግሞ ፊቴን አዙሬ ስሄድ ወደ ሁለት ወር አገባደድኩ። መቼም መንገድ ላይ የማገኘውን ሰው አስቁሜ ስጠይቅ እብድ ነሽ ወይ ሳትሉኝ አትቀሩም። የአገሬን ሰው ወገኔን የመሰለ ሳይ ደስ ስለሚለኝ፣ ብቸኝነቴ ስለማይሰማኝ ነው። ያንን ሁኔታ ያለፋችሁበት ታውቁታላችሁ።በተፈጥሮዬ ተጫዋች ሰውን መቅረብ የምወድ በመሆኔ ብዙ ሰዎች እተዋወቅና አንዳንድ የሚያስፈልጉኝ ነገሮች ይረዱኛል።ግራ የገባኝን ያስረዱኛል።

በዚህ አጋጣሚ ግን ይህን ያህል ሰው የምፈልገው የገንዘብ ችግር ኖሮብኝ ሳይሆን እራሱ የኢትዮጲያዊ ስም መጥራቱ፤ ከኢትዮጲያኖች ጋር ማውራቱ ለእኔ ከምሳና ከእራት የሚበልጥብኝ ነገር ስለሆነ ነበር። ይህ ሆኖ ታዲያ ዛሬ ያኔ ብዙ ተዋወቅሁ የምላቸው በተለይ ወንዶቹ ጥሩ ጓደኞች አገኘሁ በምልበት ወቅት ያልሆነ ነገር እኔ የማልፈልገውን ይጠይቁኝና ካልተፈጸመላቸው እየሸሹኝ በመሄድ ላይ ናቸው። እኔ ተጫዋች መሆኔ ሰውን ለመቅረብ ነው እንጂ ሌላ ፍላጐት ኖሮኝ አይደለም። በዚህ ላይ የማምነው የሚያምነኝ እጮኛ አለኝ። ለማስረዳት ስሞክር የሚቅርብልኝ ሃሳብ የሚያስገርምም የሚያናድድም ነው። ስለችግር እያወራችሁት፣ ስለ አገር መልመድ እያወራችሁት ዓይኑን የሚያስለመልምባችሁ፤ የሚያቁለጨለጭባችሁ፤ "እዚህ አገር ከመጣሽ ሴክስ አድርገሻል ወይ?" የሚል ሰው ሲያጋጥማችሁ ምን ይሰማችኋል ወገኖቼ። "እሱ የለም፤ ቢመጣመም ቆይቶ ነው፤ እስከዚያው ድረስ ታዲያ ምናለበት?" የሚሉ አነጋገሮች ሲገጥማችሁሳ? በተለይ ደግሞ አንዱማ እንዲያው አማርኛ የጠፋው ይመስል "ብስምሽ ምን ይመስልሻል? እኔ ቤት ሄደን ለምን ትንሽ አንተኛም?"አለኝ በእንግሊዝኛ። እውነቴን ነው የምነግራችሁ። ልክ የመሳምና የመተኛት ችግር አጋጥሞኝ አገር ለቅቄ የተሰደድኩ ይመስል አፍን እያሾሉ ይህንን ጥያቄ ጠይቆ መልስ ሲያጣም ልክ በጥሩ አማርኛ ያስረዳኝ ይመስል ፈገግ ፈገግ እያለ "ምናልባት እኔ እኮ ላግባሽ አላልኩም። የጠየቅኩሽን ብቻ ነው የምፈልገው፤" የሚል ሲያጋጥመማችሁ መፈጠራችሁን አያስጠላችሁም ወይ?። ባገራችን ሴት ልጅ የምወደው እጮኛ አለኝ ስትል የመጣው ጎበዝም ይቅርታ ብሎ አንገቱን ደፍቶ ወደመጣበት ይሄዳል። እዚህ "ብስምሽ ምን ይመስልሻል?" ብሎ ነገር አይገባኝም። በፊልም እንደሚታየው የ"ሥልጣኔ ምልክት መሆኑ ይሆን? እኔም በቅርብ የመጣሁ "ገገማ" በመሆኔ ምን አውቃለሁ። እስቲ እግዜር ያሳያችሁ አሁን መሳም ብፈልግ እንኳን ምን ብዬ ልመልስ ነው? "እዎ መሳም እፈልጋለሁ ነው የሚባለው ወይስ መሳም አልፈልግም ነው የሚባለው?" መልስ የሌለው ጥያቄ እየጠየቁ ሰው ማስደንገጥ ደግ አይመስለኝም። የልጂቱን ሁኔታ አይቶ አስፈላጊ ከሆነ ጠጋ ብሎ ልክክ አለበለዚያም እንዲያው በጥሩ ፈገግታ አይን አይኗን እያዩ ከዚያው ከአይን መልሱን አውቆ መደረግ ያለበትን ማድረግ ሲገባ ችግርን ተገን በማድረግ አዲስ ልጅ ነሽ ብሎ ይሄን ያህል ጋጋታ እራስን ከማቅለል አርፎ መቀመጡ ጥሩ ይመስለኛል።

በዚህ አጭር ቆይታዬ ሌላ የታዘብኩትን ወገኖቼ ላይ ያየሁትን ያልጠበቅሁትን ነገር ላጫውታችሁ። ይህቺ አገር ጥሮ ግሮ ሆዱን ሞልቶ

ቢሉን ከፍሎ እንዲኖር ታደርጋለች። ታድያ ጥሮ ግሮ የሚያድረው ራሱን አሻሽሎ ከፍ ብሎ ሲታይ በወገን በመኩራትና ደስ በመሰኘት ፋንታ እርር ድብን እያሉ ስም የሚያጠፉ ሰዎች አጋጥመውኛል። እንዲህ ከመቃጠል "እሰየው የአገሬ ልጅ በትንሽ ግዜ ኑሮው/ኑሮዋ ተሳካለት/ላት። እግዚያብሔር ረዳው/ረዳት ብሎ የደስታ ፈገግታ እንደማሳየት መመቀኛኘት፣ መተማማት በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው። "እባካችሁ የተከራየሁትን ቤት እዩልኝ ፣ ተሰባስበን እኔ ቤት አንድ ቀን ትርፍ ጊዜ ሲኖረን እንሰባሰብ የምናወጣው ወጪ ብዙ አይደለም። የምናገኘው የመንፈስ ደስታ ግን በሚሊዮን የሚቆጠር ነው።"ብላችሁ ሃሳብ ያቀረባችሁ እንደሆነ "እኔ 17 አመት ተቀምጬ 20 አመት ተቀምጬ ያላሰብኩትን ይች ገና አመት ሳይሞላት እንዲህ የምትሆነው ምን ብታገኝ ነው?" ብሎ ሊረዱ የቆሙትን ኢትዮጲያዊያኖች ማስቀየም አይሆንም? እያንዳንዳችን በሰው አገር ያለን ስለሆንን እየተረዳዳን፣ እየተሳሰብን ብንኖር ጥሩ ነው። ትብብርን ከሌሎች ዜጋዎች ብንማር ምናለ? ጭራሽ አንዳንዱማ ስለችግር መስማት አይፈልግም። ልክ በሱ ላይ ችግር የማይደርስ ይመስላል። ችግር ማለት ደግሞ የገንዘብ ብቻ አይደለም። የሀገር ፍቅር፣ የወገን ፍቅር እራሱ ኢትዮጲያዊ ከሆነ ሰው ጋር መነጋገሩ የሀገር ፍቅር ስሜት ላለው ሰው እንዴት እንደሚያስደስት የሚያውቅ ያውቀዋል። ምንም 20 አመት 30 አመት ቢቀመጡም እንግሊዘኛውን አጣድፈው ቢያወሩት "ዌር አር ዩ ፍሮም?" ከመባል አያድንም። ስለዚህ ይህንን አውቀን እንረዳዳ፤ እንሰባሰብ፣ እንመቀኛኝ። በመረዳዳት ላይ ካልተገኙ በራስ ላይ ምን እንደሚደርስ አይታወቅምና ያገር የወገን ፍቅር ያላችሁ ሁሉ አስቡበት፤ ነገሩ አሳሳቢ ነው። እኔ ችግር የለብኝም ማለት ደግሞ የሚያዋጣ አይመስለኝም። የሰው አገር ኑሮ አያስተማምንምና።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

የላንዳፍታን መጽሔት ባላችሁበት ቦታ ለማከፋፈል የምትፈልጉ የአከፋፋይ ኮሚሽን ከ20 - 25 በመቶ የምንከፍል ስለሆነ በአድራሻችን ደውሉልን ወይም ጻፉልን።

አድራሻችን፤-
LANDAFTA
P.O. Box 49301
Atlanta, GA 30359
(404)728-9122

ለውድ እህቴ እታለም - ናዝሬት
ከወንድምሽ ከወንድም ዓለም (ከሴንት ሉስ)


"በወንዶች ላይ ያለኝን ጥላቻ እንዴት አጠፋው ይሆን?" ብለሽ በ"ላንዳፍታ" መጽሔት 2ኛ ዓመት ቁጥር 2 ላይ የጻፍሺውን ታሪክ አንብቤአለሁ። እስቲ ምክር ቢጤ ስጡኝ ስላልሽ፣ የኔ ምክር ይሄውልሽ።

ከሁሉ አስቀድሜ ጓደኛሽ በደረሰባት ፍቅርና በፍቅርም ምክንያት (እርግጠኛ ከሆነ) ከዚህ አለም መለየቷ በጣም ያሳዝናል። "እርግጥ ከሆነ" ያልኩሽ ጓደኛሽ በመጨረሻ ለወሰደችው እርምጃ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ማረጋገጥ ስለማይቻል ነው። ፍቅር ይሆን? ፍራቻ ይሆን? እፍረት ይሆን፣ ወዘተ መልሱን እሷ ብቻ ነው መስጠት የምትችለው። የማንኛውም ነፍሷን ይማረው። አንቺም ነገሩን በደንብ ሳትመራመሪበት "ወንዶች ሁሉ" አስጠሉኝ ስትይ ልጅነትሽ በግልፅ ይታየኛል። ምንም እንኳን ጥሩ መጨረሻ ያላቸው ታሪኮች ብዙ ጊዜ ባይጻፉም ብዙ ወንዶችና ሴቶች የዚህኑ ዓይነት ታሪክ ያላቸውና በሰላም አንድ ላይ በመኖር ወይንም ተለያይተውም በሰላም የሚኖሩ አሉ።

አንቺም የጓደኛሽን ዕድልና ታሪክ በመመርኰዝ የራስሽን ኑሮ አታማሪ። እርግጥ እንዳልሺው "ወንዶችን በጣም እፈራለሁ እጠላለሁ" ካልሽ ነገሩን ብትመራመሪበት መልሱን አንድ ቀን ታገኚው ይሆናል።
ትልቅ ሥራ የሠራሽው ቢኖር ለሰው ማካፈልሽ ነው። ጓደኛሽም እንዳልሺው ግልፅ፣ ተጫዋች፣ ብትሆን ኑሮና ችግሯን እንዳንቺ ለሰው ብታዋይ ሕይወቷን ባላጠፋች ነበር።

ምክሬ በአጭሩ፣ ውይይትሽን ቀጥይበት፣ "ወንዶች በሙሉ" አትበይ፣ ለጥያቄሽና ለችግርሽ መልሱ የሚገኘው አንቺው ልብ ውስጥ ነውና ልብሽንና አስተሳሰብሽን ቀስ እያልሽ መርምሪው። የምታገኚውን መልስ ከሌላ ሰው ጋር ተካፈይ፣ እግዜር ብርታቱንና ብርሃኑን ይስጥሽ።

ብዙ አንባቢ ባተረፈችው
የቤተሰብ መጽሔት በ"ላንዳፍታ"
ድርጅትዎን ወይም የንግድ
ሥራዎን በርካሽ ያስተዋውቁ




# ጓ ደ ኛ ለ ሚ ፈ ል ጉ

ጓደኛ ፈላጊዎች ራሳቸውን አስተዋውቀው፣ ሊተዋወቁ የሚፈልጉትን ሰው ዓይነት የሚጠቁሙበት አምድ ነው። ስምና ትክክለኛ አድራሻ በመጽሔቱ ላይ አይወጣም። በስምና አድራሻ ፋንታ የኮድ ቁጥር ይወጣል። የኮዱን ቁጥር የምንሰጠው እኛ ነን። በስምና አድራሻ ምትክ የኮዱ ቁጥር ይወጣል። ስምና አድራሻ እኛ ጋ በምስጢር ይቆያል። ትክክለኛ ስምና አድራሻ ግን እኛ ጋ መድረስ አለበት።በጣም አጠር ተደርጐ ቢጻፍ ዕድሉን ለብዙ ሰው ማዳረስ ይቻላል።

ለመተዋወቅ የምትፈልጉት ሰው ዓይነት ወጥቶ ካገኛችሁ ቁጥሩን በመጥቀስ ደብዳቤ ጽፋችሁለት/ጽፋችሁላት አነስ ያለ ኤንቨሎፕ ውስጥ አሽጋችሁ ኤንቨሎፑ ላይ የናንተን ሙሉ አድራሻ በቀለም፣ የሚላክለትን/የሚላክላትን ሰው ኮድ ቁጥር በእርሳስ ጥጉ ላይ ጽፋችሁ በሌላ ከፍ ባለ ኤንቨሎፕ ውስጥ ከታችሁ አሽጋችሁ በአድራሻችን ትልካላችሁ። እኛም የኛን ፖስታ በመክፈት ከውስጥ ያለውን ኤንቨሎፕ አውጥተን የኮድ ቁጥር የተጠቀሰውን ግለሰብ ትክክለኛ አድራሻ ከመዝገባችን ኤንቬሎፑ ላይ በመሙላት እንልካለን። ከዚያ በኋላ እንደፍጥርጥራችሁ።

## የሚከተሉትን መመሪያዎች በደምብ አጢኑ።

1ኛ. ለፖስታና ለአገልግሎት አከፋፈሉ በሚቀጥለው ዓይነት ይሆናል፤
- ከአሜሪካ - $5.00 (በmoney order)
- ከካናዳና አውሮፓ - $6.00 (በአሜሪካ ገንዘብ፣ money order)
- ከኢትዮጵያ - ምንም አይከፈልም።
- ለ"ላንዳፍታ ቋሚ ደምበኞች (subscribers) (ላንዳፍታ ማዘዣ ቅጽ ሞልታችሁ ክፍያ የላካችሁ) $4.00 ብቻ ነው።

2ኛ. ዕድሜአቸው ከ18 በታች ለሆኑ ይህ አገልግሎት አይሰጥም።
3ኛ. ይህ አምድ ዓላማው መተዋወቂያ መድረክ ለመፍጠር ብቻ መሆኑን መግለጽ እንወዳለን።
4ኛ. እባካችሁ እንዲጻፍላችሁ የምትፈልጉትን ነገር አሳጥሩት።
5ኛ. በመጀመሪያ የብዕር ጓደኝነትን በማጠንከር የበለጠ መተዋወቅን እንመክራለን።

## አዲሱ አድራሻችን፤

LANDAFTA
P.O.BOX 49301
ATLANTA, GA 30359

---

## ከአንድ አንባቢ የተሰጠ አስተያየት፤

የቀድሞው አኩሪ ባህላችን ወጣት ወንዶችና ሴቶች ተገናኝተው የሚተዋወቁበት መድረክ በየብሔረሰቡ ባህል አዘጋጅቷል። የአሁኑ የተበረዘ ባህላችን ደግሞ በዘመናዊነት (ምዕራባዊ)ና በኢትዮጵያዊ ይሉኝታና ዓይን አፋርነት መሐል ተንጠልጥሎ ከሁለት የወደቀ ዛፍ ሁነናል። እንደ ነጮቹ በየመዝናኛው ሥፍራ መገናኘትና መተዋወቅ ያስቸግራል። በጉዞ ላይ፣ በመሥሪያ ቤት፤ በት. ቤትና በሰፈር አካባቢ ባጋጣሚ ከመገናኘት ውጪ ሌላ አማራጭ የለንም። "ላንዳፍታ" ጥንቃቄ በተመላበት ዘዴ (አድራሻችንና ስማችንን ሳያጋልጣ) ጓደኛሞች እንዲገናኙ መድረክ በመክፈቱ ከማድነቄም ሌላ አመሰግናለሁ። ታዲያ በዚህ በኩል ግኑኝነት በማድረግ የሰመረላችሁ (እኔም ልሆን እችላለሁ) "ላንዳፍታ"ችንን ለማሳደግ ምን አስበናል ወይስ ጓደኞችንን እንዳገኘን ዝም እንላለን?

# ጓደኛ የሚፈልጉ ሴቶች

---

ስም 1051፤ ዕድሜ 28፤ መኖርያ ዩናይትድ ስቴትስ፤ የትምህርት ደረጃ B.Sc. ዲግሪ፤ የቀይ ቆንጆ፤ ጸጉረ ረዥም፣ መካከለኛ ቁመት። አልጠጣም አላጨስም። መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ፤- ዕድሜው ከ30 - 43፤ የማይጠጣ፤ ፓርቲና ጭፈራ በጣም የማይሄድ፤ ታማኝ፤ደግ፣ ግልጽ፣ ትምህርት ደረጃው ከኔ እኩል ወይም በላይ፤ ልጅ የሌለው፣ ያላገባ። (በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ።)

---

---

ስም 1052፤ ዕድሜ 28፤ መኖርያ አዲስ አበባ፤ የቀይ ዳማ፤ ትምህርት 1ኛ ዓመት ዩኒቨርሲቲ አሁን ግን ያቋረጥኩ፤ በግል ድርጅት ውስጥ የምሠራ፤እምነቴ ፕሮቴስታንት፣ጸሎት ቤት መሄድ፣ መዝሙር መስማት እወዳለሁ። መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ የተማረ፣ ክርስትያን፣ ዕድሜ ከ30 በላይ፤ ቁመቱ መካከለኛ፣ ጌታን የሚወድ፣ ለሰዎች ዝቅ የሚል፤ ተጫዋችና ቁምነገረኛ፣ እግዚአብሔርን የሚፈራ፤ ለዘላቂ ትዳር። (በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ።)

---

---

ስም 1053፤ ዕድሜ 22፤ መኖርያ አዲስ አበባ፤ መልኬ ቀይ፣ ጸጉሬ መካከለኛ፣ትምህርቴ ኮምፒውተር ሳይንስ፣ የምሰራው E.C.A. መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ፤ ዕድሜው ከ35-40 ለኔና ለሱ የሚያኖር ተመጣጣኝ ሥራ ያለው፤ መልከመልካም (በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ።)

---

---

ስም 1054፤ ዕድሜ 29፤ መኖርያ አዲስ አበባ፤ ትምህርት ጨርሻለሁ፣ መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ፤ ንጽሕና በጣም ወዳ፲ሁ፤ መዝሙር መስማት፤ ጊዜን በፕሮግራም መምራት ወዳለሁ። መጥፎ ልምድ የለኝም። አልጠጥም አላጨስም፤ መልኬም ቆንጆ ነው። ተመሳሳይ ባህሪ ያለው፣ የኔን ባህርይ የሚወድ ለዘላቂ ትዳር መተዋወቅ እፈልጋለሁ። (በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ።)

---

---

ስም 1055፤ ዕድሜ 24፤ መኖርያ አዲስ አበባ፤ መልኬ ጠይም፣ ጸጉሬ አጭር (ፓንክ)፣ትምህርቴ 12ኛ ጨርሻለሁ፤ሥራ በመፈለግ ላይ ነኝ።. መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ፤ ዕድሜው ከ35-40፤ ጠየም ወይም ጠቆር ያለ፤ መካከለኛ ውፍረት ያለው ወንዳ ወንድ፤ እኔንና እሱን የሚያኖር ደመወዝ ያለው ተመጣጣኝ ሥራ ያለው፤ (በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ።)


---

# ጓደኛ የሚፈልጉ ወንዶች

---

ስም 1056፤ ዕድሜ 23፤ መኖርያ አዲስ አበባ፤ እሰራለሁ፤ አላገባሁም። ሥራዬን እወዳለሁ።ታማኝና ግልጽ ነኝ። በቡድን ሽርሽርና የእግር ጉዞና እስፖርት ወዳለሁ፤ መተዋወቅ የምፈልጋት ሴት የማታጨስ፣ ዕድሜዋ ከኔ ያነሰ፣ አሜሪካ፣ አውሮፓ ወይም ኢትዮጲያ የምትኖር፤ ጥሩ ጠባይ ያላት፤ (በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰሽ ጻፊልኝ።)

---



# እስፖርት



## የሚደነቅ እስፓርተኛና ደራሲ ወጣት!



ወጣት ብሩክ ታደሰ

የ18 ዓመት ወጣት ነው። የደራሲነት የሰዓሊነትና የእስፖርተኛነት ችሎታ አለው የሚል ወሬ ሰማን። ሮድ አይላንድ በተካሄደው ዓለም አቀፍ እስኮላር አትሌት ጌምስ የኢትዮጲያን ወጣቶች ወክሎ አራት የወርቅና አንድ የብር መዳሊያ ያገኘ ወጣት ነው ሲሉን በቀጥታ ያለበት ከተማ ደውለን አድራሻውን አገኘን። ብሩክ ታደሰ ይባላል። ጉባ በሚገኘው የባቱ ተራራ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ያጠናቀቀው ይኸው ወጣት አትሌት ሰዓሊና ደራሲ ብሩክ ከዚህ ችሎታዎቹ ሌላ በጣም ብዙ የብዕር ጓደኞች (pen freinds) ጋር በአለም ዙርያ በመጻጻፍ ታዋቂነት አለው። ብሩክ አለበት ከተማ ቦስተን ደውለን አገኘነውና ጥያቄዎች አቀረብንለት።

ላንዳፍታ:
የተሳተፍክባቸውንና ያሸነፍክባቸውን ውድድሮች ብትገልጽልን

ብሩክ:-
1ኛ. በ21 ኪ.ሜ. ግማሽ ማራቶን አንደኛ የወርቅ
2ኛ 2,500 ወጣቶች በተሳተፉበት የጎዳና
5,000 ሜትር ሩጫ ሁለተኛ በመሆን የብር
3ኛ. በሥነፅሁፍ አንደኛ በመሆን የወርቅ
4ኛ. በሥዕል አንደኛ በመሆን የወርቅ
5ኛ. በ10,000 ሜትር አንደኛ በመሆን የወርቅ
ሜዳሊያዎች ተሸልሜአለሁ።

ላንዳፍታ:-
ለውድድሩ እንዴት ልትመጣ በቃህ?

ብሩክ:-
በውድድሩ ኢትዮጲያ እንድትሳተፍ በባህልና እስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ግብዣው ይመጣል። ውድድሩ ከ 16 - 19 ዓመት ዕድሜ ባላቸው ወጣቶች መሐል የሚካሄድ ስለሆነ ዕድሉ ለት/ቤቶች ይሰጣል። ት/ቤቶች ሁሉ ጣምራ ችሎታ ያላቸውን ወጣቶች በመመሪያው መሠረት መርጠው ይልካሉ። መመሪያው ከችሎታዎቹ ባሻገር በትምህርት ችሎታቸው ከክፍል ከ1-10 ከወጡት መሃል ይላል። በባህል ሚ/ር በፌዴሬሽንና በት/ሚኒስቴር የተወዳዳሪ ግለሰቦች ችሎታና ዶኩሜንት ከተለካና ከተመረጡ በኋላ ለመጨረሻ ማጣሪያ ወደ አሜሪካ ለውድድሩ አዘጋጆች ተላከና በመጨረሻ የመረጠን ሮድ አይላንድ ያለው የዚሁ የአለም አቀፍ እስኮላር አትሌት ጌምስ አዘጋጅ ክፍል ነው።

ላንዳፍታ:- የመረጠን ስትል ሌሎችም ተወዳዳሪዎች መጥተው ነበር?

ብሩክ:-
አዎ የመጣነው ሦስት ነበርን። ሁለቱ ወደ አገር ቤት ተመልሰዋል።

ላንዳፍታ:-
አንተ ቀርተሃል ማለት ነው?

ብሩክ:-
አዎን ቀርቻለሁ። አሁን ብዙ ኮሌጆች የጠየቁኝ ስለሆነ ለኮሌጆች የሚያበቃኝን ዝግጅት ጨርሼ (TOFFL) ጥሩ የሆነ ኮሌጅ ገብቼ ትምህርቴን በበለጠ ለመቀጠል እፈልጋለሁ። ልመጣ ስል በጣም ችግር ገጥሞኝ ስለነበረ ብመለስ ችሎታዬን ወደፊት ለማዳበር ጥሩ ዕድል አላገኝም የሚል ፍርሃት ስላደረብኝ ነው።

ላንዳፍታ:-
እስቲ ስለዚህ ውድድር ትንሽ አስረዳን፣ በየስንት ጊዜው እንደሚካሄድ ጭምር፤

ብሩክ:-
ይህ የአለም አቀፍ እስኮላር አትሌት ጌምስ



ብሩክ፤ ከበላይነህ ዴንሳሞ፤ መሐመድ ከድርና እሼቱ ቱራ ጋር

---

የሚካሄደው በየአራት ዓመቱ ነው። ይህ የመጀመሪያው ነበር። በ1997 የሚቀጥለው ውድድር አትላንታ ከተማ ይካሄዳል፣ ዋናው ኦሎምፒክ በተካሄደ በዓመቱ።

ላንዳፍታ:-
ወደ ቅድሙ ብመለስ፤ ችሎታዬን ለማዳበር ዕድል አይኖረኝም የመጣሁት በችግር ስለሆነ ብለሃል፤ ምን አይነት ችግር ነው የገጠመህ?

ብሩክ:-ነገሩ ብዙ ነው። በመጀመሪያ ነገር አገሬን ወክዬ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስወዳደር የእስፖርት ኮሚሽን የመጓጓዣና የመሳሰሉትን ወጪዎቼን ይችለኛል ብዬ ነበር። በመጀመሪያ ሮተሪ ክለብ እስፖንሰር ያደርግሃል ተብዬ ነበር። ኋላ ግን የገንዘብ እጥረት አለብኝ አለ። ነገር ግን ከኔ ጋር አብረው የመጡት ሌሎቹ ሁለቱ ፌዴሬሽኑ ሲከፈልላቸው እኔን ለአንተ የለንም "ከፈለገ ትምህርት ሚኒስቴር ይቻልህ በማለት ቀርቼ ነበር። በጣም ነው የተጉላላሁት። ኋላም የደረሰብኝን ችግር በይፋ አውጥቼ ሄራልድም ላይ ተጻፈ፤ የኢትዮጲያ አየር መንገድ እስከ ለንደን እንደሚችለኝ ገለፀልኝ።

ፌዴሬሽኑ እኔን መርዳት በፍፁም እንዳልፈለገ ያወቅሁት ቀደም ሲል ለላብ መተኪያ በልምምድ ወቅት የሚያስፈልገኝን አገር ወክዬ ስለምወዳደር መስጠት የሚገባውን "ከአካባቢያችሁ ተመርጦ የመጣው ብሩክ ታደሰ ለውድድሩ ስለተመረጠ የላብ መተኪያ ወጪውን እንድትችሉት ብሎ ፌዴሬሽን ለክፍለ ሀገሩ ቅርንጫፍ፤ ክፍለ ሀገሩ ለምኖርበት ቀበሌ (ባሌ) ድረስ ሲጽፍ ነው። በመጨረሻም ጊዜው ደረሰና እኔም በቃ ቀረሁ ስል የሮታሪ ክለብ ሊቀመንበር በነገሩ አዝነው አለሁበት ድረስ ምሽት ላይ መጥተው $5,000 ክራሴ ነው ብለው ሰጡኝ። እኔም ማምሻውኑ ቲኬቱን ከአየር መንገድ አስቆርጬ በነጋታው በረርኩ።

ላንዳፍታ:-
ሌሎቹ እንዴት ሊከፍልላቸውና ላንተ እንዴት ላይከፍል እንዳልቻለ የተረዳኸው ነገር አለ?

ብሩክ:-
መረዳቴማ እንዴት ይቀራል? በችሎታም ሆነ በሁሉ ነገር ከነሱ እበልጣለሁ። ማሸነፌ ራሱ ምስክር ነው፤ እነሱ የሆኑትን ግን እኔ አይደለሁም የምናልባት አንድ ነገር ብቻ ነው። እነኚያ ሁለቱ ኤርትራዊያን መሆናቸውን አውቄአለሁ። ስማቸውንም ለመግለጽ እወዳለሁ። አንደኛው ሳሙኤል ወ/ገብርሔል ሁለተኛዋ ሩት ተክለ ይባላሉ። ቅድም እንዳልኩት እነሱ ተመልሰው ሄደዋል።
ላንዳፍታ:-
ሌላ ያጋጠመህ ችግር ነበር?

ብሩክ:-
አዎ። አገሬን ወክዬ ስወዳደር ካሸነፍን የምናውለበልበው ሰንደቅ ዓላማ እንጠይቅ ብዬ አብረውኝ የሚሄዱትን ብጠይቅ "ኤድያ" ቢሉኝ እኔ ብቻዬን ጠይቄ ከብዙ ጭቅጭቅ በኋላ የሚውለበለብ ሳይሆን ትንሽ አንበሎች የሚቀያየሩት ዓይነት ተሰጠኝ። እዚህ መጥቼ የመጀመሪያውን ውድድር እንዳሸነፍኩ አብረውኝ ተወዳድረው 2ኛና 3ኛ የወጡት የአገራቸውን ሰንደቅ ዓላማ ሲያውለበልቡ እኔ ስላልነበረኝ መሸለምያ እስቴጅ ላይ ስወጣ አለቀስኩ። ሂጂ እንዳልገዛ አገሩን አላውቅ። በኋላም እዚሁ ውድድሩ ላይ የተዋወቅሁት የብራዚል ወጣት ከውድድሩ በኋላ ሂዶ ፈልጐ ገዝቶ መጣልኝ። ከደስታ ብዛት እንባዬ አቀረረ። በኋላም ለመታሰቢያ ከዚሁ የብራዚል ተወዳዳሪ ጋር የአገሬን ባንዲራ ለብሰን አብረን ፎቶ ተነሳን። አገሬን ወክዬ ተወዳድሬ ሳሸንፍ አገሬን የማስተዋውቅበት ባንዲራ የማይሰጠኝ ምክንያቱ ምንድነው?

ላንዳፍታ:-
ለአገርህና ለባንዲራህ ያለህን ፍቅር በጣም እናደንቃለን። ሌላ የምንጠይቅህ ስለ የብዕር ጓደኞችህ ነው እስቲ ስለሱ አጫውተን።

ብሩክ:-
የብዕር ጓደኛ (pen freind) ጋር መጻጻፍ የምወደው ነገር (hobby)ዬ ነው። ባሌ እያለሁ ከ36 የብዕር ጓደኞች ጋር በዓለም ዙርያ እጻጻፍ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ ከ118 የዩኒቨርሲቲ የባህል ተቋሞችና የእስፖርት ፌዴሬሽኖች፣ ኩባንያዎች ጋር እጻጻፍ ነበር። International Youth Service የተባለው ድርጅት ባዘጋጀው የደብዳቤ መጻጻፍ ብዛት ውድድር 153 ቦታዎችና በርካታ አገሮች በመጻጻፍ የዓለም የወጣቶች ደብዳቤ መፃፃፍ 3ኛ ሪከርድ በmarch 1993 ይዣለሁ። ቴምብሮች ፊላቴሊክ በመሰብሰብ በሀገራችን የቴምብር መሰብሰብ ዝንባሌ ወጣቶቻችን እንዲለምዱት ሳበረታታ ነበር። "አረንጓዴው የብዕር ጓደኛ "በሚል መጠሪያ በባሌ ጐባና በአ/አ ቅርንጫፍ ያለውን ክለብ አቋቁሜ ክለቡ ከ3,000 በላይ ለሆኑ ወጣቶች የብዕር ጓደኛ እንዲያገኙ አገልግሎት በመስጠት ላይ ነው።



ብሩክ ከብራዚሉ ጓደኛው ጋር የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ለብሰው

ላንዳፍታ፤-
እናመሰግናለን ብሩክ። በመጨረሻ የምትለው ነገር ካለህ?

ብሩክ፤-
አለኝ። በ1994 በቦስተን ማራቶን ስለምወዳደር እኔን እስፖንሰር ለማድረግ፣ በሃሳብም ሆነ በሞራል ለመደገፍ፣ ባለኝ ችሎታ ሁሉ ተሳትፌ ኢትዮጵያን እንዳስጠራት የምትፈልጉ ሁሉ ከኔ ጋር ደብዳቤ ለመጻጻፍ የምትፈልጉ ሁሉ በዚህ አድራሻ ጻፉልኝ።


Biruk Tadesse
P.O.Box 748
Boston, MA 02123


---

በሮድ አያላንድና በኢትዮጵያ ጋዜጦች ስለ ብሩክ የተጻፋውን ተመልክተናል። በተጨማሪም ፌዴሬሺኑና እሱ፤ ፌዴሬሺኑም ለክፍለሀገሩ፤ በጠቅላላ ስለሱ ጉዳይ የተጻጻፉባቸውን ደብዳቤዎች ቅጂ ቡሩክ ልኮልን ተመልክተነዋለል። በፌዴሬሽኑ ላይ ያቀረበውን ቅሬታ በሰፊው ተከታተልንና የአሜሪካው ድምፅ ሬዲዎ የአማርኛ ፕሮግራም በስልክ የኢትዮጲያን ፌዴሬሽን እስፖርቶች መምሪያ ሀላፊን አቶ ስብሃት በላይን ስለዚሁ ጉዳይ የጠየቀበትንና ያገኘውን የአቶ ስብሃት መልስ ያለበትን የቴፕ ቅጂ አገኘን።

አቶ ስብሃት በትራንስፖርቱ ወጪ በኩል ለምን እንዳልተቻለ ለቀረበላቸው ጥያቄ "የሱ ጉዳይ እኛን ሳይሆን የሚመለከተው ትምህርት ሚኒስቴርን ነው። በኛ በኩል የምንችለውን ሁሉ አሟልተናል።" ብለዋል። ሰንደቅ ዓላማን በተመለከተ ላቀረበው ቅሬታ የሰጡት መልስ "በመሠረቱ ሰንደቅ ዓላማ አስፈላጊ መሆኑን ብናውቅ ኖሮ እንሰጠው ነበር 2ኛ አሜሪካን የኢትዮጲያ ኤምባሲ አለ፤ እዚያም ሊጠይቅ ይችል ነበር፣ እሱ ያስፈልገኛል ብሎ እኔን አልጠየቀኝም፣ የጠየቀው ማንን እንደሆነ አላውቅም፤" በማለት መልሰዋል። "አስፈላጊነቱን እንዴት ፌዴሬሽኑ አያውቅም፤ በዚሁ ላይ ኤምባሲው ያለው ዋሺንግተን ዲሲ፣ ውድድሩ ሮድ አይላንድ እንዴት አድርጎ እንግዳ የሆነ ሰው በምንስ ወጪ ዲሲ ሄዶ ሊጠይቅ ይችላል?" ብሎ የሬዲዎ ዝግጅቱ ክፍል ላቀረበላቸው ጥያቄ "ሃላፊነቱ፤ ይህን ሁሉ ማሟላት የነበረበት ት/ሚኒስቴር ነው። ይህ ያስፈልግሃል ይህ አያስፈልግህም የሚለውን መጨረስ የነበረበት ትምህርት ሚኒስቴር ነው" በማለት በደፈናው መልስ የሰጡበትን ቃላቸው ያለበትን የቴፕ ቅጂ አግኝተናል። አቶ በላይ ስብሃት "ስለ ሌሎቹ ወጣቶች አላላክ ለቀረበላቸው ጥያቄ "እነሱ የተላኩት በፌዴሬሺኑ ስለሆነ ወጪያቸውን ፌዴሬሺኑ ችሏል።" በማለት መመለሳቸውን ልናረጋግጥ ችለናል። ትምህርት ሚኒስቴር የሚለውን ደግሞ ለመስማት እንጓጓለን።

#  የአበው ቅርስ 

ይህ አምድ በአማርኛ የተደረሱ ቅኔዎችን፣ ተረትና ምሳሌዎችን፤ ፈሊጦችን፤ የዘፈን ግጥሞችን፤ እንቆቅልሾችን፤ እንካ ሰላንቲያዎችንና የመሳሰሉትን፤ በተለይም ከአባቶቻችንና ከእናቶቻችን የወረስናቸውን፣ እንዳይረሱ የምንዘግብበት፣ የተረሱንን እንድናስታውሳቸው የሚረዳን መድረክ ነው። አንባብያን በየመዘክሮቻችሁ ያከማቻችሁዋቸውን ቅርሶች በመላክ እንድትተባበሩን እንጠይቃለን። ከአገር ርቀን ላለን ባህላችንን ጠብቀን የምናስከብርበት፣ አባት እናቶቻችንን የምናስታውስበት፣ የቋንቋቸችንን ምጥቀት እየተረዳን የምንኮራበት ነውና። ቀደም ላሉት እትሞች፤ ለዚህኛውም አስተዋጽዖ ላደረጋችሁ ሁሉ በአንባብያን ስም ምስጋናችንን እናቀርባለን።

---

## ቅኔ አዘል ግጥሞች

ከጥንት መጽሐፍ የተወሰዱ

1. ውብ አገሬ ኢትዮጲያ ጥሩ እህል አብቃይ፣
   ወይንና ትርንጐ አልደረሰም ውይ?
   ትርንጐውን በላው ጉልበት ያለሰው፣
   ወይኔን ይዤ ቀረሁ እኔ ደካማው።

2. በስተሰሜን በኩል ትንሽ ዝናም ካፋ፣
   ዘር ያሳችሁ ዝሩ የኔ ዘሬስ ጠፋ።

## ተረትና ምሳሌዎች

1. የሌባ ትርፉ ጥፋቱ።
2. ሲያዩት ያምር ሲይዙት ያደናግር።
3. የዘመድ ጥል የስጋ ትል።
4. ከስስታም አንድ ያንቀው፤ አንድ ይነቀው።
5. አንድ ቀን ቢስቱ ዓመት ይፀፀቱ።
6. ብልጥ ለብልጥ አይን ብልጥጥ።
7. እየፈጩ ጥሬ።
8. ያሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ።
9. ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል።

## እንቆቅልሽ ምን አውቅልሽ?

1. በጎታ ሙሉ ጦር

2. ዓይኑ ያየውን በእጁ የሚለቅም

3. ከእናቷ ሆድ ወጥታ በርግጫ ትማታ

4. ሁለት ወንድማማቾች እኔ እቀድም እኔ እቀድም
   ጎራውን ዞሩት

5. ከዋና ሲወጣ ፀጉሩ የማይረጥብ

## ሚስትና ጎባን

ከመዝገቡ ዘመን (ጉንደር)

ሚስት፤–

ጥጡ ያንቺ ቢሆን እንዝርቱ የኔ ነው፤
ቶሎ ቶሎ ብለሽ ብትለቂልኝ ምነው?
የገደሊት አቦ የገደል የገደል፣
በሽታ የለም ወይ ጉባን የሚገድል።

ጉባን፤–

እግሯን አትታጠብ መስታወት አታይ፣
የሷን ባል ቢቀሙ ኩነኔ አለወይ?

ሚስት፤–

እግሬን ባልታጠብ መስታወት ባላይ፣
የልጆቼን አባት ልትቀሚኝ ነወይ?

ጉባን፤–

እንጨትም አልለቅምም በረሀም አልወርድ፣
ያች ቡልቡላ ሚስትህ በንዴት ትንደድ።
እንዳይደርቁ ጉመን ስትንከረፈፊ፣
ወሰድኩት ባልሽን ከእንግዲህ እረፊ።
አትበይ ቀናሁ ቀናሁ ይሉሻል ቲናዳጅ፣
አታገኚምና ሰው ያልነካው ወዳጅ።
ዝናብ እንደመታው አሞራ ስትንከረፈፊ፣
እንዳልፈላ ጠላ ስትኩረፈረፊ፣
ወሰድኩት ባልሽን ከእንግዲህ እረፊ።

ሚስት፤–

ውሰጂው ውሰጂው ውሰጂው ሳላይ፣
የውሽ ዳረጉት ጥዬ አላውቅም ወይ?

ጉባን፤–

ባልሽ እኔን ወዶ አንቺ እኔን ጠልተሽ፣
እንደ ሽሮ ዱቄት ክንብል ያድርግሽ፤
በገዛ መጠጊያሽ በገዛ ጀንዲሽ፣
እጥፍ ጭምቅ አርጐኝ ሲስመኝ ባልሽ፣
እኔስ እረሳሁሽ ከነመኖርሽ።

ሚስት፤–

ከዓሣ መረቅና ከዱባ መረቅ፤
የሚጣፍጠውን እሱ ይጠየቅ።

# ለዚነት ሙሃባ መታሰቢያ

ወርቃፈራሁ ጌታሁን (ከቀራኒዮ መድኀኒዓለም)

ወደ ጀነት፣ ይድረስ ለዚነት ሙሃባ፣
"ከንበል ደፋ ይላል ጉፈሬው፣"
እያልሽ ስታዜሚ ስታንጎራጉሪው፣
አበባዋ ዚነት ከንበል ደፋ አልሽው፣
በጉፈሬው ፋንታ እንቺው ተተካሽው።
በሞቴ ብለሽ ስታዜሚለት፣
እንቺው እራስሽ ሙትት አልሽለት።
እዬ ዚነት ሙሃባ፣
ለጋዋ ወጣት አበባ።
"አንተ ጉብል አንተ ጉብል ሎጋ፣
ወርደህ ከማማው ላይ ቁጭ ብለን እናውጋ፤"
ብለሽው ነበር ዚነት ወጉ ተወጋ።
ባያጋጥምሽ ትልቅ አደጋ፣
ወጉስ ነበር የሚወጋ?
...ዚነት...ዚነት...
የሙዚቃዋ እመቤት
ስመ ጥር ድምጻዊት
ዋይ፡ ዋይ፡ አንተ ሞት
ካላጣሽው እሷን ትጉትት?
ፍቅር ይዟት ከአይናማ
በናፍቆት ተይዛ ታማ
ሳትጨርስ አረፈች ዚነት አበባ! ሙሃባ!
መሬቱ ይቅለላት ይሁን ገለባ
ምናለ ደሴ ምናለ ገራዶ?
ምንስ አለ ዳውዶ?
አቅፎ ይዞሽ እንቺን ወዶ።
ሐይቅ ምናለ?
አጣሪት ገንዳ ምናለ?
በቃ ተከተተ ደሴ ጭር አለ፤
አምሮበት ተውቦ እየዋለ፣
የሞት ኃይል አሸነፈ አየለ።
ኸረ ዚነት ደሴን በረደው፣
ማን ይቀፍ ማን ያሙቀው?
አንቺ ነበርሽ ዘዴውን የምታውቂው፣
ኸረ ደሴ ደሴ እያልሽ፣
ገራዶን ከወዲህ
ሐይቅን ከወዲያ አሳብረሽ
አሻግረሽ ከደቡብ ቦረና ና ብለሽ
ዳውዶን አስከትለሽ፣
"ተከተል ጉፈሬ ተው ምታ" እያልሽ፣
እስክስታው ሲቀልጥ ሆታው ሲሞቅልሽ።
ስትጠፊ ምናለ ኩታ በር ጭረቻ፣
አምባሰል ውጫሌ አልብኮ ኮምቦልቻ።
ተኩለደሬ ወረኢሉ ቃሉና መርሳ፣
እስቲ አልቅሱላት ሞቴና ዑርጌሳ፤
ዋይታችሁን ሰምታ ድንገት ብትነሳ።
መተኪያ ሌላ የማይገኝልሽ፣
ወደር አቻ የሌለሽ፣
ዚነት መሬት ይቅለልሽ።
ዋ! ዋ! ብዬ ልለይሽ፣
"ዋ!ዋ! ብሎ መለየት በአንተ
ያምራል" እንዳልሽ፤
አስቤ አስታውሼ የተቀኘሁልሽ፤
ወርቃፈራሁ ነኝ የሙያ አፍቃሪሽ።

# የዘፈን ግጥሞች

አወሉን ጠጥቼ ተውሁት ቡናሽን፣
ተይኝ አላልኩም ወይ ሁለተኛሽን።

ነጠላ ነው ልብሴ አላልሺኝም ወይ፣
ደርበሽ አገኘሁ አሮጌ መሳይ።

ታናሽና ታላቅ ሳለ ተቤታቸው፣
ልብ ብቻ መስረቋ ለምን ነው ልጃቸው።

ጉብል ስታበጥር ዶሮ እየበላባት፣
እሺ ስትል ጊዜ እንዴት አማረባት።

ከደንጊያ ላይ ደንጊያ ከዚያ ላይ ወፍ አለች፤
መውደድ አመንምኗት እንደኔ ሁናለች።

አጭር ነው ይሉታል ዕድሜያቸው ይጠር፣
ኮረሪማ አይደለ ወጥ የሚያሳምር።

ተረረም ተረረም ከለመደ ሴቱ፤
ድስትና ጉልቻ በደህና ሰንብቱ።

ትልቁን አጉዛ ሸጠችው ለብር፣
ትንሽ ልምድ አመጣች የማያኗኑር።

(ከዚህ ከአሜሪካን የተገኘ)

How are you አለችኝ በእንግሊዝኛ፣
እንደምነሽ አልኳት እኔም በአማርኛ፤
ቋንቋችን አንድ ሆነ አልጋ ላይ ስንተኛ።

# ቢስቁም ባይስቁም

## አለቀብና!

ሴትዮዋ ባሏ ስለታሰረ እንዲፈታላት የከተማውን ሹም ትማጠናለች።

ሹሙ፤

ባልሽ ምን አጥፍቶ ነው የታሰረው?

ሴትዮዋ፤

ከዳቦ ቤት ዳቦ ስለሰረቀ።

ሹም፤

ባልሽ እንዴት ነው? ለመሆኑ ጥሩ ባል ነው?

ሴትዮዋ፤

ምን ጥሩ ነው? ይጠጣል፣ አምሽቶ ይገባል፣ ቁማርተኛ ነው፤ በዚህ ላይ ሲገባ ልጆቹን ይደበድባል።

ሹም፤

(በመገረም) ታዲያ እንዲህ ያለው ባል ተፈትቶ ቤት ቢገባ ምን ይጠቅማል?

ሴትዮዋ፤

ዳቦ አለቀብና።

## አንድ መደብር ውስጥ የተሰቀለ ማስታወቂያ

"ከሞት በኋላ ሕይወት መኖሩን ለማረጋገጥ የፈለገ ነው ከዚህ ቤት ዕቃ መሥረቅ የሚያምረው።"

## አርቆ አሳቢው

ከከተማ ውጪ የሚሄድ አውቶቢስ ማመቆሚያ ነው። አንድ ወጣት አንዱን እድሜያቸው ጠና ያለውን አውቶቡስ የሚጠብቁ ሰው ሰዓቱ እንንት እንደሆነ ይጠይቃል።

"ሰዓቱ ስንት እንደሆነ አልነግርህም" ይሉታል ሰውዬው "ለምን? ምናለበት?" ይላቸዋል ወጣቱ። "ለምን እንደማልነግርህ ማወቅ ትፈልጋለህ? ቀላል ነው። ሰዓት ከነገርኩህ ታመሰግነኛለህ። ምስጋና ስታቀርብልኝ ምን ዓይነት ጨዋ ልጅ ነው ብዬ በአውቶቡሱ ስንጓዝ ጨዋታ እጅምራለሁ። ከአንተ ጋር ጨዋታው ይደራና በመካከላችን ጥሩ መግባባት ይፈጠርና ከተማችን ስንደርስ እቤቴ እራት እጋብዝህ ይሆናል። ከዚያም የደረሰች ልጄን ትተዋወቃታለህ፣ ላውጣሽ ትላትና ታወጣታለህ። ፍቅር ይይዝህና ላግባሽ ትላታለህ። እሷም እሺ ትላለች። አየህ እንግዲህ እኔ ደግሞ ሰዓት እንኳ የሌለው ሰው ልጄን እንዲያገባ አልፈልግም" ይለዋል።

## አይ 84

ዋሺንግተን ዲ ሲ የሆነ ነው አሉ። አንዱ የአገራችን ሰው I 84 በተባለ ጐዳና ላይ በ84 ፍጥነት ይነዳና ፖሊስ አባሮ አስቁሞ ይይዘዋል።

ፖሊስ፤– በምን ያህል ፍጥነት እንደምትነዳ አውቀኸዋል?

ነጂው፤– አውቃለሁ። በ84 ፍጥነት ነው።

ፖሊስ፤– ከተወሰነው ፍጥነት በላይ ነው 84፤

ነጂው፤– የተወሰነው ፍጥነት ስንት ነው ልትል ነው?

ፖሊስ፤– 55 ነዋ!

ነጂ፤– እዛ የተለጠፈው ታዲያ ስንት እንደሚል አይተሃል? (አሸናፊነት እየተሰማው)

ፖሊስ፤– የቱ?

ነጂ፤– ያ ነዋ 84 የተጻፈበት

ፖሊስ፤– (በመገረም) በል ተወው! እንኳን ብቻ ወደ I 494 አልሄድክ፤ ለዚህኛው ግዴለም

ሰውዬው ከልጅቷ ከበስተኋላዋ ተጠግቶ በእጆቹ ግጥም አድርጐ ዓይኖቿን ሸፈነና

" ሶስት ስም ጠርተሽ ማንነቴን ገምተሽ ካላወቅሽኝ ትላሚያለሽ" አላት።

እሷም በችኮላ፤– "አጼ ቴዎድሮስ፣ አጼ ዮሐንስ፤ አጼ ምኒልክ" አለች።

ሰውዬው የጥንት ጓደኛውን ቤቱ ይጋብዘዋል። ሚስቱ ያዘጋጀችው ነገር ስላልነበረ "ቡና አፈላለሁ አደራ ምግብ አቅርቢ እንዳትለኝ" ብላ አስጠንቀቀችው። ቡናው ተፈላና በጠረጴዛው ዙሪያ ቁጭ ብለው እየጠጡ እያለ እንግዳው ሊሄድ መሆኑን ገለጸ። ባል ሆዬ የተነገረውን ረስቶ "ቆይ ራት በልተህ ትሄዳለህ" ይለዋል። እንግዳው ድንግጥ ብሎ እመር ብሎ ይነሳና እሄዳለሁ ይላል። ቢለመን እንቢ ይላል። እንግዳው ከተሸኘ በኋላ ሚስት ሆዬ" ምነው ነግሬህ ራት ካልበላህ ትለዋለህ?" ትለዋለች። ባልም "ውይ ረስቼው እኮ ነው" ይላታል። "እግርህን ደጋግሜ እየረገጥኩ እንዴት አይገባህም?" ትለዋለች። "በጤናው አልቸኮለማ፤ እኔ መስዬሽ እግሩን ስትቀጠቅጪው ቆይተሻላ!" አላት ይባላል።

# ጨዋታና ሰንጠረዥ

## አዕምሮዎን ይፈትኑት

### ያለፈው እትም ጥያቄዎች መልስ

1ኛ.በለጠ፣ ከበደ፣ አበበ፣ ተስፋዬ /ወይም/ ከበደ፣ በለጠ፣ አበበ፣ ተስፋዬ
2ኛ. ሀ – እውነት፤ ለ ሐ ሠ – ውሸት፤ መ – ሊሆን ይችላል
3ኛ. 1ኛ. ላቀች፤ 2ኛ. አስቴር፤ 3ኛ. ቆንጂት፤ 4ኛ. ዓለሙ፤ 5ኛ. ተሰማ፤ 6ኛ. መገርሳ
(አቶ ጫኔ ቢሆነኝ ከዋሺንግተን ዲ ሲ ከ2ኛው በስተቀር ሌላውን በትክክል መልሰዋል)

---

### እስቲ እነኚህን ይሞክሩ፤

1ኛ. ሰባት ሰዎች (በለጠ፣ አሰፋ፣ ተሰማ፣ ረጋሣ፤ ዓለሙ፣ ፍስሃና ዘለቀ) በመደዳ ከግራ ወደቀኝ ፊታቸውን ወደኛ አዙረው ተሰልፈዋል። እያንዳንዳቸው በጀርባቸው ላይ የተለያየ ( ከ1 እስከ 7) ቁጥር ለጥፈዋል። አንዱ ያለውን ቁጥር ሌላው የለውም። ትንሽ መመሪያ (hint) እንስጠትና የእያንዳቸውን ቁጥር ይነግሩናል። የረጋሣ ቁጥር ከበለጠ ቁጥር በሶስት ያንሳል። የአሰፋ ቁጥር መካከለኛው ነው። የፍስሀ ቁጥር ከአሰፋ የሚያንሰውን ያህል የተሰማ ቁጥር ከረጋሳ ይበልጣል። የዘለቀ ቁጥር ከዓለሙ ይበልጣል።

____ በለጠ ____ አሰፋ ____ ተሰማ ____ ረጋሣ ____ ዓለሙ ____ ፍስሃ ____ ዘለቀ

---

2ኛ.ጣርማ፤ ቡቃያ፤ ጠንበል፣ ጦስኝ፣ ሰግርና አምባር ስድስት ጉረቤታማ ከተሞች ናቸው። ጣርማ ከቡቃያ በስተሰሜን ከጠንበል በስተምዕራብ ይገኛል። ጦስኝ ከጣርማ በስተሰሜን ከሰግር በስተምዕራብ ይገኛል። አምባር ከጣርማ በስተደቡብ ምሥራቅ ይገኛል። በሉ እንግዲህ በዚህ አባባል ከሚቀጥሉት የትኛው ልክ የትኛው ስህተት እንደሆነ ይጠቁሙን።

1. ሰግር ከጠንበል በስተደቡብ ነው።
2. ጠንበል ከአንባር በስተደቡብ ነው።
3. ጠንበል ከጣርማ በሰስተሰሜን ምዕራብ ነው።
4. ቡቃያ ከጦስኝ በስተደቡብ ከጠንበል በስተሰሜን ነው።
5. ቡቃያ ከአምባር በስተምዕራብ ነው።

---

## ያለፈው ሰንጠረዥ መልስ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 ፌ | 2 ሳ | 3 ሰ | 4 ፉ | ■ | 6 ቃ | 7 ሰ | 8 ሽ | 9 ባ | 10 ፏ |
| 11 ሬ | 12 ገ | 13 ሙ | ■ | 15 መ | 16 ተ | 17 ኛ | 18 ች | ■ | 20 ሙ |
| 21 ስ | ■ | 23 ኞ | 24 ፋ | 25 ተ | 26 ኛ | ■ | 28 ዓ | 29 ገ | 30 ግ |
| 31 ገ | 32 ጠ | 33 ር | ■ | 35 ው | ■ | 37 መ | 38 ጸ | 39 ሰ | 40 ል |
| 41 ዛ | 42 ገ | ■ | 44 ሽ | ■ | 46 ሽ | 47 ል | 48 ል | 49 ም | ■ |
| ■ | 52 በ | 53 ቀ | 54 ሰ | 55 ተ | 56 ሬ | 57 ከ | ■ | 59 ን | 60 ብ |
| 61 የ | ■ | 63 ች | ■ | 65 ሽ | 66 መ | 67 መ | 68 ው | ■ | 70 ሙ |
| 71 ሽ | 72 ች | 73 ር | 74 ገ | 75 ም | ■ | 77 ል | 78 ባ | 79 ሽ | 80 ግ |
| 81 በ | 82 ል | ■ | 84 ጹ | 85 ር | ■ | 87 ካ | 88 ና | 89 ጸ | ■ |
| 91 በ | 92 ቅ | 93 ሙ | 94 ም | ■ | 96 የ | 97 ም | 98 ች | 99 ሳ | 100 ቸ |

እንዳለፉት ቃላት በሰንጠረዥ ጨዋታ ነው የሚጫወቱት። ለእንግሊዝኛው የአማርኛ ትርጉም በመስጠት፤ በአማርኛ ለተጻፈው ስሜት በሚሰጥ ተስማሚ ትርጉም ሰንጠረዡን ይሞላሉ። መልሱን የሠራችሁ ላኩልን። መልሱንና በትክክል የሠሩትን ስም ዝርዝር ሲልኩልን አብረን እናወጣዋለን።

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | ■ | 9 | 10 |
| 11 | 12 | 13 | 14 | ■ | 16 | 17 | 18 | 19 | ■ |
| 21 | 22 | 23 | ■ | 25 | 26 | 27 | ■ | 29 | 30 |
| 31 | 32 | ■ | 34 | 35 | 36 | ■ | 38 | 39 | 40 |
| 41 | ■ | 43 | 44 | 45 | 46 | ■ | 48 | 49 | 50 |
| ■ | 52 | 53 | 54 | ■ | ■ | 57 | 58 | 59 | ■ |
| 61 | 62 | 63 | 64 | ■ | 66 | 67 | 68 | ■ | 70 |
| 71 | 72 | 73 | ■ | 75 | 76 | 77 | 78 | 79 | 80 |
| 81 | 82 | ■ | 84 | 85 | ■ | 87 | 88 | 89 | 90 |
| 91 | 92 | 93 | 94 | ■ | 96 | 97 | ■ | 99 | ■ |

## ወደጎን

1. God's Work
9. Night
11.parasite
16.Soft
21.Earth
25. Saliva
29.Common
31.She is sick
34.መጨፍለቅ
38.When they are far.
43.ፈታሽ
48.Uncle
49.ጥፍራም/ገሪባ
57.a type of disease
61. Frightening
66. He estimated
71.Get of my sight (ለሴት)
75.seen at dark
81.happy/good
84.enough
87.used to have duplicates
91. to talk
96. divorce

## ወደታች

1. Complicated
2. እህል የሚወቃበት
3. equipment
4. Send
6. Phone call
7. በጃሜይካ ያሉ
9. to interpret
25. ባሌ ውስጥ ያለ ወረዳ
30. Naked
34. Inspector
38. When he teaches
43. ትልቅ ሰታቴ ድስት
52. Go fast and
57. An applicant
61. አጠፋ
66. He bumped
70. We saw
75. agony
79. ቤተክርስቲያን የሚገኝ
84. Door

# የላንዳፍታ መጽሔት ደምበኛ ይሁኑ!

ይህች ውብ ድንቅ የሆነች መጽሔት በምትታተምበት ጊዜ ሁሉ እንዲደርሶት
የሚከተለውን ቅጽ ሞልተው ከነክፍያው ይላኩልን።
ለአራት ተከታታይ እትሞች ክፍያው እንደሚከተለው ነው።

| | |
|---|---|
| ለዩናይትድ ስቴትስ | $12.00 |
| ለካናዳ | U.S. $15.00 |
| ለአውሮፓና እስያ | U.S. $18.00 |

የሚላክሎት በመጀመሪያ ደረጃ ፖስታ አገልግሎት ይሆናል።
ክፍያው በሙሉ በአሜሪካን ብር ሆኖ በMoney Order ይሆናል።

---

ቅጹን ሞልተው ከክፍያው ጋር ሲልኩ ስም ይመዘገብና ዕጣ ውስጥ ይገባል።
ዕጣ ከወጣሎት ከሚቀጥሉት ሽልማቶች በዕጣው አወጣጥ መሠረት ተሸላሚ ይሆናሉ።
1ኛ ዕጣ - ባሉበት ከተማ በሚገኝ በሚፈልጉት የኢትዮጵያ ሬስቶራንት ከጓደኛዎ ጋር የራት ግብዣ ወጪ - $30.00 በአድራሻዎ ይላክሎታል
2ኛ ዕጣ - ለሁለት ጓደኞችዎ የአራት እትም "ላንዳፍታ" መጽሔት ደምበኝነት በነፃ
3ኛ ዕጣ - ለአንድ ጓደኛዎ የአራት እትም "ላንዳፍታ" መጽሔት ደምበኝነት በነፃ
(እጣው የሚወጣው በሜሪላንዱ የእግር ኳስ ጨዋታ ወቅት ይሆናል)

---

በተጨማሪ ከዚህ በታች ያለውን ቅጽ በመሙላት ለራስዎና ለአንድ ጓደኛዎ የላንዳፍታን መጽሔት የጎደኛዎ የደምበኝነት ክፍያ ሲደርሰን የ፲፱፻፹፮ ዓ.ም. ካሌንደር (በላንዳፍታ የሕትመት ክፍልና በሞዴት ኢትዮጵያ የግዕዝ ሶፍትዌር ኩባንያ የተዘጋጀ) በተጨማሪ የ$1.00 ክፍያ ብቻ እንልክሎታለን። የ$1.00 ክፍያውን አብረው ይላኩ። ይህ ስጦታ ለጎደኛዎ ጭምር ሲያዙ ብቻ ነው።

## LANDAFTA SUBSCRIPTION FORM

For Office Use :

Name ______________________________

Address ______________________________

City ______________ State ________ Zip ______________

Phone (______) ______________

---

*Please, send my gift subscription to the following person. (Please, include a payment of $12.00 for U.S. , $15.00 U.S. for Canada or $18.00 U.S. more for Europe .)*

Name ______________________________

Address ______________________________

City ______________ State ________ Zip ______________

Phone (______) ______________

*Please, send money order or check payable to:*

*LANDAFTA. P.O.Box 49301, Atlanta, GA 30359*

# CP TRAVEL ሲፒ የጉዞ ወኪል

*WISHES YOU*
*A HAPPY ETHIOPIAN NEW YEAR !!*

## እንኳን ለአዲሱ ዓመት
## በሰላምና በጤና አደረሳችሁ።

## በአዲስ ዓመት
## ልዩ ቅናሽ


## ከአትላንታ -- አዲስ አበባ *$1,515.00*

ለማንኛውም የጉዞ አገልግሎት
በርካሽ ዋጋ

Special to
AFRICA

## ATLANTA TO ADDIS ABABA
## *$1,515.00 Only*

** Some restrictions apply*



## ሲፒ የጉዞ ወኪል

AT LINDBERGH PLAZA
2851 PIEDMONT ROAD, N.E. SUITE B-1000
Phone: (404) 233 - 2511 - Fax: (404)231-9557

ሕዳር ፲፱፻፹፮ ዓ.ም NOVEMBER - DECEMBER 1993

| እሁድ SUNDAY | ሰኞ MONDAY | ማክሰኞ TUESDAY | ረቡዕ WEDNESDAY | ሐሙስ THURSDAY | ዓርብ FRIDAY | ቅዳሜ SATURDAY |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፩ 1 / 10 | ፪ 2 / 11 | ፫ 3 / 12 | ፬ 4 / 13 |
| ፭ 5 / 14 | ፮ 6 / 15 | ፯ 7 / 16 | ፰ 8 / 17 | ፱ 9 / 18 | ፲ 10 / 19 | ፲፩ 11 / 20 |
| ፲፪ 12 / 21 | ፲፫ 13 / 22 | ፲፬ 14 / 23 | ፲፭ 15 / 24 | ፲፮ 16 / 25 | ፲፯ 17 / 26 | ፲፰ 18 / 27 |
| ፲፱ 19 / 28 | ፳ 20 / 29 | ፳፩ 21 / 30 | ፳፪ 22 / 1 | ፳፫ 23 / 2 | ፳፬ 24 / 3 | ፳፭ 25 / 4 |
| ፳፮ 26 / 5 | ፳፯ 27 / 6 | ፳፰ 28 / 7 | ፳፱ 29 / 8 | ፴ 30 / 9 | | |
| | | | | | | |

## የሀዳር ወር ፲፱፻፹፮ ካሌንደር

የዓመቱን ለማግኘት

$5.00

ለላንዳፍታ ይላኩ

ላንዳፍታ
Landafta
P.O.Box 49301
Atlanta, GA 30359
Phone: (404)728-9122

የኢትዮጵያ ኮምፒዩተሮችና ሶፍትዌር
Ethiopian Computers & Software
9781 W. Fremont Pl.
Littleton, Colorado 80123, USA

Phone (303) 972-2186
Fax (303) 973-4342

መርሐ ትልቁ ዘመን ዘኢትዮጵያ ፡፡ ፲፱፻፹፮ ዓ.ም ፡ ዘመነ ማርቆስ ፡ አበቅቴ ፲፰ ፡ መጥቅዕ ፲፪ ፡፡
በሞዴት የኢትዮጵያ ቃላት ማተሚያ የተሠራና የታተመ የኢትዮጵያ (ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን) ቀን መቁጠሪያ
Ethiopian calendar (1986) created with NodEth, the Ethiopian Word Publisher

ቀይ ልድ ሄር

Live Reggae

THE WILD HARE
& SINGING ARMADILLO FROG SANCTUARY




CHICAGO

(312) 327 - Hare